ኪሎ ሜሬት ኋልፈው ሱዳን ድንበር ላይ የሚያለሙ የትግራይ ልጆች ነበሩ:: በተለይ አቶ ተስፋዬ አድዋ፤አቶ ተስፋየ ሊንሳ፤ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ከሁመራ ባላባቶች ጋር ተስማምተው መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ሱዳንን ገርፈው የሰደዱ ሲሆኑ ልማታቸውን አስከብረው ኑረዋል:: እኔ እስከማውቀው ድረስ የወልቃይት ልጆች ለአገራቸው ያደረጉት ልማትና ድንበር ጥበቃ ሊያስመሰግናቸው ይገባል:: ስማቸውን የማስታውሰው ፊታውራሪ ሰረበ ለማ፤ አቶ ጌታቸው ይርጋ፤ አቶ አቡሃ አብተው፤ መላከ ሰላም ሲሳይ አየልኝና ሌሎች ብዙ ጀግኖች ተዋግተው አገራቸውን አስከብረው ነበር::"

"ዛሬ እንሆ እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸውን በጥቂቱ የጠቀስኳቸው ግለሰቦችና የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ ተዋግቶ ያስቀረውን መሬት ለሱዳን ሊሰጡ ነው:: ለሚቀጥለው ትውልድ የምመክረው ነገር ቢኖር ከሁመራ እስከ ጋንቤላ 1600 ኪሎ መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ታስቧል:: እኔ ዛሬ እድሜዬ ከ70 ዓመት በላይ ነኝ:: ስለ ሀገሬ ግን እንገበገባለሁ:: እበሳጫለሁ! ስለዚህ ዛሬ 20 ዓመት የሞላህ ወጣት አትርሳ አለብህ አደራ:: ቀደም የነበሩ አባቶችህ አንድ ሁነው ተባብረው ኢትዮጵያን አቆዩን እኛም በአቅማችን ተዋግተን አቆየን:: ዛሬ ወያኔ ለሱዳን ሲሰጥብህ እንደ ቀድሞዎች አባቶቻችን "እብሚ ለሀገሬ" ብለው ተነስና አንድነትህ አስከብር አደራ እልሃለሁ" ሲሉ ገልጸውልኛል::

እንባቢያን በአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች ቀላድ አትጥሉበትም ሲባሉ ለሱዳን ሸጠዋል ይባላል:: እነዚህ አንዳንድ ግለሰቦች ከግል ጥቅማቸው ጋር እያይዘው በግዴለሽነት መሬቱን ለሱዳን ሊሰጡ በመታሰቡ የአካባቢው ሕዝብ የገጠሩ በሕይወቱ የከተማው በሥነ መንግሥት ተከራክሮ ያስቀረ መሆኑ ታሪክ የነገረን ሲሆን ዛሬም ይህ ተመሳሳይ ድርጊት በመፈጸም ላይ መሆኑን ማስገንዘብ እሻለሁ::

የአስር አለቃ አባይነህ መሸሻ!



## ምክንያት ሶስት

አቶ ዘውገ ፈንታ፤ "የኢትዮጵያን የሚያውቁት የደህንነትና የአገር ግዛት፤ የፖሊስ ጽፈት ቤት እንዲሁም ውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ባለሞያዎች ናቸው:: የተሳለውን ካርታ ርቀቱንና ርዝመቱን የሚያውቁት" በማለት በወቅቱ የገጸ ምድር ካርታ ድርጅት ሠዓሊው አስረድተውኛል:: በእርሳቸው አገላለጽ "አንድ እስክርቢቶ ጭረት ያረፈባት በጣም ብዙ ኪሎ ሜትር ስለሚሆን በትክክል መጠኑን ልነግርህ አልችልም:: ምክንያቱም የሀገር ጉዳይ ነው" ብለውኛል::

ግለሰቦች ይህን ካርታ በ250 ሺህ ብር ለሱዳን ሸጠዋል:: የሚባለውን ወሬ ደጋፊው ብዙ ነው:: የአቶ ዘውገ ፈንታን አባባል ሻለቃ ጌታቸው የሮም ወሬ ሳይሆን ትክክል ነው በማለት ከመጽሐፋቸው ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል መቶ አለቃ በቀለ ወ/ጊዮርጊስ፤ መሆናቸውን ገልጸው ነግረውኛል::: በገንዘብ ተሸጧል ከሚለው ላይ የሁሉም አንድ ሲሆን አቶ ዘውገ! ጀኔራል ነው ሲሉኝ ሻለቃ ጌታቸው የሮም ደግሞ መቶ አለቃ ነው አሉኝ:: የአቶ ዘውገ አባባል " ካርታውን ሰርተን እንደጨረስን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ስልክ ተደውሎ ካርታውን ለማንም እንዳይሰጥ በተለይ እገሌ እንዳይወስድ ምስጢር ነው ብለው አስጠነቀቁኝ" ሲሉ ነግረውኛል:: እኔ አቶ ዘውገን ከውጭ ጉዳይ ሚንስትር ስልክ ደውሉ ማን እንዳስጠነቀቃቸውና ለእገሌ አትስጥ ተብሎ የተነገራቸውን ስም ይነግሩኝ እንደሆን 3 ቀን በተለያዩ ጊዜ ጠይቄያቸው ከላይ ያሉትን መድገም ካልሆነ በቀር አስጠንቃቂውንም ሆነ እንዳይወስድ ስም ተጠርቶ የተነገራቸውን ስም እንዲነግሩኝ ብጠይቅ ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም:: ይህ በገንዘብ ተሸጧል የሚለውን ወሬ ሳይሆን ትክክል ነው ጎንደር ድረስ ተሰምቷል ሲሉ አቶ ወልደ ገብርኤል ደግመውኛል::

ሻለቃ ጌታቸው የሮም <u>ስም ከመቃብር በላይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 106-107 "በወሎ ጠቅላይ ግዛት ደሴ ከተማ ተወለዱ:: የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም በተወለዱበት በደሴ ከተማና በኋላም አዲስ አበባ በመምጣት በከፍተኛ ነጥብ አጠናቀዋል:: በዚሁ መሠረት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ገብተው በመማር ላይ እንዳሉ በነበራቸው የወታደርነት ፍላጎትና ዝንባሌ የዩኒቨርስቲውን ትምህርታቸውን አቋርጠው በ1960 ዓም ሀረር ውስጥ በነበረው የጦር ሰራዊት አካዳሚ ት/ቤት ይገባሉ::"

"ከሀረር ጦር አካዳሚ በትምህርታቸው የላቀ ውጤት በማስመዝገብ በ1964 ዓም በክብር ተመርቀው የምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ ያገኛሉ:: በትምህርታቸውና በአካል ብቃት እንቅስቃሴያቸው ከፍተኛነት ከተመረጡበት ወጣት መኮንኖች አንዱ በመሆን ወደ አርሚ አቪየሽን በረራ ሥራ ላይ እያሉ በ1966 ዓም በተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅ ሣቢያ የመንግሥት ሥልጣን ለመቆጣጠር ብቻውን ወታደራዊ ቡድን ውስጥ ይገባሉ:: በዚሁ ቡድን ውስጥም እየሠሩ ሳለ በ1967 ሕዳር 14 ቀን ቀደም ብለው በእስር ላይ በነበሩበት

ከፍተኛ ባለስልጣኖች ላይ የፖለቲካ እርምጃ በማለት በወሰነው ኃይል እርሳቸውም አብረው ተገድለዋል" ሲሉ ጽፈዋል።



መቶ አለቃ በቀለ ወልደ ጊዮርጊስ!

ሻለቃ ጌታቸው የሮም ጋር ስንወያይ "ይህ መቶ አለቃ በቀለ ታስሮ ከተፈታ በኋላ ከየቦታው የተሰባሰበው ደርግ ካርታውን የሸጠ መሆኑን እንዳወቀ እስሮ ከ60ዎቹ ጋር ገደለው" ብለውኛል። ገጸ ምድር ካርታው ተሸጧል በማለት አቶ ዘውገ ፈንታ ያምናሉ አሟሟቱን አስመልክቶ ደግሞ እርሳቸው እንዲህ ይላሉ "እኔ በዚህ ወቅት ከአገሬ አልነበርኩም የሰማሁት ታሪኩን ነው። አንድ ቀን መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እስረኞችን ሲጎበኝ እርሱ የታሰረበትን ምክንያት ሲጠይቅ በአገር ምስጢር ካርታ በመሸጡ ነው ብለው ሲነግሩት ከሀዲን አስራችሁ ትቀልባላችሁ በሉት" ብሎ በማዘዙ መገደሉን ሰምቻለሁ ሲሉ ነግረውኛል። ስማቸው እንዳይነገር የፈለጉት አዛውንት መቶ አለቃ በቀለ፣ የተጠቀሙበት
1ኛ ልጅ በመሆኑ
2ኛ ከእነሱ ያልሆነ ሰው በመሆኑ አዘውታል"።



"ምስጢሩ ሲጋለጥ የደህንነቱ ሰዎች ቢያስሩትም እንዲፈታ ሆነ። እንዲያውም እነሱ እንዳይጋለጡ በለፈጉ እንዳይመረመር አስደርገዋል። የመቶ አለቃ በቀለ፣ ከውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሆነ ከካርታ ድርጅት አለቆች ጋር ግንኙነት ሲኖረው ይችላል። ነገር ግን ይህን ተንኮል ለመፈጸም እርሱ ሲሆን አይችልም። ሌሎች ባለሥልጣኖች ከሱዳን መንግሥት ጋር ግንኙነት አድርገው ከተስማሙ በኋላ እርሱ ካርታውን እንዲያደርስ አድርገውታል። ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይሰራ የነበረ አንድ ሰቪል ደርግ ደርሶበት ከአንድ በሲ.አ.ኤ ከተጠረጠረ ግለሰብ ጋር የተገደለ ሲኖር ሌሎች ግን ሳይነቃባቸው ያመለጡ ዛሬ ድረስ በሕይወት ያሉ ናቸው" ሲሉ ነግረውኛል።

<u>ስም ከመቃብር በላይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 372 "የመተማንና የሁመራን አካባቢዎች ለሱዳን አሣልፎ ለመስጠት የነበረውን ድርድርና ስምምነት አጥብቀው እንደሚቃወሙ ይጠረጠሩ የነበሩት የቤጌምድርና ስሜን አጠቃላይ ግዛት ፖሊስ አዛዥ ብ/ጄኔራል ሥዩም ገሠሠና አባሪዎቻቸው ናቸው የተባሉትን ሁሉ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ይደረጋል" ሲሉ ጽፈዋል። ከላይ የዓይን ምስክሮች የተናገሩት ታሪክ ከዚህ ከፍ ተብሎ ከተነበበው የመጽሐፍ ጥቅስ ጋር ይገናኛል። ቅድሚያ መሬቱ በቀላድ መያዝ የለበትም በማለት አድማ ያደረጉት ሰዎች ሁሉ እንዲዛወሩ ተደርገዋል። የአቶ ወልደ ገብርኤል አበጌና የአቶ ሊቀ እጅጉ ምስክርነት ከሻለቃ ጌታቸው የሮም አጻጻፍ ጋር ተመሳሳይ ነው። መንግሥታት የተሰጣትን የራስ ገዝነት መብት በራሷ አፍርሳ ከኢትዮጵያ ጋር ኤርትራ ከተቀላቀለች ጀምሮ አንዳንድ የኤርትራ ተወላጆች ወደ አረብ አገርና ግብጽ መሰደድ ጀመሩ።

በአረቦች ድጋፍ ጀብሃ በ1954 ዓም ካይሮ ተመሰረተ። አረቦች ቀደም ጀምረው ኤርትራ ነፃ አገር መሆን ይደግፉ የነበረው ለኤርትራ ሕዝብ ደህንነት ብለው ሳይሆን ቀይ ባህርን በቁጥራቸው ስር ለማድረግ አስበው ነበር። ለዚህም ዋናው የኢትዮጵያ መንግሥት ከቀደም ጀምሮ የንጉስ ሰሎሞን ጋር የተያያዘ ግንኙነት መኖርና የእስራኤል መንግሥት መመስረት ቀይ ባህርን በሕብረት እንዳይጠቀሙበት ለማድረግ አረቦች ፀረ ኢትዮጵያ የሆኑ ጀብሃን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ግለሰቦች እንዲከዱ ለማድረግ ጥረት አድርገዋል። በ1962 ዓም አውሮፕላን ጠልፈው ሱዳን ያረፉት ተማሪዎችን የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አስሮ ለማምጣት ያደረገው ድርድር በባዶ ተፈጽሟል። ሱዳን እነዚህን ተማሪዎች ለኢትዮጵያ መንግሥት አሳልፋ እንዳትሰጥ አረቦች ጥረት አድርገዋል። ደግሞም ተሳካላቸው ተማሪዎቹ ከሱዳን አልጄሪያ እንዲሄዱ ነው የተደረገው።

ያሬድ ጥበቡ የአመጹን <u>አዙሪት ለመስበር</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 8 "ከ30 ዓመት በፊት ከባህርዳር በጠለፉት የእንቁላል ማመላለሻ አውሮፕላን ጀግንነታቸው ብቻ እያደነቅን እንድንኖር ለምንድን ነው የተፈረደብን? ምናልባት ዲፕሎማሲ አዲስ መስክም ስለነበር እየወደቁ እየተነሱ መማር ስለነበረባቸው ነው የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል። ግን በድርጅት መስክስ የአቶ

ኢያሱ አመራር በፓርቲው ምን አተረፈው?" ሲሉ ጽፈዋል። በኢትዮጵያ ታሪክ አውሮፕላን መጥለፍ ያስተማሩ በዚያን ወቅት ከጠለፉት መካከል በሕይወት ያሉ አቶ ኢያሱ አየማየሁ ናቸው። የተማሪውን የትግል ታሪክ ስትመረምሩ የምታገኙት ሠነድ የአልጀሪያው ቡድን የሚለው ሁሌም የነአቶ ኢያሱ አለማየሁና አቶ ብርሃነ መስቀል ሌሎችም ሁነው የጻፉት ነው።

በአቶ አሰፋ ጫቦ "ጥናት መሰረት ዛሬ የአንቀጽ 39 መንስኤ እንዴት ወደ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ እንደደረሰች ሲያትቱ ያችን የብሔሮችን ጽሑፍ ያረቀቋት ጀብሃ ሲሆን ለነአቶ ኢያሱ አለማየሁ ተሰጥቶአቸው እነሱ ሉስ አንጀለስ ይማሩ ለነበሩት ለዛሬው ሊቀ ጠበብት እንድርያስ እሸቴ ልከውት እርሳቸው አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ይማሩ ለነበሩት ለአቶ ዋለልኝ መኮንን ልከዋታል። አቶ ዋለልኝ መኮንን እንደበተ ሩሑቱ በመሆናቸው የራሳቸው አድርገው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አደረሷት" ይላሉ። ይህ ብሔራዊ መፈክር ሁኖ የወጣው ሠነድ ውሎ አድሮ በኢሕአፓ መርሃ ግብር መካተቱ አይዘነጋም። ከዚያም ደግሞ ወያኔ አንቀጽ 39 ቀርፆ እንሆ ኢትዮጵያን እያፈረሰበት ይገኛል።

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ አዛውንት "አረቦች በዚህ ወቅት በኤርትራ የተጀመረው እንቅስቃሴ በአጭር እንዲቀጭ ለማድረግ የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አረቦችን ለማስደሰት ሲሉ እነሱ የሚያዙአቸውን ሲፈጽሙ ኑረዋል። ዓረቦች ምንጊዜም ለኢትዮጵያ የማይተኙ መሆናቸውን የአጤው መንግሥት አልተረዳም ነበር። አረቦች ቅድሚያ ያደረጉት ኢትዮጵያ ከእስራኤል ጋር የነበራትን ግንኙነት እንድታቋርጥ ነበር።"

"አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእስራኤል ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያቋርጡ አሰበለዚያ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል የሆኑ በሃይማኖት እስላም የሆኑትን አገሮች ሊያቋርጡ ይፈልጋሉ ሲሏቸው አጤው በዚያን ወቅት የዓለም አባት ለመባል ይፈልጉ ስለነበር በሳውዲያ አረቢያ ንጉሥ የቀረበላቸውን ጥያቄ ሳያቅማሙ ተቀብለዋል። በእርግጥ አረቦች ቃል የገቡላቸው እርሳቸው ከእስራኤል ጋር ያላቸውን ግንኙነት ካቋረጡ እነሱም የጀብሃን ታጋዮች መርዳት እንደማይፈልጉ ነገሩአቸው ነበር። ስለዚህ አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእስራኤል ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አቋረጡ። በተለይ ይህን ግንኙነት ማቋረጥ እንደሌለባቸው የሃይማኖት ሊቃውንቶች ተማጽነው ነበር። ነገር ግን አረቦች በቃላቸው አልጸኑም። እንዲያ መርዳት ሊያቋርጡ ቀርቶ ይበልጥ እንዲጠናከሩ አድርገዋል" ሲሉ ተናግረዋል።

የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለስልጣኖች በጉቦም ሆነ በሌላ መንገድ የፈለጉትን ካስደረጉ በኋላ ቅድሚያ ከዘውድ ምክር ቤት ውይይት ተደረገበት። ችግር ሲፈጠር ወደ ሕዝብ ምክር ቤት ገባና የባሰ ተደባደቡበት። አንድ ግልጽ ሊሆንልኝ ያልቻለ ጉዳይ ደግሞ ውይይት የተደረገበት ቅድሚያ ከሕዝብ ምክር ቤት ወይስ ዘውድ ምክር ቤት ነው? የሚለውን ትክክለኛ ታሪክ ማግኘት አልተቻለም።



ፈንታዬ ወ/ዘሊባኖስ <u>የአባ ጠቅል አጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 307 "አንዳንዴ በየጊዜው ከሚነሱት ብሔራዊ ዓላማ ከነበራቸው ጉዳዮች መካከል በጣም አከራካሪ የነበረው የሰቲት ሁመራ የእርሻ ልማት እየተስፋፋ በሄደበት ጊዜ የኢትዮጵያና የሱዳን የድንበር ወሰንን አስመልክቶ የተነሳው ክርክር ነበር። በዚህ በኩል ለብዙ ዘመን ሳይከለል በቆየው በዚህ ወሰን አካባቢ በቅርቡ በተገኘው በሁለቱ አጎራባች አገሮች የወዳጅነት መቀራረብ ላይ ተመስርቶ ሰፋ ያለ መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ነው ተብሎ ያልተጣራ ወሬ ተናፈሶ ነበርና ይህንን ዓይነት የተዛባ ስምምነት እንዳይፈጸም በተለይ የቤጌምድርና የስሜን ጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎች አንድ ላይ በመቃወም ባቀረቡት ሀሳብ ሌሎች የምክር ቤቱ እንደራሴዎች ባለመደገፋቸው በተነሳው ክርክር ከፍ ያለ የሀሳብ መለያየት ላይ በተፈጠረው አለመግባባት እርስ በርስ መደባደብ ደርሰው እንደነበር አስታውሳለሁ። ስለሆነም በዚህ ምክንያት ጉዳዩ እልባት ሳያገኝ ቀርቷል" ሲሉ ጽፈዋል።

ክቡር አቶ ፈንታዬ ወ/ዘሊባኖስን ከዚሁ አሜሪካ ሰላሉ ታህሳስ 12 ቀን 2001 ዓም በስልክ እናግሬያቸው ነበር። እርሳቸውን ያቀረብኩላቸው ጥያቄ "በመጀመሪያ ምክር ቤት እንዴት ለውይይት ሊያቀርበው ቻለ?" የሚል ጥያቄ ነበር ያቀረብኩላቸው እርሳቸው "በውነቱ እኔ እንዴት እንደተጀመረ አላስታውስም። የማስታውሰው ክርክሩን ነው። በስም ጠርቼ እገሌ አቀረበው ለማለት የዘነጋሁት ሲሆን ወደ ሕዝብ ምክር ቤት ለውይይት ያቀረቡት የአካባቢው እንደራሴዎች ናቸው። ለውይይት አጀንዳ ሊያዝ አይችልም ያሉት የሐረር እንደራሴ ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ ናቸው። ሁመራ በወቅቱ ስመጥር የሆነው በአጭር ጊዜ ሥራ ብዙ ገንዘብ የሚገኝበት መሬት በመሆኑ ነው" ብለውኛል።

ይህን በተመለከተም በወቅቱ የኢትዮጵያ የካርታ ስራ ይሰሩ የነበሩት ፎቶ ግራፈሩን አቶ ዘውገ ፈንታንም ደጋግሜ ጠይቄያቸው ነበር። አቶ ዘውገ ፈንታ፤ እንዴት ሊጀመር ቻለ?ለሚለው ጥያቄ መልሳቸው" በተለይም ሰሜን ኢትዮጵያን ለማልማት የዓለም ባንክ የሚሰጠው ገንዘብ ነበር በዚህ ወቅት የሁመራ ልማት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። የሁመራ ልማት ከፍ ማለት ሲጀምር ሱዳኖች ቅናት አድሮባቸዋል። በወቅቱ እንደተባለው በግብጽ ወይም በዓረብ አገሮች ግፊት ምክንያት ተነሳስተው ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህ ደንበራችን ይወሰን ብለው ጠየቁ። በዚህ ምክንያት ምክር ቤት ሊደርስ ቻለ? እንዴት ምክር ቤቱ እንደሰማው አላውቅም" ብለውኛል።

ልጅ እግዛው ውብነህ <u>ራስ አሞራው ውብነህ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 146 "1964 ዓም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሰብሳቢነት ከጠቅላይ ሚኒስቴር እስከ ም/ሚኒስቴር የየጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴዎች የሕግ መወሰኛ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት እንዲሁም የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዜዳንትና አባሎች በተሰበሰቡበት በቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ከሁመራ እስከ ጎጃም የሚያዋስነውን የኢትዮጵያና የሱዳን ወሰን ድምብር ስለሚያካልለው በውጭ

ጉዳይ ሚኒስቴር በጠቅላይ ሚኒስተሩ የቀረበው ሐሳብ ከተነበበ በኋላ በአጤ ምኒልክ ጊዜ ሱዳን በእንግሊዝ ቅኝ ገዢነት ስር በነበረችበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሰው የሱዳንና የኢትዮጵያን ድንበር እንዲከለል" ሲሉ ጽፈዋል።

በፋ. አድርገው ታሪክ ጠቅሰው የጻፉት ሲሆን በራስ አሞራው ውብነህ ተሰማ አባባል ደግሞ "የየጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴዎች" የሚለው ቃል ሳነብ ቅድሚያ ከዘውድ ምክር ቤት ሳይሆን ከምክር ቤት ውይይት የተደረገበት ይመስላል ከዚህ የሚቀጥለውን ሰነድ ማንበብ ይቻላል።

አምሳ ለቃ (ደጃዝማች) አፈራ አዳነ ራስ አሞራው ውብነህ የነገሩኝ ብለው ያጫዎቱኝ ታሪክ ከዚህ የሚከተለው ነው። "ከምክር ቤቱ ፓርላማው ከተደባደበበት በኋላ ጃንሆይ ይህን ጉዳይ ማን ያውቃል ብለው ሲጠይቁ ራስ አሞራው ውብነህ ያውቃል ተብለው ተነገራቸውና ተጠራን። ጃንሆይ ራስ የኢትዮጵያንና የሱዳንን ድንበር ታውቀዋለህ? ብለው ጠየቁን። እኛም አዎ ጃንሆይ አውሬ ስናድንበት የነበረው ጥርሳችን ሰብሮ ያሳደገን አገራችን ስለሆን ገዳሪፍን አልፎ መደኔ ይደርሳል አልናቸው። ጃንሆይ እርሱንማ አጤ ምኒልክ ተደናብረውታል አሉ። እኛም ጃንሆይ አጤ ምኒልክን የምናከብራቸው የአድዋን ድል በማድረጋቸውና ለኢትዮጵያ ስልጣኔ ማስገባታቸው እንጂ በደንበር ጉዳይ እኮ አናመሰግናቸውም" ብለን በመናገራችን ጃንሆይ ተበሳጭተው ካባቸውን አጣፍተው ሄዱ።"

"ለካ ካባቸውን ካጣፉ ይታሰር የሚል ትዕዛዝ ማስተላለፋቸው ነው። ወዲያው በዚህ መጡ ሳልላጠብደሎች እየገፈተሩ ምድር ቤት አስገቡን። ኋላ ተፈቅዶልን ሕደን እጅ እንድንነሳ ሆነ ጃንሆይ አንተ እሚሉ አጤ ምኒልክን ተሳዳቢ ለ6 ወር ከቤትህ እንዳትወጣ አዘናል ብለው በቁም እስር ከቤታችን እንድንታሰር ሆነ" ብለው የነገሩአቸውን አምሳ ለቃ (ደጃዝማች) አፈራ ሱዳን ሳለን አጫውተውኝ ስለነበር ለማረጋገጥ ጥር 20 ቀን 2001 ዓም ስልክ መታሁና ደንበሩን አስመልክቶ ስንጫወት ሳይረሱት ከ24 ዓመት በኋላ ያንኑ ታሪክ ነገሩኝ። ነገር ግን ስለራ አሞራ ውብነህ መጽሐፍ ላይ ቃል በቃል የተመዘገበ ባይሆንም ተቀራራቢ ነው።

ደንበርን አስመልክቶ የጻፉት ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይመልከቱት። በ1988 ዓም ከአሜሪካ ኢትዮጵያ ስሔድ ሱዳንና ኢትዮጵያ ጠብ ላይ ነበሩ። ይህ የራስ አሞራው ውብነህ አባባል ከጭንቅላቴ ገብቶ ቆይቶ ስለነበር ጎንደር አቶ ማሞ ስበር የት እንዳሉ ስጠይቅ አዲስ አበባ መሆናቸውን ነገሩኝ። ብፈልግ ማግኘት አቅቶኝ ተመለስኩ ኋላ በ1989 ዓም ላይ ስልካቸውን አግኘቼ ደውዬ አነጋግሬአቸው ነበር።

በ1989 ዓም የነገሩኝ "ደንበርን በተመለከተ የፓርላማው ሰብሳቢ ለውይይ አጀንዳ አይያዝም በማለቱ ምክንያት ችግር ሊፈጠር ቻለ። የጎንደር የፓርላማ አባላት ብቻ ሳንሆን የእኛን አቅዋም ደግፈው እስከ መታሰር የደረሱ የሕዝብ እንደራሴዎች የሌሎች ክፍለ ሀገር እንደራሴዎች ተባባሪ ነበሩ" ሲሉ ነግረውኝ



ነበር። በቅርቡ ይህ የደንበር ጉዳይ ከተነሳ በኋላ አቶ ማሞ ስበርን ለማነጋገር ቀደም የማውቀውን ስልክ ስደውል የማይሰራ በመሆኑ የጠቀስኩት በ1989 ዓም የነገሩኝን ነው።

ከላይ ከክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ጹሑፍ መረዳት እንደሚቻለው በጅቡቲ፥ በኬንያ እና በሱማሌ በኩል በግማሽ የተሰመረበት መሆኑን ሲገልጹ በጎንደርና በጎጃም በዛሬው ኤርትራ በኩል እርሳቸው ያልጻፉት ያላለቀ ፋይል ነበር። ሱዳን ከእንግሊዝ ነጻ ከሆነች አንስቶ በጎንደር ክፍለ ሀገር ጎንደር ዙሪያ አውራጃ ታች አርማጭሆ ወረዳ ተወላጆች ሱዳኖች ጓንግ ወንዙን ተሻግረው ማርስን ተመለከቱ። እነዚህ አርማጭሆዎች ሱዳኖችን ማረስ እንደሌለባቸው መከላከል ጀመሩ። ሱዳኖች አትረሱ ሲባሉ ግብር ለኢትዮጵያ መንግሥት እንከፍላለን በማለት ሲያርሱ ይከርሙና ባመቱ ፖሊስ ማዚያ ያቋቁማሉ። ቦታውን በአርብኛ ስም ይቀይሩታል። በዚህ የሱዳኖች ድርጊት ያንገበገባቸው የአርማጭሆዎች የሱዳንን አራሾች የሚጠብቁትን ወታደሮች ተዋጉአቸው። በዚህ ጦርነት አቶ ገብሬ ተወልደ መድህን አቶ ድረስ አይናለምና አቶ አወቀ ዋናሁን፤ እንዲሁም ሌሎች 4 ሰዎች ሞቱ። ከዚህ በኋላ ሱዳኖች ክትት ብለው ነበር።

<u>ስም ከመቃብር በላይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 367 "ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህን ሕያው ታሪክ በመርሳት የኢትዮጵያ አካል ከሆነው መሬት ላይ ክፍለውና ቆርሰው ለሱዳን በችሮታ ለመስጠት በድፍረት ተነስተው ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ ለመደራደር የሱዳን ፕሬዝዳንት የነበሩት ጄኔራል ኑሜሪ አዲስ አበባ መጥተው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት ላይ እንዲገኙ በማድረግ ከሻሳሚው ንጉሥና ከተሸላመዊው ጋር በ1964 ዓም ፎቶግራፍ ተነስተው ታሪካዊ መረጃ እንዲሆን አድርገዋል" ሲሉ ጽፈዋል። አንባቢያን የራስ አሞራው ውብነህ እና የሻለቃ ጌታቸው ደንበርን አስመልክቶ የጻፉትን ከዚህ የሚቀጥለውን ከየራሳቸው መጽሐፍ እንዳለ በየመጽሐፋቸው ላይ ገልብጨ (ኮቢ) አድርጌ ከዚህ በታች ያለውን ተመልከቱ።

በ፲፱፻፷፬(1964)ዓ.ም. በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሰብሳቢነት ከጠቅላይ ሚኒስቴር እስከ ም/ሚኒስቴር የየጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎች የህግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት እንዲሁም የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና አባሎች በተሰበሰቡበት በቤጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት ከሑመራ እስከ ጉሽም የሚያዋስነውን የኢትዮጲያና የሱዳን ወሰን ድምበር ስለሚያካልለው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር[1] በጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀረበው ሐሳብ ከተነበበ በኋላ በዓፄ ሚኒሊክ ጊዜ ሱዳን በእንግሊዝ ቀኝ ገዥነት ሰር በነበረችበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሰው የሱዳንና የኢትዮጲያ ድምበር እንዲከለል ከእንግሊዝ በቀረበው ጥያቄ መሠረት በዓፄ ሚኒሊክ ተቀባይነት አግኝቶ በድንበሩ ላይ ተገኝቶ የሚከለል ሰው እንዲደረግ በተወሰነው መሠረት አንድ በቤጌምድር ሰሜን የሚገኙ ደጃዝማች መሸሻ የተባሉ ተገኝተው ከእንግሊዝ ከተላከው ወኪል ጋር ተገናኝተው ለመከለል በጉዞ ላይ እንዳሉ የዓፄ ሚኒሊክን ሞት ሰምተው በከሉሉ ቦታ ሳይገኙ ወደ ኋላ በመመለሳቸው የእንግሊዙ ተወካይ በቦታው ተገኝቶ በራሱ መንግሥት በሚያመች ሁኔታ የኢትዮጲያ ርስት ኀብት የሆነውን ሁሉ ወደራሱ ክልሉ በማስገባት ድምበርተኛ ያልተገኘበትን ካርታ አንስቶ በሄደው መሰረት ሱዳን ነጻነቷን ባገኘችበት ጊዜ ይህ ህጋዊ ያልሆነውን ካርታ ይዛ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያው በዓፄ ሚኒሊክ ጊዜ የተወሰነ ካርታ ስለሆነ በዚያው መሠረት ሊፈጸም ይገባል ብለው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ባሉበት ለተባለው ጉባኤ ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት ጉባኤውና ንጉሠ ነገሥቱ ከተነጋገሩበት በኋላ አባት የሠራው ለልጅ እንደሚባል ዓፄ ሚኒሊክ የሰሩትን ማፍረስ ስለማይቻል ያው እንግሊዝ በሠራው ካርታ መሠረት ይፈጸም ብሉ ከተወሰነ በኋላ ክቡር ራስ ውብነህ ተሰማም በላይ በተገለጸው መሠረት ውይይት በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ እጃቸውን በማውጣት ለመናገር እድል እንዲሰጣቸው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ይጠይቁ ስለነበረ ከውሣኔ በኋላ ኩመደር እስክንድር ብዙ ጊዜ ያዋቸው ስለነበር የተቀመጡትም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉን ስለነበር ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ራስ ውብነህ እኮ ብዙ ጊዜ እጃቸውን እያወጡ ለመናገር ቢፈልጉ ጃንሆይ አልተመለከቱዋቸውም መሰል እባክዎት ያሳስቡላቸው ባሉዋቸው መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እክሊሉ ኃብተወልድ ለጃንሆይ ራስ ውብነህ ጥያቄ አላቸው መሰል እጃቸውን ያወጣሉ ሲሉዋቸው ጃንሆይ ተመልክተው ተናገር ይሉዋቸዋል፡፡



አምራውም ጃንሆይ ይህ የተባለው የሱዳን ጠረፍ እንግሊዝ ሱዳንን ቀ
አድርጉ ከመጣ ጊዜ ጀምር የእንግሊዝ ሱዳንና የኢትዮጲያ ድንበር
ከአትበራ አልፎ አያውቅም አሁን ሱዳን ነጻነቷን አግኝታም ከቆየች ወ
፲፱፻፶፱(1959)ዓ.ም. የእኛ የጠረፍ ጠባቂዎች ፖሊሶች ተገኝተው እን
ከተደረገ ወዲህ በልዩ ልዩ መደለያ እየተቀበሉ ጥንት ከእንግሊዝ ይዞ
የተባለውን ወንዝ ድምበር ባንድ በኩል አብጢር ከሚባለው ባንድ
ሑመራ አጠገብ ከአይሮፕላን ማረፊያ ጥግ ድረስ ለሱዳን አስረክበው
አስፍርበታል፡፡

ይህች ከላይ የገለጽኳትን ድምበር እኔ ራሴ ያደኩበት በርሃና ጹር
በትክክል የማውቀው የመሬቱን የእንጨቱን ዓይነት የማውቀው ነው፡፡
በዚህ ክፍል የሚገኘው ተወላጅ ቀርቶ የሱዳን ወጣቱ ሳይሆን የሱዳን
አዛውንቱም ቢሆን ይህ ከጎንግ ወዲህ ያለው ወሠን የኢትዮጲያ
ይመሰክራል፡፡

ጃንሆይ በዓፄ ሚኒሊክ ጊዜ አውሮፓውያን መላ የአፍሪካን አህጉር ቀ
በማድረግ ወርሰው ኢትዮጲያን ለመጉረስ በሚያኩበኩቡበት ጊዜ እንኳን
ያልሰጡትን ፈርተው ቢሰጡትም አይፈረድባቸውም አሁን በግርማዊ
ነገሥት ረዳትነት መላ የአፍሪካ ሀገር ነጻነቱን ሲጎናጸፍ እኛ ለሦ
ዘመናት በነጻነት የኖረችውን አገር እንዲት በፈቃዳችን ፈርመን እንሰጣ

ጉልበት አተን በጉልበት ቢወስደው[1] ልጆቻችን ጉልበት ባገ
ይመልሱታል፡፡ በፈቃዳችን መሆን የለበትም ባሉ ጊዜ ግርማዊ ጃንሆ
ማይሉ ከውሣኔ በኋላ በመቃወማቸው ይመስላል ተቆጥተው በመነሳት
ጥለው ይነሳሉ፡

ከዚህ በኋላ ፀሐፊ ትእዛዝ እክሊሉ ኃብተወልድ ጃንሆይን ተከትለ
ውብነህ ጉባኤውን ብቻ ሳይሆን ንጉሠ ነገሥቱንም ደፍረዋል፤ እንድጠ
ይፍቀዱልኝ ብለው በመለከቱት መሠረት የሚመስልህን ሰው ይዘህ
ይሉዋቸውና ይመለሳሉ፡፡

ወዲያውኑ ራስ ውብነህ እንዳይሄዱ ይባላል፡፡ ፀሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ባ

1ኛ. ደጃ/ክፍሌ ዳዲ
2ኛ. ፀሐፊ/ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ

3ኛ. ደጃዝማች ፍሬ አርጋው
4ኛ. ደጃዝማች በዳ ተሰማን ይዘው ራስ ውብነህ ያስጠራሉ፡፡

በኋላ በደጃዝማች ፍሬ ዳዲ ጠያቂነት ክቡር ራስ ለመሆኑ ሥራዎን ያውቁታል
ይሉዋቸዋል፡፡
ዐ አውቀዋለሁ፤
ዲያ ካወቁ የንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ ምክር ቤት አባል ሆነው የዘውድን
ነር ማእረግ በመጠበቅ ፈንታ እንዴት ንጉሠ ነገሥቱ ውሣኔ ከሰጡ በኋላ
ቸውን ውሣኔ በማፍረስና በማዋረድ አፍራሽ የሆነ ነገር ይናገራሉ
ኑዋቸው፤
፣ ንጉሠ ነገሥቱን የሚያዋርድ አልተናገርኩም ንጉሠ ነገሥቱን
ሚያስከብር ነገር ተናገርኩ እንጂ፤ አላዋረድኩም፡፡ የምታዋርዷቸው እናንተ
ችሁ!!

እንኳን በአንደኛ ደረጃ የምወደው ሀገሬንና ነጻነቴን ነው፤ ጃንሆይን
ዳቸው በሁለተኛ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የሚያጠያይቀን ነገር ያለ
ሰለኝም ብለው ሕዝብ ሳያውቀው ታፍኖ ከምቀር ሕዝብ እያየኝ ብታሠር
ል ብለው ከመቅጽበት ተቆጥተው በሩን ከፍተው በመውጣት ከመኪናቸው
፡ ገብተው ወደ መኖሪያ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡

በኋላ ፀሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ይመሩት ከነበረው ጉባኤ ተነስተው ጃንሆይ
ብት ክፍል ገብተው ጃንሆይ ራስ ውብነህ ቀደም ብለው ከተናገሩት ይልቅ
፣ ይበልጥ ሳደረግንላቸው ጥያቄ ምንም አላጠፋሁም በማለት በአንደኛ ደረጃ
ንና ነጻነቴን ነው የምወደው፤ ጃንሆይን የምወደው በሁለተኛ ደረጃ ነው
፣ እኔህ መታሰር አለባቸው እንዲታሰሩ ይፈቀድ ሳሉት፦

ይ ሲመልሱ አክሊሉ እኖቱ ትመስለኝ ነበር ለካስ አታውቅም፣ እንዴት
ብህም ውብነህ እኮ ዛሬ የሰራው ሥራ በአርበኝነት ከሠራው ሥራ የበለጠ
እንዴት ይታሠር ትለኛለህ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ መሣቂያና መዘባበቻ
ደርገን ነው፤ የተናገረውም እውነት ነው ሀገሩንና ነጻነቱን ይወዳል፡፡
ም አይጠላንም፤ ብለው ለሱዳን የተሰጠው ውሣኔ አይተላለፍ ካሉ በኋላ
ንና ኢትዮጲያ ድንበር ሁለቱ መንግሥታት ተስማምተው ውሣኔ እስከተሰጠ
፡ በያሉበት በየይዞታቸው ይቆዩ ተብሎ ተወስኖ እስካሁን በዚያው ውሣኔ
ለ ነው፡፡



ሥም ከመቃብር በላይ

# ክፍል አራት

## የጠረፍ ድንበሮች ጉዳይ

## የኢትዮጵያና የሱዳን ጠረፎች ድርድር

ኢትዮጵያና አጐራባች አገሮችን በሚመለከት ሲጠኑ የሚገባቸው በቂ ትንታኔና ግንዛቤ ሊሰጥባቸው፣ምክንያቶችና ውጤቶች ሊመረመሩባቸው የሚገባቸው ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች አሉ፡፡ የኮንትሮባንድ ንግድን የወንጀለኞች ከአንዱ ወደ ሌላው መዘዋወርና መደበለቅ የዘር ትስስር የግጦሽ ሆነ የእርሻ መሬት ይዞታ የኃይል አጠቃቀምና ቁጥጥር የመሣሰሉት ሌሎችም ሕገ መንግስት ከሚደነግገው ውጭ ባለሥልጣናት የሚያከናውኗቸው ወይም ለመደራደር የሚያደርጓቸው ስምምነቶችና በርካታ ጉዳዮች ሲጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በእያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ውስጥ በተደጋጋሚ የምገልፀውና አንባቢዎችም እንዲገነዘቡልኝ አጥብቄ የምጠይቀው፣ ትረካው ሁሉ የግሌን ምስክርነትና ትዝታዬንም የሚገልፅ መሆኑን ነው። የሱዳንና የኢትዮጵያን ግንኙነት የምገልፀውም በኔ ምስክርነት ሥር ያሉትን እንጂ ርዕሱን በመመልከት ሰፊና ጥልቅ የፖለቲካ ጉዳዮች ተዘርዝረው የሚቀርቡበት አይደለም። የእስከዛሬዎቹ የታሪክ ጸሁፎች መረጃችን ለማስደሰትና የፖለቲካ አመለካከትን ለማንፀባረቅ ሲባሉ የሚቀርቡ በመሆናቸው በተራው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ልብ ውስጥ ያሉትን እውነታዎች ይጋርዷቸዋል። ስለሆነም ሣይገለፁ የታለፉትን፣ ተራ የሚመስሉ ጉዳዮችን በዚህ ቦታ እጠቃቅሳቸዋለሁ። በንጉሠ ነገስቱና በባለሥልጣኖቻቸውም ይሰጡ የነበሩ ውሣኔዎችን በጥቂቱ አሣያለሁ። ታሪክ የህዝብ መሆኑንም የሚመሰክሩ እውነታዎች አቀርባለሁ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተጠቀሱት የተለያዩ ርዕሶች ላይ የጊዜ ጉዳይ በጥቅሉ እንጂ በተለየ ተረጋግጦ አልተገለፀም:: ይህ የሆነው ታሪኩቹን ለመፃፍ ሲባል ከመነሻው ጀምሮ ዕለትና ወር እየተመዘገበ የተሰበሰበ መረጃ ስላልሆነ ነው። ይልቁንም በትውስታ የሚታሰበው የተገለፀበት ነው። የሱዳንና የኢትዮጵያን ግንኙነት በተመለከተ የማነሣው ታሪክ ከ1956 ዓ.ም ወዲህ ያለውን ጊዜ ያመለክታል። ይህም የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የነበረበት ጊዜ በመሆኑ ባለሥልጣናቱም የዚያው ጊዜ ሰዎች ናቸው። በተጨማሪም ትረካው

## ሥም ከመቃብር በላይ

በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር አካባቢ የሚገኙትን የመተማንና የሁመራን አካባቢ የሚያመለክት ነው።

በዚህች አነስተኛ ርዕስ ስር ለመጥቀስ የምሞክረው በኢትዮጵያና በሱዳን ጠረፎች ላይ ስለነበረውና እስከዛሬም ስለሚከናወን አንድ አገራዊ አጀንዳ ነው። ይህን በመሠለ ከተጎንጣይዋ ኤርትራ ጋር በምስራቅ ከምታዋስነን ጅቡቲ ጋር፣ከምስራቅ እስከ ደቡብ ካለችዉ ሶማሊያ ጋር እንዲሁም በደቡብ ከምትገኘው ኬንያ ጋር ድንበርን አስመልክቶ ስላለው ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይደበቀው ሊያውቀው የሚገባው ጉዳይ ነው። ስለ አገር ማወቅ መብት እንጂ ስጦታ ወይም ችሮታ አይደለም። አገርን በሚመለከት ጥቂቶች ባሻቸውና ለነርሱ የሥልጣን ዕድሜ ሲባል በተመቻቸው መልክ የሚስተካከልና የሚሸራረፍ የሚጨመርና የሚቀነስ ሲሆን አይገባም። ዜጎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል ናቸው የሚለው ሕገ መንግስታዊ አንቀፅ የሚረጋገጠው እያንዳንዱ ዜጋ በአገሩ ላይ እኩል ድርሻ ሲኖረው ብቻ ነው።

በጦርነት በበሽታ በረሃብ የሚረገፈው ድሃው ሕዝብ ነው። ይህ አገሬ ብሎ ደሙን የሚያፈስስና የግዛት ሉአላዊነት ተረጋግጦ እንዲኖር የሚያደርግ ዜጋ ጦርነቱ፣በሽታውና ረሃቡ ከቶውንም በማይነካቸው ገዥዎቹ ፍላጎትና እምቢተኛነት አገሩን በሚመለከት ወሳኝ እንዳይሆን ሲደረግ ነበር። አሁንም ቢሆን ይህ አለ። በርግጥ እምባገነንና ጨቋኝ ገዥዎች የሚያውቁትና የሚገነዘቡት የራሳቸውን እምነትና ቋንቋ ብቻ ቢሆንም አልፎ አልፎ ግትር አቋማቸው እያባነን የሚያንቃቸውና የሚያስጠነቅቃቸው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መከሰቱ አየቀርም።

የግዛት ሉአላዊነት ተከብሮ ተረጋግጦና ፀንቶ የሚኖረው ድንበርተኛ በሆኑ አገሮች መካከል በሚደረስ አለም አቀፍ ተቀባይነት በሚያገኝ ስምምነት ነው። ይህ ስምምነት በተለያዩ ታሪካዊ ፖለቲካዊና ምናልባትም ወታደራዊ ሰበቦች ሊስተካከል ይችል ይሆናል። ይህም ቢሆን የሁለቱም አገር ሕዝቦች በመሬታቸው ላይ የመወሰን የዜግነት መብታቸው ሳይዘነጋ ነው። ምክንያቱም ወደፊት ሊያጋጥም የሚችለውን ማንኛውንም ዓይነት ችግር መቅረፍ የሚቻለው በነዚሁ በሚመለከታቸው ዜጎች ተሣትፎ ስለሚሆን ነው።

ዜጎችን ያላሣተፈ የድንበር ስምምነት ለሰላም መታጣትና ለጦርነት መቀስቀስ ያስጥርጥር ሰበብ ይሆናል። በድንበር አካባቢ የሚኖረውን ሕዝብ የዜግነት መብትም የመወሰን ኃይል ያለው





## ሥም ከመቃብር በላይ

የአካባቢው ነዋሪ እንጂ የፖለቲካ ሥልጣን የያዘው ገዥ መደብ ሲሆን አይገባም። ስለዚህ የወሰን መስመሮችን እንደገና በማስተካከል ጊዜ የተወሰነ የሕዝብ ክፍል ያለ ፍላጎቱና ያለ ጥያቄው የሌላ አገር ዜጋ እንዲሆን ቢወሰንበት ማን በዜግነት መብቱ ላይ ሊወስን ይችላል የሚል እመፅ ይጀምራል። ይህ እንግዲህ በግድ ተገዛ የሚልና በግድ አልገዛም የሚል የማይታረቅ ቅራኔ ያስከትላል።

ይህ አነስተኛ ርዕስ የታሪክ ተመራማሪዎችንና የፖለቲካ ጠበብቶችን ስሜት ኮርኩሮ ሠፊ ጥናት እንዲጀመርበት መነሻ እንዲሆንና እኔ በሕይወት አጋጣሚ ያወቅኋቸውን እውነታዎች በመግለፅ ምን ያህል ትክክል እንደሆኑ እንዲረጋገጥ በማሰብ ነው። በመሆኑም በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር በተለይም በጎንደር ክፍለ ሃገር በሁመራ መስመር ያለውን ለማሣየት እሞክራለሁ።

የኢትዮጵያ ሕልውና ከታወቀበት ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ጀምሮ የውጭ ጠላቶች ጦር ሰብቀው ሠራዊት አሰልፈው ነጋሪት ጉስመው በተደጋጋሚ የመጡብን በዚሁ በሰሜናዊ ምዕራብ የወሰን በራችን ነበር። ግብፆችና መሃዲስቶች ያከናወኗቸው መከራዎች በቂ ማስረጃዎች ናቸው። በርግጥ በቀይ ባህር በኩልም መከራና እልሮ ተርፎ ግዛት ያተነጠቅንበት ታሪክ ቢኖርም ነገሥታት «ከተት ሰራዊት» በማለት የዘመቱበት ይህኛው መሥመር ይበልጥ ይወሳስታ ። አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዮሐንስ ሕይወታቸውን ያጡባቸው ጦርነቶች በዚሁ መስመር በመጡ ጠላቶች ነው። የነገሥታቱን መስዋዕትነት ስንዘክር አብርቸው የዘመተው የትግራይ፣የጎንደር፣የጎጃም፣የወሎና የሸዋ ሕዝብ አፅሙ የተከሰከሰበት ደሙ የፈሰሰበት ቦታ መሆኑም የማይዘነጋ ነው።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከአምስቱ ዓመት የኢጣሊያ ፋሽስት ወረራና ጦርነት በኋላ ከስደት የተመለሱትም በዚሁ በር ተጉዘው ነበር። የውጭ አገራት አማፆች ጉብኝዎችና አጥኚዎች ይገቡና ይወጡ የነበረውም በዚ በር ነበር። ኢትዮጵያውያንም ወደ ግብፅና እየሩሣሌም በኋላም ወደ አውሮፓ ሲመላለሱ የነበረው ይህን መስመር ተከትለው ነበር። እነዚህን በዝርዝር ያልተፈተሹ የመንደርደሪያ ነጥቦች የጠቀስኩት ይህ በር ምን ያህል ተፈላጊነት እንዳለው አመላካች ይሆናል በሚል ነው።

<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

ከ1964 ዓ.ም እንደ ከውሮፓውያን አቆጣጠር ወይም ከ1971ዓ.ም በፊት የነበረውን ሁኔታ ታሪክ ተመራማሪዎች ሲፈትሹት ብዙ የሚገለፅ ጉዳይ ይኖር ይሆናል። አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ በተነሱበት ጊዜ ከውስጥ የተነሱባቸው መሳፍንትና ትናንሽ ነገስታት ይህን ዓላማቸውን ሲቻላቸው በፊት ለፊት ውጊያ ሲጨንቃቸው በሽፍትነት እያመፁባቸው የተረጋጋ መንግስት እንዳይመሰርቱ አድርገዋቸው ነበር። ይህ ሁሉ አልበቃ ያላቸው መሣፍንትና ስሙ-ነገስታት በመጨረሻው አስተባብረው ያመጡት የእንግሊዛውያን ጦር ወደ መሀል አገር መግባት የቻለው በዚሁ በር ነበር። ቴዎድሮስ እጅ ሰጥተው መማረክ ወይም በሽሽትና በስደት መሞት ታሪካቸውን እንደሚያጉድፈው ወታደሮቻቸውንም እንደሚያሸማቅቅ ስላወቁ ራሳቸውን ሰውተው አለፉ።

አፄ ዮሐንስ የሩቅ ዓላማቸው የኢትዮጵያ አንድነት ነበርና ቴዎድሮስን ሲያስቸግሩ የነበሩትን መሣፍንትንና ትናንሽ ነገስታትን በኋላ በሚደረግ ውጊያም ሆነ ዲፕሎማሲያዊ ዘዴ እንደሚያሸንፉ በማወቅ ቅድሚያ የሰጡት በሰሜን ምዕራብ በኩል ይቃጣባቸው የነበረውን የደርቡሾች ትንኮሳ ማክሸፍ ነበር። የጉንደር የጉሽም የወሎና የሸዋ መሣፍንት እብጠትና ከፋፋይነት የቤት ውስጥ ጉዳይ መሆኑን በማመን የደርቡሾች ጉዳይ ግን ይዋል ይደር የማይባል ፍፁም የባዕድ ሀይል መሆኑን በመረዳት ያደረጉት ዘመቻ ነበር። ዮሐንስ እንዳሰቡት ደርቡሾችን አሸንፈው በሕይወት ወደ ዙፋናቸው አልተመለሱም። ይህን ታሪክ የተረከቡት አፄ ምኒልክም በዘመናቸው ከእንግሊዞች ጋር ባደረጓቸው የተለያዩ ውሉችና ስምምነቶች ይህ እየጠቀስኩት ያለው የወሰን ድንበር ተከብሮ ኖሯል።

በልጅ እያሱ አጭር የአገዛዝ ዘመንም ይሁን በንግስት ንገሥታት ዘውዲቱ ጊዜ በዚሁ ድንበር በኩል የሚጠቀስ ችግር ሳይደርስ ዙፋኑ በአልጋ ወራሹ በተፈሪ መኩንን እጅ ገባ። ተፈሪ መኩንን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ከተባሉ በኋላ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ጥያቄ የሚያስነሣ ነው።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ይህን የሰሜን ምዕራብ የድንበር ሁኔታ በነበራቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ከታሪካዊ መነሻው እስከራሳቸው ዘመን የነበረውንና ያለውን መረጃ በውል መገንዘብ





<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

ይገባቸው ነበር። ስነዎድሮስ በውጭ ወራሪዎች መዉጋትና መውደቅ ለዮሐንስ መስዋዕትነ ሰበብ የሆነው ይህ መስመር ታሪኩ ተጠብቆና መስመሩም ተከብሮ መኖር ሲገባው ይ የዘነጉት የሚመስል ተግባር በዘመናቸው ተፈፅሞ ነበር። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ይህን ሕያ ታሪክ በመርሣት የኢትዮጵያ አካል ከሆነው መሬት ላይ ከፍለውና ቆርሰው ለሱዳን በችሮ ለመስጠት በድፍረት ተነስተው ነበር በዚሁ ጉዳይ ላይ ለመደራደር የሱዳን ፕሬዝዳን የነበሩት ጀነራል ኑሜሪ አዲስ አበባ መጥተው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሽልማት ድርጅት እንዲገኙ በማድረግ ከሽላሚው ንጉሥና ከተሸላሚዎች ጋር በ1964 ዓ.ም ፎቶግራፍ ተነስተ ታሪካዊ መረጃ እንዲሆን አድርገዋል።



*የኢትዮጵያና የሱዳን መሪዎች በድንበር ጉዳይ ላይ ከተወያዩ በኋላ*

## ሥም ከመቃብር በላይ

የኢትዮጵያ መተማና ሁመራ አካባቢዎች እስከ ሱዳን ድንበር ድረስ እጅግ ሠፊ የሆኑ ሜዳማ አገሮች ናቸው። መሬቶቹ ከባህር ወለል በላይ እጅግም ከፍ ስለማይሉ የአየር ጠባያቸው እጅግ ሞቃታማ ነው። በተለምዶ አገላለፅ በረሀማ ናቸው። ነገር ግን የኢትዮጵያ መተማና ሁመራ የተለዩ በረሀዎች ናቸው። መሬቶቹ በሙሉ ለእርሻ የሚያመቹ ናቸው። በሁመራ ወረዳ ውስጥ አቋርጦ ወደ ሱዳን የሚፈሰው ብቸኛው ጅረት የተከዜ ወንዝ ነው።

የመተማና የሁመራ መሬቶች እጅግ የሚደነቁት በሰሊጥ ምርት ነው። የአካባቢው ገበሬዎች ከዚህ ምርት ጠቀም ያለ ገንዘብ ስለሚያገኙ ሀብታሞች ናቸው። ጥጥ፣ ማሽላና በቆሎም በብዛት ይመረታል። የዕጣን ምርቱም ለውጭ ገበያ እስከመቅረብ የደረሰ ክምችት አለው። ነዋሪው ሕዝብ ባህሉ ሆኖ ዘመናዊና ጥንታዊ መሣሪያዎችን በየዓይነቱ የታጠቀ ነው። ሲያኮርፍ ለመንግስት የማይገዛና የማይገብር ሕዝብ ይሆናል። ነገር ግን ኢትዮጵያ የሚለው የአገር፣ የዜግነት የርሱነት መገለጫውና መለያው ኩራቱና ክብሩ ነው።

የተከዜ ወንዝ የኢትዮጵያና የሱዳን የተፈጥሮ ወሰን አካላይ ሆኖ ረዥም ርቀት ይጓዛል። ከተከዜ በስተምዕራብ ያለው የሱዳን ግዛት መሬት በኢትዮጵያ ካለው የሁመራና የመተማ መሬቶች ጋር በለምነት ሲነፃፀር ፍፁም ተቃራኒ ነው። የሱዳን ግዛት መሬት እፍኝ የሚሞላ ምርት አይሰጥም። ደረቅና አሸዋማ ነው። ሱዳናውያን ለከብቶቻቸው የሚሆን በቂ ግጦሽ ሳር የላቸውም። የቤት መሥሪያ እንጨት ስለሌላቸው ቤቶቻቸው ከጭቃና ከአፈር የሚገነቡ ናቸው።

ሱዳናውያን መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት በማያስችላቸው መሬታቸው ላይ የማያገኙትን ጠቃሚ ነገር ሁሉ ከኢትዮጵያ ለማግኘት ያልተቋረጠ ጥረት ያደርጋሉ። በግዛታቸው ውስጥ የሌለውን እንጨት ድንበር ጥሰው በጉልበት በመጠቀም ቆርጠው ይወስዳሉ። በሰፈው መሬታቸው ውስጥ የማያገኙትን የእጣን ምርትም በመሣሪያ ተማምነው ለቅመው ይጭናሉ። በኃይል እጠቃቀም የሚታጀበውን ዘረፋቸውን ለበቀል ኢትዮጵያውያን የአካባቢው ነዋሪዎችም በተመሣሣይ ሁኔታ ወሰን ተሻግረው ከብት ዘርፈው ይመለሳሉ።





## ሥም ከመቃብር በላይ

በሁለቱ ድንበረተኞች መካከል የሚከሰተው የዜጎች ፀብ እየተባባሰ በመሄዱ የየአገሮቹ ባለሥልጣናት ግንኙነት በማድረግ ሁመራንና መተማን ለሱዳኖች ለመስጠት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴና በጀኔራል አልኑሜሪ መካከል የውሣኔ ስምምነት ላይ ይደረሣል። የዚህ ስምምነት ምስጢር ለጎንደር ሕዝብ ሲደርሰው የእርማጭሆ፣ የወልቃይት ጠገዴ ዙሪያ፣ የሁመራና የመተማ ነዋሪዎችን ቁጣ ይቀሰቅሣል። ሕዝቡ መሬቱንና እርስቱን ለታሪካዊ ባላንጣው አሣልፎ የሚሰጠውን ውሣኔ ከሰማ በኋላ አልገዛም በሚል መነቃነቅ ይጀምራል። ሱዳናውያን በሀይል ሊየገኙት ያልቻሉትን አገር በሰላም ሊረከቡ ሲዘጋጁ መመልከት ባለመቻሉ ወሰን እየተሻገረ ግድያ ይጀምራል። የሱዳን መንግስትም የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ስምምነቱን ወደተግባር እንዲለውጡና ሕዝቡንም እንዲያስታግሱ መጎትጎታቸውን ይቀጥላሉ። ስምምነቱ በፊርማ እስኪፀድቅ ድረስም ሕዝቡም መሬቱም የነርሱ ስላይደለ ዲፕሎማሲያዊ ጥረታቸውን ያጣድፋሉ።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት ሕዝቡን በሠላማዊ ዘዴ ከማስረዳትና ስምምነቱም እንዲተገበር ከማድረግ ይልቅ በጦር ሀይል ተጠቅሞ ዜጎቹን ማንበርከክና አሣልፎ መስጠት እንደሚሻለው በማመን ይህን አማራጭ ተጠቀመ። በዚሁ መሠረት በብ/ጄኔራል ይማም ጎሹ የበላይነት የሚመራ አንድ ወታደራዊ ኮሚቴ ተቋቋመ። በተሰጠው ትዕዛዝም ብ/ጄ ይማም ጎሹ በደንብ የታጠቀ አንድ የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ጦር ይዘው ሁመራ ይደርሣሉ። የሚመሩትን ዘመናዊ ወታደር በመተማመን ከሕዝቡም ጋር አንዳች ምክክር ሳያደርጉ፣ የተከሰተውንም የድንበር ላይ ግጭት ሣያበርዱ የየአገሮቹ መሪዎች የወሰኑትን ለመተግበር ሙከራ ያደርጋሉ።

ለሱዳን በሽልማት ወይም በገፀ በረከትነት ሊሰጥ ያለማቅማማት የተወሰነበት ኢትዮጵያዊ መሬት ሁመራ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ነበር። የሁመራ አካባቢ ቃላት በበቂ ሁኔታ ሊገልፁት የማይችሉት እጅግ ሞቃታማ በረሀ ነገር ግን እጅግ ሰበፃ ደግሞ ለም የሆነ አገር ነው። ሁመራ በተለይ ለሰሊጥ ምርት ተስማሚነቱን ለተገነዘበ ሁሉ ቦታው የሚያጓጓና የኔ በሆነ የሚያሰኝ ነው። ሁመራ በሰብልና በመኸር ወቅቶች ለሚጎበኘው ሰው አካባቢው የሀብት

<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

እጅግ በሰፋት የተንጣለለው ሜዳ ትራክተሮች ያለ አንዳች ሳንካ የሚፈነጩበት የመስኖ ውሃ በተፈጥሮ የሰበት ሕግ እንደልብ የሚንደረደርበት አቅምና ጉልበት እስንለ ድረስ ያለማቅማማት ከረሀብና ከድህነት ኢትዮጵያን ለማዳን የሚችል የምርት መጠን ሊታፈስበት የሚችል ነው።

የውጭ ጠላቶችና አጎራባች አገሮች ለዚህ የተለየ ቦታ የሚነገበገቡትም በዚህ የልማት ቦታነቱ ርግጠኛነት ስላላቸው ነው። የመተማን ልማት ሰበብ በማድረግ የሁመራንና የአካቢውን ልማት የመግቢያ ቀዳዳ በማድረግ የፕሬዚዳንት ኑሜሪና የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስምምነት ምስጢር ይታወቃል። ይህ ስምምነት የአያቶቻቸውና የአባቶቻቸው ደም የፈሰሰበት፣ እጥንት የተከሰከሰበት ኢትዮጵያውያንን ከዚያ በፊት ንጉሥ ነገስቱ ሪፖርት ተደርጎላቸው የማያውቅ አስፈሪ ሕገባዊ ቁጣቸውን መቀስቀሱን ይሰማሉ። ኢትዮጵያውያን ዜጎች የአገራቸውን መንግስት ክህደት በመገንዘብ ለተደረገው ሕገ-መንግስትን የጣሰና የኢትዮጵዊነት መብታቸውን የደፈረ ስምምነት ላለመገዛት ለጦርነት ዝግጅት ይጀምራሉ። ከዚህ አስቀድሞ ግን በድንበር አካባቢ በተለምዶ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ሁሉ ይገታሉ።
ከዚህ አስቀድሞ ግን በድንበር አካባቢ በተለምዶ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ሁሉ ይገታሉ። የሁመራና የመተማ አካባቢን ሕዝብ መራራ ቁጣ የሰሙት ንጉሥ ነገስት በጊዜው ለአገር ግዛት ሚኒስትሩና ለፖሊስ አዛዡ ትዕዛዝ ይሰጣሉ። በዚህ ትዕዛዝ መሠረት አንድ የፈጥኖ ደራሽ ኃይል በአስቸኳይ ወደአካባቢው እንዲላክ ያደርጋሉ። የፈጥኖ ደራሹን ኃይልና በኋላም የኮሚቴ አባላት የሉብትን ቡድን ከአካባቢው ኢትዮጵውያን ዜጎች ጋር ውይይት የሚያደርግ በመምራት ብ/ጀኔራል ይማም ጉሹ ይላኩና ሁመራ ይገባሉ።

የፈጥኖ ደራሹ ኃይል በተቆጣው ሕዝብ ጉያ ስር ፋይዳ የሌለው መሆኑን አዛዡ ይገነዘባሉ። በጊዜው የተዋጣለት ብ/ጀኔራል ይማም ጎሹ የሚመራው ጦር በዘመናዊ ትጥቅና ሥልጠና ነበር። ቢሆንም የአካባቢውን ባህል ጨርሶ የማያውቅ ስለሆነ በምን ዓይነት ሕዝብ መሀል እንደሚገኝ አልተረዳም። ወታደሩ ሲታዘዝ ወደ ግዳጁ ከመንቀሳቀሱ በስተቀር የሁመራና የመተማ ሕዝቦች እቤቱታና ቅሬታም ምን እንደነበረ አያውቅም። መሪዎቹ የአለም አቀፉን ሕግና የአገሪቱንም ሕገ-መንግስት ጥሰው የሚፈፅሙትን አያውቅም። በሕገ-መንግስቱ ላይ የተካፈውን ሁሉ «. . . በፈቃዳችን የሰጠነው . . . » የሚለውን ሐረግ «. . . በፈቃዳችን የምንነካው . . .» የሚል ተዛምዶ እንዳለው በማሰብ ሕጉን ሲያፈርሱት ሕዝቡ ይቀበለዋል ብለው መገመት አልነበረባቸውም።





<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

የጎንደር ሕዝብ በተለይም በወሰን አካባቢ የሚገኘው የወልቃይት ጠገዴ፣ የአርማጭሆ፣ የመተማና የሁመራ ነዋሪ ታሪክ ማጠቀስ ይጀምራል። «ሱዳናውያን አገራችንን ወረው ከአፄ ቴዎድሮስና ከአፄ ዮሐንስ ጋር ተዋግተዋል። ብዙ ሺህ አያቶቻችን በጀግንነት ተዋግተው ይህን ድንበር አስከብረው አስረክበውልናል። አፄ ዮሐንስ በድንበር ማስከበሩ ላይ ሲዋጉ መስዋዕት ሆነዋል። አሁን የታሰበው ውሣኔ የዚህን ሁሉ ታሪክ መካድ ነው። ይህ ወንጀል ነው። ማንም በኃይል እንድንቀበለው ማድረግ አይችልም።» ማለት ይጀምራል። ነዋሪው ሕዝብ የፈጥኖ ደራሹን ጦር እንደልብ ማግኘት ባለመቻሉ ቅሬታውን እየገለፀ የተቃውሞ ወረቀት መበተን ይጀምራል።

ብ/ጀኔራል ይማም ጎሹ እየመሩት የወሰዱት የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ጦር የታሰበውን ግዳጅ ሊወጣ የማይችል መሆኑን ውለው አድረው ተገነዘቡ። ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ለአለቆቻቸው ሪፖርታቸውን በማቅረብ ድጋሚ መመሪያ ይቀበላሉ። በሱዳን ወሰን አጠገብ የሚኖረው የጎንደር ሕዝብ የጀመረው የአመፅ እንቅስቃሴ ለብ/ጀኔራል ይማም ጎሹ ችግር አልነበረም። ይልቁንም ይህን በሞቃታማና በረሀማነቱ የሚነገርለትን የሰሜናዊ ምዕራብ መሬት ሲመለከቱት የርሣቸውም ልብ ሸፈተ። ገደብ የሌለው የሰሊጥ፣ የጥጥ፣ የማሽላና የበቆሎ ሰብል ሊያሣፍሳቸው የሚችለው ለም ድንግል መሬት አጓጓቸው። የሕዝቡ ቁጣ መልካም መከታ እንደሚሆናቸው አመኑ። ክጠቅላይ አዛዡ ከሌ/ጀኔራል ድረሴ ዱባለ ጋር በመነጋገር ለሱዳኖች የታሰበውን መሬት እርሣቸው ወስደው በፖሊስ ሠራዊት ስም ለማልማት ተነሱ። ለእርሻ የሚያገለግሉ ትራክተሮችን፣ የመጓጓዣ መኪናዎችንና በዚህም ዓ ይነት በሰሜንም በመሀል አገርም የሚገኙ የወታደራዊ አዛገሮችና ሲቪል ባለሥልጣናት ወደ ሁመራ ጠቅለው ለመግባትና በእርሻ ሥራ ላይ ለመሠማራት ሲዘጋጁ በ1966
ዓ.ም. የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ አመፅ አሽማቀቃቸው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ቦታ ሱመለከቱ ለምን ለባዕድ ይሰጣል እኛስ ሌላው ቀርቶ በግል አቅም እንኳ ልናለማው እንችል የለምን በሚል አመለካከት ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ለላኳቸው ባለስልጣኖች ያስረዳሉ። የብ/ጀኔራል ይማም ጎሹ አቀራረብ ለዘመኑ ሥልጣናቸው

<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

መራዘምና ከልማቱ የሚገኘው ፈሰስም ያጓጓቸው ንጉሥ ነገስትና ባለሟሎቻቸው ሌላ መራራ ጣጣ ውስጥ በመግባት አስቸጋሪ ሁኔታ እንዳይገጥማቸው ሀታቡን ይቀበላሉ። የሕዝቡን ቁጣ ለማብረድና እስተሣሰቡንም ለመቀየር ሲባል አንድ የፖሊስ የልማት ቡድን የእርሻ ሥራ እንዲጀምር ይባላል። ለዚህም የሚያስፈልገው የገንዘብና የትራንስፖርት በጀት ይመደባል። ብ/ጄኔራል ይማም ጎሹም ከግላቸው ገንዘብ ማያወጡ በፖሊስ ሠራዊት የልማት ቡድን ሥም ሥራውን ይቀጥላሉ።

የመተማመንና የሁመራን አካባቢዎች ለሱዳን አሣልፎ ለመስጠት የነበረውን ድርድርና ስምምነት አጥብቀው እንደሚቃወሙ ይጠረጠሩ የነበሩት የቤጌምድርና ስሜን አጠቃላይ ግዛት ፖሊስ አዛዥ ብ/ጄኔራል ሥዩም ገሠሠና አበሪዎቻቸው ናቸው የተባሉት ሁሉ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ይደረጋል። በመንግስት ሥራና ኃላፊነት ላይ ተቀምጠው የመንግስትን ነውረኛ አካሄድ የማይቀበሉ ሁሉ ከአካባቢው ተነስተው ምንም ስለሁኔታው የማያውቁ ወይም ቢያውቁም ተባባሪ ይሆናል ተብለው በሚታመንባቸው የፖሊስ አዛዦችና ሠራተኞች የሥራ መደቦች ይሞላሉ። የአካባቢውን ኢትዮጵያውያን እመለካከት የሚደግፉ በጎንደር ወስጥ የሚሰሩ የፖሊስ መኰንኖችና ወታደሮች ሣይቀሩ እንዲዛወሩ ተደረገ። ብ/ጄኔራል ሥዩም ገሰሰ ከጠቅላይ ግዛቱ ፖሊስ እዛዥነታቸው ተነስተው በምትካቸው ለአካባቢው አዲስ የሆኑ ኰሎኔል ተሾሙ። ይህ ሹመት በራሱ የጠቅላይ ግዛቱን የፖሊስ አዛዥ የማዕረግ ደረጃ ያልጠበቀና ለግል ጥቅም ሲባል የተፈፀመ ሴራ እንደነበረ ያስረዳል።

ይህ የሽግግር ወቅት ሁኔታ ከመጠናከሩና ከመጎልበቱ በፊት ለነብ/ጄኔራል ይማም ጎሹ ያገለግላል የተባለ አንድ የፖሊስ ሻምበል የሆነ መኰንን ጎንደር ከተማ ውስጥ በጥይት ይገደላል። ይህን ግድያ ያከናወነው "ደም ለመመለስ በራሱ የሚንቀሣቀስ ሰው" መሆኑም በስፋት ይወራል። ይሁን እንጂ ብ/ጄ ይማም ጎሹ እንደተመኙት የአካባቢው ፀጥታ በፈጥና ደራሹ የፖሊስ ጦር እየተጠበቀ እርሻውን እንዲቀጥል አደረጉ። ላይ ላዩን በሚታየው ሰላማዊ ሁኔታ በውስጥ የተረገዘው ቁጣና እልህ ጎልቶ አልወጣም። ንጉሥ ነገስቱና መንግስታቸው ከሱዳን አመራር ጋር አደረጉት በተባለው ስምምነት ሳቢያ ለፀጥታ ማስከበር ሲባል ከተላኩት የፈጥኖ ደራሽ አባላት መካከል ጥቂት የማይባሉ ባመፁ ዜጎች ተገደሉ። ኢትዮጵያውያን ቁጣቸው በማየሉ ወሰን እየተሻገሩ ሱዳናውያንን መግደላቸውን ቀጠሉበት ውሉ እድሮ ግን





<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

አጠቃላይ ሁኔታውን የተረዱ ፖሊሶች በሌ/ጄኔራል ድረሴ ዱባለና በብ/ጄኔራል ይማም ጎሹ ላይ የተቃውሞ ወረቀት መበተን ጀመሩ።

ለአገር ሉአላዊነት ሳይሆን ከልማቱ የሚገኘው ገቢ ያጓጓቸው ባለስልጣናት አካባቢውን በኢትዮጵያ መንግስት ግዛትነት ሥር እንዲቆይ ሰበብ ይሆናሉ። የልማቱ ተግባርና ወጤቱም ብዙ ኢትዮጵያውያን ባለስልጣናትን የሚማርክና የሚስብ ይሆናል። መሬትን ቆርሶ ለመስጠት የተወጠነው ሴራ ሲከሽፍ ባለሥልጣናቱ በልማት ስም የተጧጧፈ ዘረፋ ውስጥ ገቡ። ይህ ስግብግብነት የተረዱትን ተቃዋሚዎች ለመበቀል የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ፣ ብ/ጄኔራል ይማም ጎሹን የፍርድ አጣሪ ኰሚቴ ሊቀመንበር አድርገው ሌሎች ተባባሪ ጀኔራሎችንና ኰሎኔሎችንም በአባልነት መደቡ። በዚህ መሠረት ብዙ ወጣት መኰንኖችና ወታደሮች እየተወነጀሉ ታሠሩ ወይም አገልግሎታቸው ሣይታይ ወደ ገጠርና ወደ በረሀ እንዲዛወሩ ተደረጉ። አስፈሳጊ ቁሣቁሶችን ለማሟላት በፀጥታ ማስከበሩ ስም ብዙ መቶ ሺህ ብር በጀት በማስፈቀድ ሥራ መጀመር ፈለጉ ከነዚህ መካከል የደርግ ወታደራዊ መንግስት የደህንነት ኰሚቴ ሊቀመንበረ የነበሩት ኰ/ል ተካ ቱሉ የተባሉት አንዱ ሰለባ ነበሩ። ይህ ለአብነት የቀረበ መረጃ እንጂ ሌሎች ብዙ መኰንኖችና ፖሊሶችም ነበሩ።

ብ/ጄኔራል ይማም ጎሹ ከአዲስ አበባ ወደ ሁመራ እየተመላለሱ መሥራት ከበዳቸው። የተጀመረው እርሻም በተቃውሞውና በአባላቱም አውቆ መለገም እንደታሠበው ሊቀጥል አልቻለም። ባለሥልጣኖች የጎነጎኑት ሴራ በሕዝቡ የተባበረ ጥረትና ኃይል፣ ሱዳኖች ሁመራንና መተማን የመውሰድ ተስፋቸው ሣይሣካላቸው ቀረ። አካባቢውን በስምምነት አሣልፎ ለመስጠት ወግኑ ላይ የደረሰውም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት በ1966 ዓ.ም. በተቀጣጠለው ሕዝባዊና ወታደራዊ ንቅናቄ ከመንበረ ስልጣኑ ተባረረ። የሁመራ፣ የመተማና ዙሪያ ገባውን ያለው የጠረፍ ነዋሪ ሕዝብም ኢትዮጵያዊ ዜግነቱ ቀጠለ።

በዚህ አጭር ታሪክ ውስጥ አገርን አሳልፎ ለመስጠት ሴራ የሚሻረበው በቤተመንግስት ሊነሣ መቻሉን፣ የሕዝብን የዜግነትና የንብረት መብት ለመወሰን የፖለቲካ መሪዎች አስነዋሪ ተግባራትን መፈፀማቸውን ሕዝብ ምን ጊዜም የማይደፈር ኃያልነቱን በማረጋገጥ የመንግስትን ውሳኔ ሊያሽርና ሊያስቀለብስ መቻሉን፣ በአገርና በወገን የሉአላዊነትና የአንድነት

## ሥም ከመቃብር በላይ

ስም የግል ብልፅግና ተልዕኮን እንዴት እንደሚያሰናክል፣ የተለያዩ አጋጣሚዎች ፀንቶ የኖረውን የግዛት መስመርም እንደተጠበቀ እንዲዘልቅ ማድረጋቸውን ለማመላከት ተሞክሯል። የተጠቀሰው ታሪክና የተሰጠውም ሀተታ በቂ ላይሆን ይችላል። ቁምነገሩ ታሪኩ እንዳይዘነጋና ተድበስብሶ እንዳይቀር ማድረግ መቻሉ ነው። ዛሬስ ሁመራን፣ መተማን፣ አሜድላን፣ ጋምቤላን በተመለከተ ከሱዳን ጋር ምንም አይነት የመሬት መስጠትና መቀበል ድርድሮች የሉም ይሆን? የአማራ ክልል፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ የጋምቤላ ክልል የፖለቲካ መሪዎችና ኢትዮጵያውያን ዜጎች አይንና ናጫ የሚሆኑባቸው ስምምነቶች የሉም ይሆን ለማንኛውም እኔ መነሻውን አስጨብጫለሁ። ዝርዝሩን ሥራ እንዲቀጥሉበት ለተመራማሪዎች በአደራ አስተላልፋለሁ።





## ምዕራፍ 3

## ደርግና ጻር ደንበር

አጤ ኃይለ ሥላሴ ለስልጣን ሲሉ ብዙ ሰዎች እንደገደሉ ሁሉ ሀገራቸውን ለማበልጸግ መልፋታቸው መካድ የለበትም:: እኔ የትውልድ ሀገሬን ታሪክ በተመለከተ ብዛት ያላቸው ደራሲያን የጻፏቸውን መጽሐፍት ተመልክቻለሁ:: የኢትዮጵያ ደራሲያኑ የሚያንጸባርቁት ስፈርተኛ መሆናቸው ነው:: ይህን አሊ የሚል ካለ ዛሬም እውነቱን አልተረዳም ማለት ነው:: አንድ ደራሲ በብዛት ምሳሌ የሚጠቀመውና የሚደጋግመው ባደገበት አካባቢ መሆኑ ባልከፋ እኔም እጠቀማለሁ:: ነገር ግን አንዱን ግለሰብ ሲረዳው ኑሮ አንድ ቀን አልችልም ቢለው ቀደም ሲል የተረዳውን በመርሳት ሲቀየምና የሚያውቀውን ታሪክ ሲክድ ይታያል:: አብረው በአንድ ጉዳይ ላይ ሲሰሩ ኑረው በሌላው ጉዳይ ላይ ሳይግባቡ ቢቀሩ ከዚያ በፊት የነበራቸውን ግንኙነት ሲያጠፉት ይታያሉ:: ይህ በኛው ደረጃ ባሉት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ማዕረግ ደርሰው በነበሩ ሰዎች ሁሉ የሚፈጸም ጉዳይ መሆኑን በተለያየ ወቅት የተጻፉትን ታሪክ ማመሳከር ይቻላል::

ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ፍጹም ናቸው የሚሉ ደራሲያን በሁለት አይናቸው የማያዩ ናቸው:: ቅድሚያ አጤ ኃይለ ሥላሴ ቅዱስ ናቸው ከማለት በፊት በሌሎች ክፍለ ሀገር የተደረገውን ሻጥር ማወቅ ይጠይቃል:: አሁን ችግር የገባነው በአንዳይና አስተያየት የሚያዩ ደራሲያን አጤው ቅዱስ ናቸው ሲሉ ሌሎች ጥሩውንና መጥፎውን የሚያዩትን ዜጎች መጥፎውን ብቻ እንዲያዩ እያደረጉ መሆናቸውን ተገንዝቤአለሁ:: ስለዚህ አጤ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ታላቅ ሥራ የሰሩ ሊከበሩ የሚገባቸው አባት ሲሆኑ አጤ ኃይለ ሥላሴ ያጠፉትም ጥፋት እንዳለ መታወቅ አለበት:: ይህ መጽሐፍ የእርሳቸውን ጠንካራ ጎንና ደካማ ጎን ለመጠቆም የተዘጋጀ ሳይሆን በእርሳቸው እየተመካኘ ብዙ ዜጎች የተበደሉ መኖራቸውን ለመግለጽም ነው:: የእርሳቸውን ደካማ ጎን ባንድ ክፍል ጠንካራ ጎናቸውን ባንድ ክፍል በታሪክ አስደግፎ ለመጻፍ የሚቻል ይመስለኛል:: እግዚአብሔር ይመስገን የሠነድ ችግር ያለብኝ አይመስለኝም የግዜ እጦት የገንዘብ ችግር እንጂ ይህን ልለፈው ለወደፊቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ልንመለስበት እንችል ይሆናል::

ርዕሠ ብሔር አማን አንዶም ከመስከረም 2 ቀን 1967 ዓም እስከ ሕዳር 14 ቀን 1967 ዓም ኢትዮጵያን በርዕሠ ብሔር ናቸው:: እርሳቸውን ወደ ሥልጣን ያመጣቸው ደርግ 120 አባላት ያላቸው ወታደራዊ ቡድኖች ሲሆኑ ከስብሰባቸው መካከል ከእነሱ በላይ የሆነ ባለስልጣን በእርሰ ብሔርነት እንዲመረጥ ብቁ ሰው ፈልጉ ሲባል ስማቸውን ለደርጉ ያቀረቡ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ናቸው:: ጀኔራል አማን ቢሆኑም ጥሪውን በጸጋ ተቀብለዋል:: ነገር ግን እርሳቸው የአገር አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ

አልፈለጉም። ዛሬ አንዳንድ ሰዎች ጄኔራሉ ስህተት የለባቸውም ደርጉ ለመግደል ስለፈለገ እንጂ የሚባለው ከእውነት የራቀ መሆኑን የሚያብራሩ ብዙ ሠነዶች ማሰባበስ ይቻላል። ሻዕቢያ አስመራ ከተማን ለመያዝ የቀረው ትንሽ ኪሎ ሜትር እንደነበር አይዘነጋም። የሻዕቢያ ብርታት ሊያገኝ የቻለው በእርሳቸው ተጠልሎ ነው። ደርጉ ወታደር ወደ አስመራ ይላክ ሲል ርዕሠ ብሔር አማን አይላክም እያሉ ባለብት ወቅት ሻዕቢያ አስመራን ለመያዝ ተቃረበ። አገር ተደፈረ ምን ይደረግ ሲባሉ እርሳቸው "ሁሉንም ነገር ለእኔ ተውት" ይላሉ። በዚህ ምክንያት ወደ ደርጉ የስብሰባ አዳራሽ ይምጡ ሲባሉ እርሳቸው መሄድ አልፈለጉም። በዚህ ወቅት በሽምግልና አልመጣም ሲሉ ደርጉ ወጊ ጦር ልኮ አስገደላቸው። የርዕሠ ብሔር አማን ታሪክ በአጭር በዚህ ተደመደመ በሥልጣን የቆዩት 72 ቀን ሲሆን ከተራ ወታደር ጄኔራል ማዕረግ ያበቁአቸውን አጤ ኃይለ ሥላሴን አንድም ቀን ከእስር ቤት ሊጠይቋቸው አላሰቡም። አጤው ጅኒናር አማን አይጠይቀንም እያሉ ይናገሩ ነበር።

የሰዩም ጣሰው ማስታወሻ <u>የንጉሡ ገመና</u> በተባለው መጽሐፍ 103 "ጅኒናር አማንን ጥራልኝ እንዴት እርሱ እንኳ አይጎበኘንም ወይ? እባካችሁ ጥሩልኝ ይሉ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል። ርዕሠ ብሔር ተፈሪ ባንቲ! ከኤርትራ ደርጉ ጠርቶ የኢትዮጵያ ርዕሠ ብሔር መርጠነዎታል ብሎ ሾማቸው። እርሳቸው ሹመቱን ተቀብለው የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ ጥረት አድርገዋል። ወቅቱ የሱማሌ ወረራ ጅምር ሲሆን በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ አገራቸውን ዳር ደንበር ለማስከበር ጥረት አድርገዋል። ታዲያ እርሳቸው ዘመናዊ ወታደር ብቻ ሳይሆኑ ዘመናዊ ምሁርም በመሆናቸው የኢሕአፓን አቅዋም ደግፈዋል በመባል በደርጎች በኩል አልተወደዱላቸውም በዚህ ምክንያት ደርጎች ጥር 29 ቀን 1968 ዓም ገደሏቸው። መልካም አገር መሪ የሚወጣቸው እንደሚሆኑ ብዛት ያላቸው አስተያየት ሰጭዎች ይገልጻሉ።

በእርሳቸው የሥልጣን ዘመን አገርን ለመበተን ከውስጥ እስከ ውጭ የታቀደውን ኃይል ለመቋቋም ጥረት ማድረጋቸው አይዘነጋም። በእርሳቸው የመንግሥት ዘመን ዛሬ ያለችው ኢትዮጵያን ለማስከበር ጥረት ሲያደርጉ የጅቡቲን ሁኔታ የኃይል ድጋፍ አስፈላጊ በመሆኑ መውሰድ አለብኝ ብለው ለመጠየቅ ሙከራ አላደረጉም። አንዳንድ የታሪክ ሰዎች "የጅቡቲን ነፃነት መቀበል አልነበረባቸውም። ቢቀበሉም የባህር በር ጉዳይ ለወደፊቱ ኢትዮጵያ የምትጠቀምበትን ሁኔታ ማስተካከል ነበረባቸው" የሚሉ አሉ። ቅኝ ገዥዎች ሱማሌን ሲለቁ ትተውት የሄዱት መርዝ ታላቋ ሱማሌን እንዲያጠናክሩ መክረው ለቀዋል። በዚህ ወቅት በአጤው ዘመን ሱማሌ ልትወር መጥታ ተደብድባ ብትመለስም ደርግ ሥልጣን በያዘ ማግስት ቤተ መንግሥቱ ባዶ መስሏት ከአረብና ከአደጉ አገሮች በተቸረችው የጦር መሳሪያና የገንዘብና ቁሳቁስ ዳብራ ኢትዮጵያን ወረራ ጀመረች። በዚህ ወቅት ወራሪው የሱማሌ መንግሥት የኢትዮጵያ እስላም ምዕመናን እንዳይተባበር ቅስቀሳ ቢያደርግም የእስላም ሃይማኖት ምዕመናን የአገር የማዳን ጥያቄ እንጂ የሃይማኖት ጉዳይ አለመሆኑን አስመሩበት። የእምነት መሪዎች ለየምዕመናናቸው ጥሪ አቀረቡ። ለታሪክ ዋቢ የሚሆን መጽሐፍ አዘጋጁ። ይህን መጽሐፍ የግራ ቀኙን



የሃይማኖት መሪዎች ንግግር ያከተተ ሲሆን የእስላም ሃይማኖትን ወክለው ከተናገሩት ከመሐመድ አወል አሕመድ ንግግር ልጥቀስ።

ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ <u>በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 32 "ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የላቀ አስተሳሰብና ቆራጥ ወኔ የረጋ መንፈስና ኩሩ ሞራል ያለው መሆኑን ያልተከሰተላቸው ወገኖች በጎሳ በቋንቋና በተለይም በሃይማኖት አሳበው በመካከሉ ለማግባትና አንድነቱን ለማፍለስ ሙከራ በማድረግ ላይ ናቸው። ግን አይችሉም። እውነት ቅድመ አብዮት በነበረው የአድልዎ ዘመን ጥቂቶችን ለማሳመን ችለው ይሆናል። ምክንያቱም አማኞችም ቢኖሩ ከአብዮቱ በፊት የነበረው ሁኔታ ሊያሳምነን በቃ ለማለት የሚያስችለው ሲሆን ከአብዮቱ ወዲህ ግን ሁኔታዎች እንደተሻሻሉ በመምጣታቸው ወደፍጹምነት የሚደርሱ የእኩልነት ብርሃን በፍጥነት እየተለወጠ ነው። ጠላቶቻችን የሀገራችንን ሕልውና ለማጥፋት ቢፍጨረጨሩ ከቶ አይችሉም÷ትናንትም እንኳን አልቻሉም ዛሬም አይችሉም ወደፊትም አብዮታዊት ኢትዮጵያ የማትበገር ለመሆንዋ እንደ ቀለበት የከበቧት ጠላቶች እርማቸውን እንዲያወጡ ሰፊው ሕዝብ ትምህርት እየሰጣቸው ሲሆን የዓለም ሕዝብ የዚህን ቆራጥ ሕዝብ የሞት ሽረት ትግል በአድናቆት እየተከታተለ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ሱማሌ የኢትዮጵያን መንግሥት ድል እንድታደርግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ በዚያን ወቅት አብዮተኛ ነን ባዮች ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በተለይ ወያኔ÷ኢሕአፓ ኢዲዩ እነግ ሌሎችም ተባባሪ ነበሩ። ኢዲዩ በተለይ በጎንደርና በትግራይ ይንቀሳቀስ ስለነበር የኢትዮጵያ ሕዝብ የርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለማርያምን ጥሪ ተቀብሉ እንዳይዘምት ጥረት ያደርግ ነበር። ይህ ጸሐፊ ጎንደር ክፍለ ሀገር ጎንደር ዙሪያ አውራጃ የታች አርማጭሆ አባት አርበኞች ወደ ጎንደር ሲጓዙ በኢዲዩ እንዳይዘምቱ ሲከለከሉ ተመልክቷል። የኢዲዩ ልጅ የኋላው ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ አንድነት የተባለው ድርጅት ሳይቀር ሱማሌ ገብቶ እንደነበር ተጽፏል።

ኮሞዶር ጣሰው ደስታ <u>የኢትዮጵያ አንድነት ትዝታና ትግል</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 179 "እኔ እ.ኤ.አ.ነሐሴ 21 ቀን 1984 ዓም ሞቃዲሾ ገባሁ። ከነሐሴ 22 ቀን ጀምሮ ከልዩ ልዩ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር እየተገናኘን ስለድርጅታችን ዓላማና ግብ በኢትዮጵያ በሱማሌ ሕዝብ መካከል ሰላም ለምን አስፈላጊ እንደሆነና ስለአገራችን ጠቅላላ የፖለቲካ ይዘት ባስረዳና ጥያቄ ስመልስ ከሰነበትኩ በኋላ በመጨረሻ ከፕሬዚዳንት ሲያድ ባሬ ጋር ተገናኝቼ በሞቃዲሾ ራዲዮ ጣቢያ ለመጠቀምና ቢሮም ከፍተን በሱማሊያ የሚገኙትን የኢትዮጵያን ስደተኞች ለማስተባበር እንድንችል ማስፈቀድ ቻልኩ" ሲሉ ጽፈዋል። የኢትዮጵያ የተማሪዎች ማሕበር ከተመሰረተ ጀምሮ በእኔ እምነት ለኢትዮጵያ የተሰራው ልማት ሳይሆን ኪሳራ ነው። ተማሪውን ያሳተፈው ኢሕአፓ ሱማሌ በኢትዮጵያ ላይ የምታደርገውን ወረራ የደገፈ መሆኑን ጽፈውልናል። ዛሬ ኢሕአፓ ተሳስቶ ነበር ብሎ መጻፍ ቀደም ከደርግ ጋር የሚያቆራኝ ሲሆን አሁን ደግሞ ከወያኔ ጋር አቆራኝቶ ባንዳ ያሰኛል። ነገር ግን ታሪክ በመሆኑ ከመጻፍ አንቦዝንም።

ጌታቸው አማረ ኢትዮጵያ ሪቪው መጽሔት ሚያዝና 1985 ዓም ወይም 1993 "ኢሕአፓ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ነበር የተሰለፈው ከተባለ የሶማሌ ጦር አብዛኛውን ሐረርጌን ባሌንና ሲዳሞን በቁጥጥር ስር እያዋለ እያለ ለምን ነበር ኢሕአፓ በመሃል አገር ይህንን ወረራ ለመከላከል የሚሯሯጡትን ወገኖቻችንን ባንዳ እያለ ሲገድል የነበረው" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ከዚህ በላይ የተነበበው ንባብ በኢሕአፓ ላይ ዜጎች የነበራቸውን ትዝብብ ነው። ከዚህ ዝቅ ብሎ ደግሞ ኢሕአፓን ሲመሩ ከነበሩት መካከል የተጻፈውን በጥሞና መመልከቱ ይጠቅማል።

ክፍሉ ታደሰ ያ ትውልድ ቅጽ ሁለት ገጽ 128 "ደርግ ለሕብረት ግንባር ያደረገውን ጥሪ ብርሃነ መስቀል በሙሉ ልቡ ተቀብሎታል። እንደሱ ሃሳብ ከሆነ ኢሕአፓ በዚህ ወቅት ታሪካዊ ድርድር አድርጎ ከደርግ ጋር አንድ ዓይነት ሕብረት መፍጠር ይኖርበታል። ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስ መነሻ ያደረገው ስለወቅቱ የኢትዮጵያ ሁኔታ ያቀረበው ትንታኔ ነበር። በብርሃነ መስቀል አስየታየት በምስራቅ በኩል የሶማሊያ መንግሥት የአገሪቱን የግዛት አንድነት አደጋ ላይ ጥሎታል። በምዕራብ ቀኝ ዘመም የፖለቲካ ኃይሎች እንደ ኢዲዩ ያሉት አብዮታዊ ግንባር ጠልፎ ለመጣል ሙከራ እያደረጉ ይገኛሉ። የኢኮኖሚ ሁኔታውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሂዶ ሐገሪቱ እየፈረሰች ስለሆነ በእሱ አስተያየት አገር ሳይኖር አብዮት ማካሄድ አይቻልምና ከደርግ ጋር አንድ ዓይነት ሕብረት መፍጠር ግዴታ ይሆናል" ሲሉ አቶ ብርሃነ መስቀል መናገራቸውን ልዩነቱ ከዚህ መጀመሩን ጽፈዋል።

ባብሌ ቶላ አንድ ትውልድ ለመምተር ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 149 "እጅግ ከባድ የነበረው ውስጣዊ ችግር የተቃጣው ደርግ ኢሕአፓ ላይ ጦርነት ካወጀ በኋላም እንኳ ደርግ ላይ ትጥቃዊ ተቃውሞ መደረግ የለበትም ባሉት ጌታቸው ማሩና ብርሃነ መስቀል ረዳ ሁለቱ የአመራር አባላት ነበር ኢዲሕንና የሶማሌን ወረራን ለመከላከል ፓርቲው ከደርግ ጋር የሕብረት ግንባር ለመፍጠር መሞከር አለበት ብለው ተከራከሩ። ከሁለቱ በደንብ የታወቀው ብርሃነ መስቀል ረዳ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል። በነገራችን ላይ ወያኔዎች በዚያን ወቅት የኢትዮጵያ ዳር ደንበር በሱማሌ እንዲደፈር ተባባሪ የነበሩ መሆናቸው አይዘነጋም።
ገብረ መድህን አርያና አብርሃም ያየህ፣ የወያኔው ታላቅ ሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ ክፍል 1 እና 2 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 127 "በሱማሌ ጦርነት ጊዜ ወያኔው በነበረው አቋም ላይ የምገልጸው አለኝ። በዚያ ወቅት በትግርኛ ወያኔው አንድ ጹሑፍ አውጥቶ ነበር። የሱማሌና የኢትዮጵያ ጦርነት ምን ይመስላል? የሚል። ወያኔ አንድ አቋም ወሰደች። ሱማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር የምታደርገው ጦርነት ፍትሐዊ ነው ብላ ኦጋዴን የሱማሌ ነው አለች። ጹሑፉ ወጣ እኛም ሕዝቡን ለማስተማር ተንቀሳቀስን። ይህ የመጀመሪያው ከባድ ጦርነት በነበረበት ከ1969 እስከ 1970 መጋቢት ወር ድረስ ነው። የሱማሊያ ጦርነት ፍትሐዊ ጦርነት ነው ወረራ አይደለም። ኢትዮጵያ ተስፋፊ እንደመሆኗ መጠን በኃይል የያዘችው መሬት ነው አለች። ወያኔ ለዚህም ውለታዋ ከሱማሊያ መንግሥት ብዙ የጦር መሣሪያዎች አግኝታለች።



እርዳታው በሱዳን ዙሮ ነው ትግራይ የገባው" ሲሉ አቶ ገብረ መድህን ተናግረዋል። እነ እነግና ሌሎችም ድርጅቶች መስሪያ ቤታቸውን መቃድሾ ያደረጉና በሶማሌ መንግሥት የሚረዱ እንደነበሩ አይዘነጋም። ጠንካራ መሪ ለድል ያበቃል እንደሚባለው በዚህ ወቅት ርዕሠ ብሔር ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሱማሌን የአስር አለቃ መለዮ ልብስ ለብሰው ተዋግተዋል።

ደመቀች መንግሥቱ ኢትዮጵ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 72 ሐምሌ 1997 ዓም ገጽ 32 "ሐረር ከተማ የደረሱት መኮንን የጊዜያዊ መንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣን መሆናቸውን ሰማን። ቆየት ብሎ ሁኔታውን ስናጠና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም እንደሆኑ ማረጋገጥ ቻልን። ጠላት አፍንጫህ ላይ ቆሞ እያናፋ ቁጭ ብለሃል!በየአልጋህ ላይ ወጥቶ ሚስትህን እስኪቀማህ ነው የምትጠብቀው? እያሉ የጦር መኮንኖቹን ይቆጡ ነበር። አንዳንዶቹ ይህቺ የአስር አለቃ ማዕረግ የለበሰችው ቆፍጣና ዕኮ መንጌ ነች እያሉ ያንሾካሹካሉ። ወዲያው እሳቸው ከሠራዊቱ ጋር ወደ አፍደም ግንባር ተንቃነቁ። ከሁት ቀናት በኋላ አብዮታዊ ሠራዊት ካራ ማራን ከጠላት መዳፍ ያስለቀቀ መሆኑን የሚያበስር ዜና ሐረር ከተማ ደረሰ" ሲሉ ሎሚ ተራ ተራ የተሰኙችውን ዘፈን ያዜሚት ድምጻዊ ተናግረዋል። ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ከሱማሌ ጦርነት ላይ መዋላቸውን ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ክደት በደም መሬት በተባለው መጽሐፋቸው ጽፈዋል። ይህ ጀግንነታቸው ግን ለ1983 ዓም ሳይሆን ቀርቷል ወደ ነበርኩበት ልመለስ።

እርሳቸው ዓለም አቀፍ ጦርነት እየተደረገባቸው ደንበር ለማስከበር ጥረት አድርገዋል። ሱዳን ሳለን የሚነገር ታሪክ ነበር። እርሳቸው ሱዳንን በግልጽ ሊጎበኙ ሲመጡ ከጃፋር ንበሪ ጋር ስለ ኢትዮጵያ ስደተኞች ጉዳይ ሲነጋገሩ አሉ ተብሎ የተነገረው "የኢትዮጵያ ስደተኞች ሱዳን አሉ ብለን የምናምነው ፖርት ሱዳንና ካርቱም ያሉትን እንጂ ገዳሪፍ ከሰላና ደባዚን ያሉትን ስደተኝ ናቸው አንልም አሉ" የእርሳቸው አባባል ምን ያህል ጃፋር ንበሪ እንደገባቸው ባይታወቅም በርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አባባል ግን ያሉት ከሀገራቸው ነው ለማት ነው። በጎንደርና በጎጃም በኩል ከሱዳን የሚያደናብረውን ጠረፍ በተመለከተ መንግሥት ለማስጠበቅ ጥረት ሲያደርግ ድርጅቶች መጠጊያ ስላደረጉት ሱዳኖች ሲጠቀሙበት ኑረዋል። ይህ ጸሐፊ በ1975 ዓም ሱዳን ሲገባ ቀድሞ ኢትዮጵያውያን ያርሱት የነበረውን ግራር ውኃ ድረስ ሱዳኖች ያረሱትን እህል ሲሰበስቡ ተመልክቷል። በሰኔ መቀር እንጨቱን ዙሪያውን ከርክረው ቅርፊቱን አስለቅቀውት ይከርማል። ይህ ተቆልሎ የከረመውን በሕዳርና በታህሳስ እጣን ይሆናል። ሱዳኖች ይህን እየቀረፉ ሲጭኑ ተመልክቷል። የበርሃ ሽመል የምንለውን ቅርቅሃ ቆርጠው አድርቀው እነሱ ሎሪ በሚሉት የጭነት መኪና ሲወስዱ ተመልክቷል። የቤት መስሪያ እንጨት ይወስዳሉ። የቤት መስሪያ እሳር ይወስዳሉ። የበርሃውን ንብ ማር ቆርጠው ሲጠቀሙበት ተመልክቻለሁ። በዚህ ወቅት ግጨው ተብሉ ከሚጠራው በርሃ የኢሕአፓ ስራዊት ነበር።

ሱዳን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሆነ መንግሥት ይፈራል። በተለይም ርዕሠ ብሔር መንግሥቱን ይፈራቸው ነበር። አንድ ቀን ከሰላ እና ገዳሪፍን ሊይዝ ይችላል የሚል ፍራት ነበራቸው። በመንግሥት ደረጃ ሳይሆን ተራው ሕዝብ ሳይቀር ይፈራቸዋል። አንድ ቀን ከተባበሩት መንግሥታት ጽሕፈት ቤት የአሜሪካ ምዝገባ ይደረጋል ተብሎ የሰማው ላልሰማው በየምግብ ቤቱ ላሉት ኢትዮጵያውያን ተነገረ። ታዲያ ኢትዮጵያዊ ሸርጡን ሳያወልቅ ሁሉም ወደ ጽፈት ቤቱ ሲሮጥ ኢትዮጵያዊ አንድ ሱዳን ቆሞ ተመለከተና "ሐበሺ ግልኩም +ሐበሽ ምን ሆናችሁ" ብሎ ሲጠይቀው "ያ ሃጅ መንግሥቱ ጃ" ሃጅ መንግሥቱ መጣ" ብሎ ሲነግረው ሱዳናዊው ለሌሎች ሱዳን "ያ ጀማ ያ ሸይጣን መንግሥቱ ጃ" እናንተ ያ ሳይጣን መንግሥቱ መጣ እያለ ጀለብያውን ሰብስብ አድርጎ በጥርሱ ነክሶ ሲሮጥ ሌሎች ሲሮጡ ዋሉ።
በ2000 ዓም የጭልጋው አራሽ እንደፋራሽ ጋር በሱዳንና በኢትዮጵያ የደንበር ጉዳይ ላይ ስንወያይ "ሱዳኖች ልብ ኑሯቸው የኢትዮጵያን መሬት ሊደፍሩ አይችሉም። ነገር ግን ወያኔ ኢትዮጵያውያንን አኮላሽቶላቸው እንሆ ደበደቡን" ሲሉ ሀዘናቸውን ገልፀዋል። ሱዳኖች በኢትዮጵያ መሬት ላይ አርሰው መብላት የጀመሩት ቀደም ብሎ ሲሆን ድርጅቶች ፈቅደውላቸው ነው ተብሎ ይወራ ነበር። በሰኔ 1983 ዓም የኢዲዩ ወሳኝ የነበሩ አቶ ታመነ አልያም ሊንጎ የተባሉ በዚያን ወቅት የትግራይ ልጆች ጠቅልለው ወያኔን ሲደግፉ አቶ ታመነ፣ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ሁነው ያለቅሱ ነበር። ዛሬ የት እንዳሉ አላውቅም ነገር ግን በዚህ ወቅት እርሳቸው አንድ ነገር ሲናገሩ ሰምቻለሁ። አቶ ታመነ "አንድ የሱዳን ባለስልጣን የድርጅት መሪዎች ጋር የተስማማንበት ጉዳይ አለ። ያም ሥልጣን ሲይዙ መሬት ሊሰጡን ፈርመውልናል ብሎ ነገረኝ። የየትኛው ድርጅት መሪዎች መፈረማቸውን ብጠይቀው ሳቀብኝ" ሲሉ ነግረውኛል ደርግ ዳር ደንበር ለማስጠበቅ ጥረት ማድረጉ እንደተጠበቀ ሁኖ ሱዳኖች ደግሞ ከግል ጥቅማቸውና ፀረ ደርግ አቅዋም ከመያዛቸው የተነሳ በደርግ መንግሥት ላይ አሲረዋል።
ርዕሠ ብሔር ጀኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን የኢትዮጵያ ርዕሠ ብሔር የሆኑት ከግንቦት 13 ቀን 1983 ዓም እስከ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም የ7 ቀናት መሪ ናቸው። በእርግጥ ዛሬ መተቸት እንችላለል። በእነዚህ በ7 ቀናት ውስጥ ምን ማድረግ ይችሉ ነበር? ለሚለው ጥያቄ ሌላው ቢቀር የዓለም ሕዝብን ጥሪ አድርገው አዲስ አበባን ወያኔ እንዳይዛት የማድረግ አቅም ነበራቸው ይላሉ። አዲስ አበባ የዓለም ከተማ ስለሆነች ሳይገቡ መደራደር እንጀምር ቢሉ ሌላው ቢቀር ለመለዮ ለባሹ ደህንነት መስማማት ይችሉ ነበር ተብሎ ይወራል። አበው ሲተርቱ "ክብሮ በሰው እጅ ታምሪያለሽ" እንደሚሉት ይሆናል። እርሳቸው በ7 ቀን ውስጥ ሊፈይዱት የሚችሉት ተግባር ለእኔ አይታየኝም። ወያኔን አዲስ አበባ አትግቡ ቢባሉ ገልብጠው መግባታቸው አይቀርም ነበር። ምክንያቱም ኃያሉ መንግሥት አረንጓዴ መብራት አሳይተቸው ስለሆነ ሽምግልናውን አይቀበሉትም። ያም ሆነ ይህ በታሪክ የ7 ቀን መሪ ይቅርና በኢትዮጵያ 6 ሰዓት መሪም ከነገሥታት ተርታ ተቆጥሮ ያለ ስለሆነ በዚሁ ለትውልዱ ለማስተዋወቅ ያህል ነው። እርሳቸው እርስ ብሔር ከመሆናቸው በፊት ተራ ወታደር መከላከያ ሚኒስተር ማዕረግ አገራቸውን ያገለገሉ ናቸው።



## ምዕራፍ 4

## ዳር ደንበር በርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ዘመን!

ከላይ እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ነበረች! ታዲያ በአንዳንድ ሥልጣን በናፈቃቸው ግለሰቦች ስበብ ደመች። ከዚያ አልፋ ወደ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ዘመን ደረሰች። እርሳቸው ግማሽ ኤርትራዊ የሆኑ በወያኔ ኮት ላይ ኢሕአዴግን ካባ ደርበው ወደ አዲስ አበባ ሠራዊታቸው ለአንድነት ሳይሆን ለልዩነት ተመመ። የርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም መንግሥት ዓለም አቀፍ ጥሳቻ ተደርጎበት እንክትክቱ ሲወጣ ወያኔ ኢሕአዴግ ኢአዲስ አበባ በመግባት የኢትዮጵያን አንድነት አፈረሰ። እርስ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ፣ ኤርትራ በተሎ መገንጠል አለባት ብለው ለተባበሩት መንግሥታት ደብዳቤ ጻፉ። በዓለም ላይ ብዙ ደካማ ስራ በአገራቸው የሰሩ መሪዎች ነበሩ። ነገር ግን እንደ አቶ መለስ ዜናዊ የሚበዛበት የሚኖር አይመስለኝም። አገሬን አልፈልግም የሚል መሪ ያለ እርሳቸው አልተወለደም። ምናልባት ሰይጣን እንጂ ፍጡር ይህን ስራ አይሠራውም።

ልጅ ሚካኤል ዕምሩ ኢትእጵ መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 054 ታሕሳስ/ጥር 1996 ዓም ገጽ 11 "ኢትዮጵያ በሕግ የተረጋገጠላትን የባሕር በር ተነጥቃ መኖር የለባትም" ሲሉ ተናግረዋል። በደርግ የመጀመሪያ ወራት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አስጠንቅቀዋል። ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን ሊያጠፉ የተነሱ ናቸው። ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ በጣም የሚገርመው ደግሞ የአፋር ሕዝብ አሰብ አስተዳደር "እኛ ኢትዮጵያዊ እንጂ ኤርትራዊ አይደለነም" እያለ ኢትዮጵያዊነቱን ለማስጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ትግል በሚያደርግበት ወቅት እናንተን አልፈልጋችሁም ኢትዮጵያዊ አይደላችሁም ብለው በግድ በኤርትራ እንዲተዳደሩ ማድረጋቸው ሰይጣንነት እንጂ የሰው ልጅነት አይደለም።

ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ዜጋ መጽሔት 5ኛ ዓመት ቁጥር 2 ጥቅምት 1996 ዓም ገጽ 23 "አሰብ የኤርትራ አካል ነች የሚለው በመጀመሪያ የተደመጠው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዋሽንግተን ለዓለም ጋዜጠኞች በሰጡት መንግለጫ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል። የአሰብን አስተዳደር የአፋርን ሕዝብ ጉዳይ በተመለከተ ከዚህ በፊት አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች! የተባለው መጽሐፍ ጽፌ ለአንባቢ ማድረሴ ይታወቃል። አንባቢያን አሰብ አስተዳደር ከቀድሞ ጀምሮ ኤርትራ የክርስትና ስም ከማግኘቷ በፊት ስማ ባሕረ ነጋሽ ትባል ነበር። በዚህ ወቅት ኤርትራና አሰብ አስተዳደር በአንድ የተዳደሩበት ወቅት ፈጽሞ የለም።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ረቂቅ በተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀ የሕገ መንግሥት ረቂቅ ሚያዝያ 25 ቀን 1986 ዓም ገጽ 1 አንቀጽ 2 "የኢትዮጵያ

የግዛት ወሰን የፌዴራሉን አባሎች ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የተወሰነው ነው" ይላል:: ይህ ሕገ ችግር እንዳለበት ከሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም በቀር ማንም የሕግ ምሁር ትክክል አይደለም ብሎ እንኳን ቀደም ዛሬም የደንበር ችግር ከተፈጠረ ጀምሮ የተቸው የለም:: በእርግጥ በአንቀጽ 39 ላይ ያልተጻፈ ጹሁፍ የለም:: ችግሩ ያለው ራሱ ይህ ሕገ መንግሥት የተረቀቀበት ቀን አንዱ ነው:: ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓም የውጫሌ ውል የተፈረበመት እስከ ዛሬ ችግር የተዘራበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሙ እንደጎርፍ የፈሰሰበት የአገሪቱ አካሏ ይበልጥ እየጠበበ የመጣበት መንስኤው የውጫሌው ውል የተፈረመበት ቀን ሲሆን ቀስ በቀስ ሌሎች ኤውሮፓ አገሮች የኢትዮጵያን ዳር ለዳር ከበው ያጣበቧት ይህን ተገን በማድረግ ነው:: ይህን ቀን የምናስታውሰው ኢትዮጵያ ልትደክም የቻለችበት ቀን መሆኑን ነው:: ለዚህም ነው ወያኔ ኢትዮጵያ ለማጥፋት ያሰበ መሆኑ ምልክቱ በዚህ ቀን አንቀጽ 39 የተረቀቀበት ቀን መልዕክት ነበረው::

ሌላው የወያኔው ረቂቅ "የግዛት ወሰን" የሚለውን ከዚህ እስከ ዚህ ብሎ ቦታ ስም ሊጠራ ያልፈለገበት ሌላ ዓላማ ስላለው ነው:: ዓላማው ኢትዮጵያን ሊገዛ ስጠየቀው ሁሉ ለመሸጥ ያመቸው ዘንድ እየተዘጋጀ መሆኑ ነው:: እንኳን በሌሎች ክፍለ ሀገር ያለውን ወሰን በቅጡ ሊጠቅስ ቀርቶ የራሴ ነው ለሚለው በትግራይ ሊያሰምርበት አልፈለገም:: ይህም ቢሆን ያቀደውና ያለመው ስላለው ነው:: በምስራቅ! በሰሜንና በምዕራብ በደቡብ ይህ አገር ያዋስነዋል ተብሎ ያልተጻፈበት አንድ ነገር መኖር አለበት ባይ ነኝ:: ልብ ያለው ሸብ ነው ልብ ያለው የለም እንጂ ቢኖርማ ይህ ሁሉ ጥፋት በአገር ላይ አይደርስም ነበር:: ዛሬ የኢትዮጵያ መንግሥት ብለን የምንጠራው ወያኔ ሲመሰረት ጀምሮ የኢትዮጵያን ታሪክ ለማጥፋት ኤርትራን ከፍ ለማድረግ ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሉ ራሷን የቻለች መንግሥት ለማድረግ የተነሳ ድርጅት እንደነበር አይክዱም:: ኤርትራውያን ከተገነጠሉ በኋላ በፌዴሬሽን ለመግባት ሀሳብ የነበራቸው ሲመስል ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ግን አልወደዱም::

አቶ ታምራት ላይኔ <u>ዜጋ መጽሔት</u> 3ኛ ዓመት ቁጥር ሰባት መጋቢት-ሚያዝያ 1994 ዓም ገጽ 17 "ከአንዳንድ የኤርትራ መንግሥትና የሻዕቢያ ከፍተኛ መሪዎች ጋር ኢትዮጵያና ኤርትራ እንደገና በኮንፌዴሬሽን ወይም በፌዴሬሽን ሊዋሀዱ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ አስመራ በሀረድኩባቸው ወቅቶችና አዲስ አበባ በመጡበትም ወቅት እያነሳሁ እወያይ ነበር:: በኤርትራ በኩል የመንግሥቱና የፓርቲው እምነት መሆኑን ባላውቅም ይህን ሀሳብ እንደግፋለን የሚሉ መሪዎች ግን ነበሩ:: ሆኖም አቶ መለስ ይህን ውይይትና ጉዳዩንም በተመለከተ መወያየትና ማንሳት እንደሌለብኝ የኢሕአዴግን ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት እየጣስኩ ነው በሚል ሽፍን ሲነግሩኝና ማስጠንቀቂያ ሲሰጡኝ ስለነበር ብዙ ጭቅጭቅ ፈጥረንበታል" ሲሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ቀርበው ያነበቡትን መጽሔቱ አውጥቶታል::



## ምዕራፍ 5

## ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን ሊሰጡ ነው?

1600 ኪሎ ሜትር የኢትዮጵያ መሬት ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን ወያኔ ኢሕአዴግ ሊሰጥ ነው:: ዛሬ ወያኔ ይህን አደረገ ብሎ መጻፍና መናገር ለአንዳንድ ጥቅም ለነካቸውና ወያኔን ለሚደግፉ ግለሰቦች "ይህ የቅንጅት ወሬ ነው" በማለት ያናንቁታል:: ቀደም ሲል ይህ የነፍጠኞች ወሬ ነው! ሲባል ቆይቶ ባለ ኋላ ደግሞ ይህ የቅንጅት ወሬ ነው! መባል ከተጀመረ ውሎ አድሯል:: ደግነቱ እኔ ነፍጠኛም ቅንጅትም አይደለሁም:: በመሰረቱ የግል ጥቅም የተጣበው ግለሰብ ሁሌም ምክንያት አያጣም:: ምክንያት የውሸት ታናሽ ወንድም ነው:: ወደኋላ ከተጻፈው መለስ ብለን ለማየት ስንሞክር የተጻፈውን ታሪክ ወያኔዎች በአገር ግዛት ምኒስትርና በሕዝብ ምክር ቤት በውጭ ጉዳይ ምኒስትር ጽፈት ቤት ያሉትን ሰነዶች ከማየታቸው በፊት እነሱ ስልጣን ሲይዙ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን እንደሚሰጡ ተስማምተዋል:: ለሱዳኖች ቃል የተገባላቸው ምናልባት በ1981 ዓም መሆኑ ይጠረጠራል:: ሱዳኖች የኢትዮጵያን መሬት ተሻግረው ማረስ የጀመሩት በ1984 ዓም መጨረሻ መሆኑን ሠነዶች አሉ:: ምክንያት ደግሞ እነሱ የሚያበሳጩት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍቶት ሱዳንን መጠጊያ አድርጎ እነሱን እንዳይወጋ ለሱዳን መሬት ለመስጠት ቃል ገብተዋል:: ለዚህም የቀድሞ የመተማውን ሀብታም የኋላው የኢዲዩ ሻለቃ አቶ አጣናው ዋሴንና ሌሎችንም ኢትዮጵያውያን ሱዳን እንዳይንቀሳቀሱ ከማድረጉም በላይ አፍኖ ለወያኔ አስረከበ:: ለምሳሌ በጭልጋ በኩል ከሱዳኖች ጋር የአካባቢው ሕዝብ ግጭት የጀመረው ቀደም ሲል ጀምሮ ነው::

አማረ አፈለ ብሻው <u>አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 201 "በጎንደር አብደራፊና መተማ ሱዳኖች ከኢትዮጵያ መሬት መቀር እጣንና የቤት መስሪያ እንጨቱን ቆርጠው ከመውሰድ አልፈው የሱዳን ወታደሮች ከተማ ውስጥ እስከ ትጥቃቸው ገብተው ኢትዮጵያውያንን ሲደበድቡ የወያኔ ኢሕአዴግ ወታደሮች ምንም አይሏቸውም ነበር:: በኋላ ሻዕቢያ በጫረው እሳት ወያኔም ገብቶ ሲነድ ፈልጎ ሲያበቃ አበረደውና ዛሬ ካለበት ሰላም ቢመጣም ቀደም ግን ኢትዮጵያውያን የጎንደር ሰዎች አልቀዋል:: በኬንያ ቢሆን ብዙ ችግር ይደርስ እንደነበር የተጻፉትን ሰነዶች አሉ:: አሰብ የነበረው የኢትዮጵያ ንብረት ሻዕቢያ ሲጠቀምበት ወያኔ ኢሕአዴግ ደስተኛ ነበር" ይል ነበር:: በየካቲት በ1998 ዓም የታተመው መጽሐፍ ተገልጾ ነበር:: እንዲሁም ግንቦት 1999 ዓም የተጻፈው መጽሐፍ ቀንጨብ አድርጎ ጠቅሶአል::

አማረ አፈለ ብሻው <u>የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 181 "በዚህ በየካቲት 1999 ዓም ጎንደር ጭልጋ ዘመድ ጥየቃ

ሕደው የነበሩ አንዲት ወዳጄ እያለቀሱ እንደነገሩኝ በጎንደር ክፍለ ሀገር በጭልጋ አውራጃ ያሉ ወረዳዎች አርሰው የሚበሉ ሱዳኖች በመሆናቸው ሕዝቡ አሳሳርስም መሬቴን ብሎ ተነስቶ ጦርነት በመግጠሙ 87 ኢትዮጵያዊን ሱዳኖች በእሳት አቃጠሏቸው:: ከዚህ ወዲህ ሕዝቡ ባሶንዳ ከሚባለው የሱዳን ከተማ ገብቶ ሰው ገድሎ ሲመለስ የወያኔ ወታደር ጠብቆ ፈጃቸው:: በጭልጋ በብዛት ኤንትሬዎች ከብትና በግ እህል ሌላም ቁሳቁስ እንደጫኑ ወደ ሱዳን ይገባሉ:: ከስላ ጤፍና ቡናውን ኤርትራውያን ተቀብለው ውጭ ይሸጣል:: ይህን ስንመለከት ሰንብተን ጎንደር ስንመጣ የወያኔ ባለሥልጣን ግለሰብ ትክክለኛ ስሙ ይሁን የበርሃ ስሙ ባናውቅም ተዋውቆን አብረን ስናመሽ ይህን አለን። አቶ ምትኩ በጭልጋ አውራጃ ውስጥ ለም መሬት በተለይም ደለሎ ሽመለጋራ፥ ሽንፋንና ሌሎችንም የቋራ የእርሻ መሬት አርሰው የሚበሉት ሱዳኖች ናቸው:: ይህን ስምምነት የተስማማነው ቀደም ብሎ ነው:: ሱዳኖች መሬቱ የእነሱ መሆኑን በካርታ ላይ ሳያወጡ ወደ አዲስ አበባ ስንገባ 90 የጭነት መኪና ስለሰጡን እኛም ይህን መሬት ፈቅደንላቸዋል:: እናንተ ምን ታደርጋላችሁ እኛ እንኳን እናንተን ቀርቶ መከረነው አልሰማ በማለቱ ታምራት ላይኔንም ከርቸሌ ዘግተነዋል" ሲል የነገራቸው መሆኑን ወዳጄ ስለነገሩኝ ጽፌ ነበር::

ከዚህ በላይ የጻፍኩት ቢሕትመት ከዋለ ጀምሮ በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ያለው መሬት ወያኔ ለሱዳን የሰጠው መሆነን ይፋ ይሆን ጀመር:: እኔም ቀደም በስደቱ አብረውኝ የነበሩ ሰዎችን ከቦታ ቦታ ፈልጎ ማግኘትና ሱዳኖች የኢትዮጵያን መሬት ከመቼ ጀምረው ማረስ ጀመሩ የሚለውን ለማወቅ ጥረት ማድረግ ጀመርኩ:: በታሪክ ስማቸውን ዘግቦ ለማስቀመጥ ያመች ዘንድ ከወዳጆቼ ጋር ተማክረን የፈረስ ስም ስጠን አሉኝ:: አሁን ያለን ትውልዶች የፈረስ ስም ምን ማለት እንደሆነ የተረሳን ይመስለኛል። የሌሎችን ትተን የነገሥታቱን የፈረስ ስም ልጥቀስ ለምሳሌ አጤ ቴዎድሮስ ታጠቅ ሲባሉ አጤ ዮሐንስ በዝብዝ ሲሆኑ አጤ ምኒልክ ዳኛው፤ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ጤና ሲሆኑ አጼ ኃይለ ሥላሴ ጠቅል ይባላሉ:: የርሰሠ ብሔር አቶ መለስ እኔ ለየምኩላቸው ሁለት የፈረስ ስም ነው:: 1ኛው አገርበትን ሲሆን 2ኛው ሕዝብንገደል ቢባሉ መልካም ይሆናል:: ስለዚህ እኔም ጭልጋና መተማ አብደራፊ ያሉትን ወዳጆቼን እነሱ ባነሱት ታሪካዊ ቃል ታጠቅ ብያቸዋለሁ::

<u>አባ ታጠቅ</u> የተባሉት ቡድኖች ጋር በስልክ ስንነጋገር "አጤ ቴዎድሮስ የአባ ታጠቅ አጽማቸው ያረፈበት ገዳም ማህበረ ሥላሴ እንዴት ለሱዳን ይሰጥ? በሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ አጤ ቴዎድሮስ ያለ ጀግና ነበር ብለን እንዳንፈክባቸው ወያኔ መቃብራቸው ያለበትን ገዳም ለባዕድ አሳልፎ ሰጠብን:: ስለዚህ ለመሬታችን እኛ እንሞታለን እናንተም አትርሱን" ባሉኝ መሰረት ቃላቸውን ሳልቀይር እንሆ ጽፌዋለሁ:: እነ አባ ታጠቅ የነገሩኝ "ሱዳኖች እኛ እንደምናውቀው እንጨትና መቀር እጣን እየለቀሙ ይወስዱ ነበር:: በማረስም ቀደም ሳይበዛ ነበር:: ኢሕአዴግ ሥልጣን እንደያዘ በ1983 ዓም በሰኔ ወር መቀር ከርካሪዮች ቀደም ከሚከርክሩበት አልፈው ከመሃል ድረስ መሄድ ጀመሩ:: መተማና አብደራፊ ወታደሮቻቸው እስከ ትጥቃቸው ይገባሉ::



ሰክረው ሰው እየገደሉ ሲሄዱ መንግስት ዝም ብሎአቸዋል:: በ1984 ዓም ላይ የእርሻ ትራክትራቸው መሀል ድረስ ገብቶ ማረስ ሲጀምር በሕዝቡና በሱዳን አራሾች መካከል ጠብ ሲፈጠር የሱዳን አራሾች ወታደር ሲረዳቸው የእኛ አራሾች ግን ስንደበደብ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር:: ከዚህ በኋላም ቢሆን ሱዳኖች ሕዝቡን ሲገድሉና ሲያሰቃዩ በእኛ መንግሥት በኩል ዝም በሉ እንጂ አይዟችሁ የሚለን አልነበረም::"

"ከ1988 ዓም ወዲህ በምን ምክንያት እንደሆነ ባይታወቅም መንግሥት አይዟችሁ ማለት ሲጀምር አራሹም ተደስቶ ያለ የሌለውን ሀብት አጠራቅሞ ለእርሻ መሰማራት ጀመረ:: በሁለቱ መንግሥታት መካከል ግጭት በመፈጠሩ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ደህና እድል በማግኘታቸው ለልማት ተዘጋጁ:: ነገር ግን ሱዳን ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን በግፍ ተገደሉ:: ሱዳኖች ኢትዮጵያውያን ገድለዋል:: እድለኛ የሆኑ ንብረታቸውን ተቀምተው ራቁታቸውን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በችግር ተሰቃይተዋል:: ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት ሹፌር የነበረው አቶ ታረኩ ዓለሜን ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል:: ለነዚህ ኢትዮጵያውያን ማንም አይዟችሁ ያላቸው አልነበረም:: አንዳንዶች ራሳቸውን እስከ መግደል ደርሰዋል::"

"በዚህ ወቅት ያለቀው ኢትዮጵያዊ አምሳክ ይቁጠረው:: ይህ ከሆነ በኋላ በተለይ ከ1991 ዓም ወዲህ ወያኔና ሻዕቢያ ሲጣሉ የሱዳንና የኢትዮጵያ ግንኙነት ተሻሽሎ እንዲያውም ያለ ቪዛ በአውቶቢስ ከጎንደር ገዳሪፍ መግባትና መውጣት ተጀመረ:: የኢትዮጵያ የጭነት መኪናዎች በቀጥታ ፖርት ሱዳን ድረስ መሄድ ጀመሩ:: ከመተማ እስከ ጎንደር በ6 ወር ውስጥ 12 ድልድይ ተሰራ:: በዚህ ወቅት አልምቶ ሀብት ለማግኘት ኢትዮጵያውያን ወደ ጠረፍ መጥተው ለስራ ተሰማሩ:: በዚህ ሰዓት ሱዳኖች ኢትዮጵያውያንን ሲገድሉና ሲያስሩ ንብረታቸውን ሲዘርፉና ሲያቃጥሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ዝም አለ:: ሕዝቡ ግን በግሉ ንብረቱን ለማስጠበቅ ጥረት ሲያደርግ የኢትዮጵያ መንግሥ ለምን አገራችሁን አስከበራችሁ፤ለምን ንብረታችሁን ለማስጠበቅ ትጥቅ ይዛችሁ ተነሳችሁ ብሎ ጨፈጨፈን:: ይህ ነው ከሞላ ጎደል በደንበሩ በኩል ያለው" ሲሉ ነግረውኛል:: ከዚህ በላይ የአባታጠቅ ቡድኖች የነገሩኝን ከሰማሁ በኋላ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ይታተሙ የነበሩ መጽሔቶችን ከመደርደሪያ ማገላበጥ ስጀምር ልክ ነው በዚህ አካባቢ የዘገቡት መኖሩን አረጋገጥኩ::

ዮብል <u>አፍሪካ ቀንድ መጽሔት</u> ሰኔ 1985 ዓም የጻፈውን እንዳለ ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይመልከቱ:: አደራ መጽሔት ግልጽ አድርጎ መሬቱን ሱዳኖች እያረሱት ነው ብሎ ሳይሆን የጻፈው መልእክቱን ያስተላለፈው በግጥም ነው:: ሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ነው የሚባለው ለዚህ ነው:: የአካባቢውን ችግር ለሚገባው ገልጾ ጽፎአል::

<u>አደራ</u> መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 1. 1985 ዓም ገጽ 13
"መተማ የጎንደር ዘማች

ተቸግሮ በጎልም አፋች
እንደሞት ሁሉ ላንድ ሞት መተማ የሁለት ፊት ትግል
ያንዱን ዕድል ለሌላው ድል
ለታሪክ ሕሊና ቁስል
በዕድሜ ምዕራፍ ስታዋውል
ሐአሰት ዓዶት መተማ
ነጋ ጠባ ስታቅማማ
ደማች የፋሲል ከተማ" ሲል ጽፏል።

የአበው አነጋገር ከመሬት ጠብ አይልም። ያም "ማልቀስ የፈለገ ቁልቋል ከእሸኸም ይጠጋል" ይላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ቁልቋል ሁኗል። ወያኔ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እሸኸም ሁኗል። ይህን አሊ የሚል ያለ አይመስለኝም። አልያም ከወያኔ ጥቅም ያላቸው ግለሰቦች ካልሆኑ በቀር የኢትዮጵያን ደህንነት የሚፈልግ ሁሉ ወያኔ ለኢትዮጵያ ሽሆ መሆኑን ያምናሉ። በሰኔ 1985 ዓም የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በሱዳን እየተሰቃዩ ናቸው የሚለው ዜና በኢትዮጵያ ተሰራጭቶ መንግስት ነኝ ባዩ ደግሞ በታህሳስ 1986 ዓም 17 ቀን የቆየ ስብሰባ ካርቱም ላይ አደረገ።

ደርቦ ሙዳይ መጽሔት መስከረም 1986 ዓም "አሁን በቅርቡ ሱዳኖች ህጋዊ የወሰን ክልሉን እየጣሱ ድልብ መሬቱን ሲያርሱበት አልፎ ተርፎም አፈር ገፍተው የሚኖሩ ወገኖቹን በመትረየስ ሲጨፈጭፍበት የመንግሥት ያለህ? የዳኛ ያለህ? የባንዴራ ያለህ" እያሉ እየተማፀኑ ነው ሲሉ ጽፈዋል።

የአፍሪካ ቀንድ መጽሔት ታህሳስ 1986 ዓም ገጽ 5 "በሱዳን ዋና ከተማ በካርቱም ሲካሄድ የቆየው የኢትዮጵያና የሱዳን የሚኒስትሮች የጋራ መማክርት ጉባዔ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ተጠናቀቀ። በጠቅላይ ሚኒስትር በአቶ ታምራት ላይኔ የሚመራው የኢትዮጵያ ልዑካን 17 አባላትን የያዘ ሲሆን የሱዳን መንግሥት ልዑካን ቡድን የተመራው በምክትል ሚኒስትሩ በጄኔራል አዚቤር ሙሐመድ ሳላህ ነበር። ጉባዔው ከዚህ በፊት በሁለቱ አገሮች መካከል የተፈረሙትን ስምምነቶች በጥልቀት የመረመረ መሆኑ ተገልጿል።"

"የሱዳን መንግሥት ለስምምነቶቹ መጎልበት ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጥ ከባለስልጣናች መግለጫ ለማወቅ አዳጋች አልሆነም። በቴክኒክ በትምህርት፣ በማስታወቂያ፣በንግድ፣በድንብር፣ ደህንነትና በመረጋጋት እንዲሁም በተለያዩ ሌሎች ጉዳዮች የተደረሰባቸው ስምምነቶች ሁለቱንም ወገኖች ማርካታቸውን በየበኩላቸው ይፋ አድርገዋል። ይህ በእንዲህ እያለ ፕሬዝዳንት አልበሽር የሀገራቸውን የፕሬስ ሰዎችን ስብሰባ ሲከፍቱ በአደረጉት ንግግር ላይ እግረ መንገዳቸውን የሁለቱን አገሮች ጉባዔ አንስተው አሞግሰዋል" ሲሉ ጽፈዋል። በዚህ ወቅት ከርዕሠ ብሔር አቶ ታምራት ላይኔ ጋር አብረው ከሄዱት መካከል አቶ ስዬ አብርሃ፣ ነበሩ። እርሳቸው የዚህን የስብሰባ ጉዳይ ደግሞ እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል።



አቶ ስዬ አብርሃ አዲስ ነገ ጋዜጣ ቅጽ 1 ቁጥር 32 ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓም ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ሳይገባ በፊት የምዕራብ ጎንደር እና ምዕራብ ትግራይ ቆላማ አካባቢዮች በርከት ያሉ ዓመታት የደርግ ጦር ለቋቸው ነበር። ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ የሽግግር መንግሥት እንደ ተመሰረተ በአካባቢው ሰራዊት አላሰፈርንም ነበር። በዚህ ወቅት ተጓዳኝ ክሥተቶች ተከፍተዋል። በአንድ በኩል በጦርነቱ ምክንያት ተስተጓጉሎ የቆየው የዚህ ቀጠና የእርሻ እንቅስቃሴ ማንሰራራት ጀመረ። ለበርካታ ዓመታት ባድማ ሁኖ የነበረው ማሳ እና ተጥለው የቆዩት አሮጌ የኢትዮጵያ ትራክተሮች መላወስ ጀመሩ። በርካታ ኢትዮጵያውያን ለዚሁ ሥራ ወደ አካባቢው ተመለሱ። በሌላ በኩል ደግሞ የሱዳን መንግሥት ይህን የጥበቃ ኬላዎች ያለመኖር ሁኔታ በመጠቀም ሠራዊቱን ወደዚህ ቀጠና ማስገባት ቀጠለ። ሱዳናውያን አራሾች የሰራዊታቸውን ኮቴ እየተከተሉ መጠጋት ጀመሩ። ባለቤት የሌለው መሬት አገኘን ብለው ደኑን ማጥፋት የእርሻ መሬቱን እንዳሻቸው መያዝ ቀጠሉ።"

"የሽግግር መንግሥት ተመስርቶ በጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ የሚመራ የሚኒስትሮች ልኡክ ወደ ሱዳን ሲሄድ ከሄዱት ሚኒስትሮች መካከል አንዱ ነበርኩ። በዚህ የሞቀ ወዳጅነት ወቅት ሱዳኖች ይዘውት የወጡት ትልቁ አጀንዳ ድንበር እንካለል የሚል ነበር። እኛ በዚህ ጉዳይ ለመነጋገር ዝግጁ አልነበርነም። ስለዚህ የኢትዮጵያ እና ሱዳን ድንበርም የጠበቀ ዕውቀት አልነበረነም።  እነርሱ ግን ስለ ጉዳዩ በደንብ የሚያውቁ ባለሞያዎች እና ሰነዶችን ይዘው ነበር የጠበቁን። እኛም እሺ ወይም እምቢ ሳንል ጉዳዩን ገሸሽ በማድረግ ውይይታችንን በሌሎች ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ብዙ ጥረት ብናደርግም አጀንዳውን ከመከላከያ እና ጸጥታ ጉዳይ ጋር በማያያዝ ነገሩን የማይታለፍ ለማድረግ መፈለጋቸውን ስንገነዘብ እቅጩን መናገር ነበረብን። ባላጠናነው እና ባላወቅነው ጉዳይ ላይ አሁኑኑ ድንበር ይከለል ማለት አንችልም። የሽግግር መንግሥት በመሆናችንም ድንበር የማካለሉ ውክልና (ማንዴት) የለንም አልናቸው ነገሩም በዚህ ቆመ።"

"ይህም ሁኖ ሱዳኖች በደንበር አካባቢ የጀመሩትን ጉዳይ አላቆሙም። ይባስ ብለው በእርሻ ሥራ መቋቋም የጀመሩትን ኢትዮጵያውያን ገበሬዎችን መተናኮል እና መጋፋት ጀመሩ። ይህ ሁኔታ እየባሰበት በመሄዱ ውስን የመከላከያ ኃይል በዚሁ አካባቢ ማስፈር ቀስ በቀስ ይህንኑ ማጠናከር ጀመርን። ሰራዊቱ ይህን በአራሾች ላይ የሚደርሰውን በደል እና በዐይናችን ፊት የሚደርሰውን ውድመት መቃወም ጀመረ። አንድ ቀን በዚህ አካባቢ የተመደበው የመከላከያ ሰራዊታችን አዛዥ የጽሑፍ መልእክቱን አስይዞ እቻው ወደ ሆነው የሱዳን ጦር አዛዥ አንድ መልእክተኛ ጓድ ይልካል። የተላከው ጓድ የተደረገለት አቀባበል የወዳጅ አገር ሠራዊት አቀባበል አልነበረም። ኑ ብለው ተቀብለው ትጥቃቸውን አስፈትተው አረዷቸው። ይህ ድፍረት እና ጭካኔ እንደ ተፈጸመ ሠራዊታችን አይምሬ የአጸፋ እርምጃ ወስዶ በአካባቢው የነበረው ጦር ወጣ ቀረ። እኔ በሐላፊነት እስከ ነበርኩበት ጊዜ ድረስ ሱዳኖቹ ወደዚህ አካባቢ ተተኪ ሰራዊት አልላኩም።"

"አቶ መለስ ሠራዊታችን በ1995/1996 አካባቢ የወሰደው ማጥቃት ብሎ የገለጸው ይህንኑ የአጸፋ እርምጃ ነው። ይህን አካባቢ ሠራዊታችን በወሰደው የአጸፋ ርምጃ ምክንያት በእጃችን የገባ የእኛ ያልሆነ መሬት አድርጎ ማቅረብ ግን ትክክል አይደለም። የሱዳን ወታደሮች እና እነርሱን ተከትለው የመጡት የሱዳን አራሾች ወደዚህ ቀጠና የመጠጋታቸው ታሪክ ከፍ ብሎ ከገለጽኩት የነገሮች አንድነት ጋር የተያያዘ ነውና ድንበር ሳይከለል በፊት እንዲህ ብሎ ፍርድ መስጠት አይገባም ነበር።"

"የአቶ መለስ መንግሥት ከኤርትራ እና ኢትዮጵያ ድንበር ክርክር ጋር በአንዳንድ የጸረና እና የአካባቢዋ ቦታዎች ላይ ለኤርትራ ምስክርነት መስጠቱ እና የሄጉ ኮሚሽን በዚሁ ተመስርቶ እነዚህ አካባቢዎችን ለኤርትራ እንዲሰጡ መወሰኑን ኮሞሽኑ ሪፖርት ለመገንዘብ ችለናል። አሁንም በአንድ በኩል ድንበር አልተካለልንም እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ ሰራዊታችን በወሰደው ማጥቃት ምክንያት የእኛ አራሾች ገብተውበት ሲጠቀሙበት የቆየ የእኛ ያልሆነ መሬት ነው ብሎ አስቀድሞ በኢትዮጵያ ላይ እየመሰከረ ነው። አቶ መለስ ስለ ሱዳኖች እርቆ አስተዋይነት ከመናገሩ በፊት ስለ ገዛ ራሱ አስተውሎ ቆም ብሎ ቢጠይቅ ይሻል ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

<u>ጦቢያ መጽሔት</u> ቅጽ 10 ቁጥር 11.1995 ዓም ሙሻዘር አምድ ገጽ 19 "የሱዳን ገበሬዎች 300.000 ሄክታር መሬት ከኢትዮጵያ ጠየቁ? ጦማር ሰኔ 10/1995 ዓም እውነት ብለዋል። ማን ከማን ያንሳል ልጄ? ይልቅስ አባት ሳለ አጊጥ ጀምበር ሳለ ሩጥ ነውና የድንበር ኮሞሽኑና የሥራ ጊዜያቸውን ሳያጠናቅቁ ይሄን ነው በነካ እጃቸው ማስፈረድ" ሲል ጽፏል።

የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፍ ላይ ደንበሩን አስመልክቶ በጻፍኩት አተታ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ትክክል አይደለህም ብለው ወቀሱኝ። ምክንያቱም ወያኔ ምንም እንኳን ፀረ ኢትዮጵያ አንድነት አቅዋም ቢኖረውም ማሕበረ ሥላሴን ገዳም ይሰጣል ማለት ሐሰት ነው" አሉኝ። እውነት በመሆኑ ታሪኩ ሲወጣ ከአንድ ዓመት በኋላ አንዳንዶቹ አይናቸውን በጨው አጥበው "እባክህ ጠቃሚ ሰነድ ካለህ ላክልን" እያሉ የጠየቁኝ ቀደም ሲል የወቀሱኝ ናቸው። እውነት ትታመማለች እንጂ አትሞትም። ከአሜሪካ ኢትዮጵያ ልማት ሊያለሙ ለሕዝብና ለአገር ሥራ የተሰራ መስሎ የታያቸው ብዙ ዜጎች ኪሳራ ደርሶባቸዋል።

<u>የጭልጋው አራሽ እንደፋራሽ</u> ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓም ሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ትምህርት ስንከታተል ቆይተን ጭውውት ስንጀምር የደረሰበትን ዘርዝረው እንዲህ ሲል ነገሩን። "በጎንደር ክፍለ ሀገር ጭልጋ አውራጃ ቢካ ወንዝ አጠገብ ነበር ልማታችን ታዲያ ብዙ ንብረት ወድሞብናል ሰራተኞቻችን በሱዳን ታፍነው ተወስደውብናል። ከሱዳን ጋር ሰላም ስለሆነ የኢትዮጵያ ደንበር ጠባቂ በአካባቢው የለም።



በትውልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት አሜሪካዊ የሆነ ተሰባስበን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከአቶ ስዩም መስፍን ጋር ለውይይት ስንቀርብ እርሳቸው።"

"እናንተ የፖለቲካ ድርጅት ደጋፊዎች ካልሆናችሁ ልማታችሁን አልሙ የሚጠብቃችሁ ወታደር እንስጣችሁ ለተዘረፈው ንብረታችሁ ከባንክ የተበደራችሁትን ሆነ የግል ብራችሁን በሚመለከት ለወደፊቱ እንነጋገራለን። ሰራተኞቻችሁ ይፈቱላችኋል ባሉን በ29 ቀን ተለቀቁልን። የኢትዮጵያ መንግሥት አውቆ እንጂ ያዘረፈን ሱዳን እንዳልሆነ ልባችን ያውቃል። እኛ የውጭ አገር ፓስፖርት ስላለን እንጂ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ታስረዋል! ተገድለዋል! ተዘርፈዋል፣ብዙ ጥፋት በአካባቢው ደርሶበታል" ካሉ በኋላ በሰዎች የሰሙትን ታሪክ እንዲህ ሲሉ "የሱዳን ወታደር መጥቶ ስንጃ ከተማ አካባቢ የኢትዮጵያውያንን ንብረት በጉንና ፍየሉን ነድቶ ወሰደ።"

"እነዚህ በስንጃ አካባቢ ንዋሪ የሆኑ 3 አርሶ አደሮች ሱዳን ገብተው ሶስት ሱዳናውያን ያዙ። ከዚያም ንብረታችንን ስታመጡ ሰዎችን እንለቃለን ብለው በአርብኛ ቋንቋ ጽፈው እንዲተው አድርገው ሱዳኖችን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ሱዳኖችም አንድም ግልገል ሳያጠፉ እየነዱ አመጡ። ሰዎችም ተለቀቁ። ወዲያው ወያኔ ወታደር ልኮ ለምን አስራችሁ አመጣችሁ ብሎ እነዚያንን አርሶ አደሮች መሳሪያቸውን ቀምቶ አሰራቸው። ሰዎችም እኛ መዘረፋችን ለመንግስታችን አቤት ብንል የሰማን የለም በጉልበታችን ንብረታችን አስመልሰናል ስለዚህ ወንጀለኛ አይደለነም። ብለው ቢከራከሩ ሰሚ አጥተው የታሰሩ መሆናቸውን ሰምቻለሁ" ሲሉ ነግረውኛል። ስማቸው እንዲጠቀስ ስላልፈለጉ ለዋቢ ጥቅስ ያመች ዘንድ የጭልጋው አራሽ እንደፋራሽ በሚል ሰይሜያለሁ።

በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ ጋንቤላን ወያኔ አሳልፎ ሊሰጥ መነሳቱ ነው። ጋንቤላን በተመለከተ ያለቀለት ጉዳይ መሆኑ ከክቡር አክሊሉ ሀብተወልድ ማስታወሺያ የተወሰደውን ማንበብ ይቻላል። ይህን ለም መሬት ወያኔ ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት መነሳት ማለት ጉዳዩ ምንድነው? የአካባቢውን ሕዝብ እርስብ በእርስ ማጫረሱ የማይበቃ ሁኖ እንዴት ዛሬ ደግሞ መሬቱን ለሱዳን ሊሰጥ ይነሳል። ሱዳኖች እነሱ መሬት ጠቧቸው ሳይሆን ፍላጎታቸው እስልምና ሃይማኖት ለማስፋፋት ታጥቆ ከተነሳው ከአረብ አገር በሚለገሱት ገንዘብ መሆኑን እንዴት ማጤን አቃተው? ለሱዳን ሱዳኖች በቀላሉ ቅልብስ የሚሉ ከመሆናቸው የመጣ ሌሎች ወያኔን የሚቃወሙ የሥነ መንግሥት የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሱዳን መሄድና የጦር መሳሪያ ገዝተውና ተውሰው በርሃ ገብተው እርሱን እንዳይወጉት ነው። ወያኔ ሥልጣን እንደያዘ የደርግ መኮንኖች ሆኑ ሌሎች ባለሥልጣኖች በሱዳን ውስጥ እንዳይቀመጡ ከፍተኛ ጫና በማድረግ እንዲወጡ ማስደረጉ አይዘነጋም። ለምሳሌ ጀኔራል ኃይሌ መለስ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችን ሱዳን እንድታስለቅቅ አድርጓል።

ወያኔ ሱዳን ከአገሯ እንድታስወጣ ሳይሆን የቀሩትንም አስራ እንድትሰጠው አደረገ። አቶ አጣናው ዋሴ (ሻለቃ) ሌሎች ቁጥራቸው ያልታወቀ

ኢትዮጵያውያንን ሱዳን አስራ ለወያኔ አስረክባለች:: መቶ አለቃ ሞላ እንዴት ሞቱ? ወያኔና ሱዳን ናቸው:: ሌሎችም ብዙ ኢትዮጵያውያንን ሱዳን አስራ ለወያኔ የሰጠችው ያለ ምክንያት አይደለም:: ወያኔን በትጥቅ እንዋጋለን እያሉ ወደ ሱዳን የገቡ ብዙ ግለሰቦች ቀደም ሲል ነበሩ:: ከፋኝ ኢትዮጵያ የጀግኖች ግንባር ሊቀ መንበር ሊቅ ዶ/ር አንዱአለም ሙላው የኢሕአፓው አቶ መርሻ ዮሴፍ ሌሎችም ብዙ አለን ባዮች ሱዳንን ረግጠው ነበር:: ነገር ግን የሱዳን መንግሥት ከግል ጥቅሙ ጋር የሚራመድ በመሆኑ የሁሉም የትጥቅ ትግል ግቡን ሊመታ አልቻለም:: ወያኔ ሱዳንን የሚያስፈራራበት የራሱ ዱላ አለው:: ያም በርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ዘመን ሱዳንን የሚቃወሙትን ድርጅቶች ይረዳ ስለነበር ወያኔ አዲስ አበባ እንደገባ ቀጥቅጦ ነው ያባረረላቸው:: ሱዳኖች ወያኔን በመከነን በአርብኛ የጻፉትን ወደ አማርኛ ተርጉመው መስታውት መጽሔት አውጥቶታል::

ዶ/ር ፒተር ኒዮተከክ <u>መስታውት መጽሔት</u> ቅጽ 1 ቁጥር 1 መጋቢት 1985 ዓም ግልጽ ደብዳቤ ለአቶ መለስ ዜናዊ በሚል ርዕሥ ገጽ 10 "በመቶ ሺሀ የሚቆጠሩ የሱዳን ስደተኞች ከኢትዮጵያ ሠፈራቸው እንዲፈናቀሉና የአክራሪው የሱዳን መንግሥት በቦንብና በጥይት እንዲቀበላቸው መደረጉ በኢትዮጵያና በሱዳን ሕዝቦች መካከል ለረጅም ጊዜ ፀንቶ በቆየው ልባዊ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል:: ዋናው መንግሥት በአሁኑ ጊዜ ራሱን እንደ ኢትዮጵያ ነፃ አውጪ እየቆጠረና እየቀረበ ሲሆን ከሱዳን ሕዝቦች ጋር ለሚደረገው ጦርነት ከርስዎ መንግሥት ንቁና ለዘብ ያለ ድጋፍ እስካሁን ድረስ ለማግኘት ችሏል" ሲሉ ጽፈዋል ብዙ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል የነበራቸውን ስሜት አሁን ቀዝቀዝ ብሏል:: መንስኤው ወያኔን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከግራቀኝ ከውስጥ እስከ ውጭ ጩሀት ስላበዙበት ለማረሳሳት ሲል ዝም ያለ መሆኑን ሊረዱ አልቻሉም::

ወያኔ ዝም ያለ የመሰለው የሕዝቡን ጩሕት ረገብ ለማድረግ አስቦ እንጂ በትክክል የሕዝቡን ድምጽ ከልብ አዳምጦና ሰምቶ ሳይሆን ግዜ እየገዛ ነው:: የአባቶች አባባል "ያደፈቀን ሠይጣን ሳያቀስ አይለቅም" ይላሉ:: በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ የምወደው በውጭ አገር የተመሰረተው የደንበር ኮሚቴ ሌሎችን ምሁራን እያሰባሰበ መርሃ ግቡሩን አስፋፍቶ ለወደፊቱ በሕጋዊ መንገድ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር እስኪከለል መስራት እንዳለበት አሳስባለሁ:: ወያኔ ለዳር ደንበር ይቆረቆራል ብሎ ማሰብ ፈጽሞ ሊሆን የማይችል መሆኑን መገንዘብ ያሻል:: ወያኔ ከስልጣን ለመቆየት ሲል የማያደርገው ነገር የለምና ነው:: የትግራይን ሕዝብ እያወናበደ ኋላም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀረ ደርግ አቋዋም ስለነበረው አወናብዶ ከሥልጣን የወጣ መሆኑ አይዘነጋም:: ወያኔ የትግራይንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የዓለምን ሕዝብ አጭበርብሮ ከስልጣን ላይ የወጣ ነው::



# ሱዳኖች በጐንደር ድንበር ጥሰው በመግባት የኢትዮጵያን መሬት ማረስ ጀምረዋል

**● የአካባቢው ገበሬዎች በኃይል ርምጃ ተገድለዋል፤ ተፈናቅለዋል**

ከዮቪል

የሕገራችን ያለፈ ታሪክ የጦርነት ታሪክ መሆኑ አሳዝኖን የዛሬ ትውልዶች ነገርችን አስተካክለን፤ የተረጋጋና የሰከነ፤ ውል መሠረቱ ያልጠፋ ታሪክን ለተተኪው ትውልድ ከማስረክብ ይልቅ አሁንም ሌላ የጦርነት ታሪክ ምዕራፍ የሚከፍት ሁኔታ ሲውጠነጠንና በመጭው ትውልድና በዚህች ቅድስት ሀገር የመከራ ቀንበር ሲጫንባቸው እያየን "ጊዜ ይፍታው" ብሎ ማለት ቸል ማለት ተገቢ አይደለም። ይህች ሀገር በሚያሳዝን መልኩ እየተሸራረፈችና ልዕልናዋ እየተጣሰ በምትገኝበት በአሁኑ ሰዓት ትናንት የከፋፍለህ ግዛውንና የተስፋፊነት ፖሊሲዎችን አውጥተውና ጦር ሰብቀው፤ ድንበራችንን ጥሰው፤ የተዳፈሩን የውጭ ኃይሎች በቆራጥ ኢትዮጵያውያን መራራ ትግል የሀፍረት ካባ ደርበው ይመለሱ ዘንድ ግድ ስሆነባቸው ሁሉ ዛሬ ነገሮች ሁሉ እነርሱ እንደሚፈልጓቸው ሆነው የተመቻቹላቸው መስሏቸዋል። ያለምክንያት አይደለም። እንደፈለጉን ሊያደርጉን በሚችሉበት ሁኔታ በመከፋፈልና በመበታተን ላይ ያለን መስሎ ስለሚታይ ነው። በእርግጥም ለብዙዎች ሁኔታው እንዲያ ነው። ብሔራዊ ስሜታችን ላልቶ ኅጠኝነት አጥቅቶናል። የእናት ሀገር ፍቅራችን ቀዝቅዟል። የአንድነት ጥንካሬያችን ላልቷል። ምራላችን የወደቀ ይመስላል። እርስ በርሳችን ስንናቆር ተከብሮ የቆየው በራችን ባለቤት አልባ ሆኖ ይታያል። አብዛኛው ሕብረተሰብ ቀደም ብሎ ባለቀለት የኤርትራ ጉዳይ፤ በሐገር ውስጥ በሚፈጠሩ ግዘናጊያ ክስተቶችና በአስተዳደር ችግር ተወጥሮ ሲታመስ የዳር ሐገሩ ለነገ አስጊ ችግርን በሚፈጥር መልኩ ይገኛል። የዚህን ድርጊት እውነታ ቀጥሎ የምናየው ዘገባ ገሐድ ያሳየናል።

የጎንደር ሕዝብ ከተከዜ መለስ የነበሩት የወልቃይት ጠገዴ፤ የሰቲት ሁመራና ጠለምትን የመሳሰሉትን ለም የቀድሞ ግዛቶቹ በክልል አንድ (በትግራይ) መጠቃለል ሲያጠያይቀው አሁንም ሌላ ውጋት አላጣውም። የአብደራፊ እና የመተማ አካባቢዎችና ሌሎች በጠረፍ የሚገኙ የክልሉ ገጠርና ትናንሽ ከተሞች በሱዳን ቁጃሮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመታረስ ላይ ነው ያሉት። ይባስ ብሎ ከሚያርሱት እርሻ ውስጥ በሰፈረው የሱዳን ጦር ሠራዊት ትንኮሳ የአካባቢው አራሽ ገበሬዎች በቆየ ባድማቸው ላይ መገደልና መቁሰል የሁኔታውን እየከረረ መምጣት የሚያመለክት እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች በሐዘንና በቁጭት ይናገራሉ።

የጦር ኃይል ከጎናቸው በማሰለፍ በሉሚናት፤ በሺመላ ጋራ በደላሉ፤ በሰናር፤ በግራዋ፤ በኩረደም፤ በገላሉባን፤ በአብድዮንና በመካሠሉት ከዳንግመስ እና ሌሎችንም የመተማና የአብደራፊ መሬቶችን የሱዳን ገበሬዎች ከአሥራ ሁለት ያላነሱ ትራክተሮችን በማሰማራት ሰሊጥ ማሽላና ጥጥ የመካሠሉትን ማምረት የጀመሩት ከዛሬ ሦስት ዓመት አካባቢ ኢህአዴግ በአካባቢው እያለ ቢሆንም ተጠናክረው ገፍተው የመጡትና በአካባቢው ነዋሪ ላይ ጉዳት ማድረስ የጀመሩት ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ የገለፁልን በአካባቢው በንግድ ሥራ ተሰማርተው የሚገኙ አባት ናቸው።

እኛም በሱዳኖች ታረሱ ወደተባሉት የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ክልሎች በመንቀሳቀስ ጉዳዩን ለማጣራት በአቅራቢያው የሚገኙ ነዋሪዎችንና የሚመለከታቸውን የመንግሥት አካላት አነጋግረን ነበር።

የአጋጣሚ ነገር ሆነና በግጭቱ ወቅት የቅርብ ተመልካች የነበሩ ግለሰቦችን አገኘን። በግጭቱ ዕለት ስለነበረውና ከዚያም በፊትና በኋላ ስለተፈጠሩት ነባራዊ ሁኔታዎች እንዲያውጉን ጠየቅናቸው። ምንም እንኳን ሁኔታውን ለመንገር ፈቃደኛ ቢሆኑም ስማቸው

እንዲጠቀስ እንደማይፈልጉ ከ
በኋላ ወደ ዋንኛ እርዕሰታችን
"እርግጥ ነው ሱዳኖች የእኛ
በማረስ ላይ ነው ያሉት። "
ንግግራቸውን ከጀመሩ በ
ቀጠሉም "ግጭቱ የተፈጠረው
በአል ሲከበር ሳምንት
ሚያዝያ 3 ቀን 1985 ዓ.ም
ቦታውም በመተማና ሁመራ
በምትገኘው በሺመላ ጋራ
ነበር።

"በሱዳኖችና በእኛ ገበሬዎች
የተፈጠረው አለመግባባት ዋ
ስዔ የእርሻ መሬት ጉዳይ ነው
ከቀን ቀን ሲስፋፉ ከእኛው ገበ
ድረስ መግባት ጀምረዋል። ገ
እንዴት በገዛ ሀገሬ እገፋለሁ ባ
በዚህ አይነት ጥሉ ከጊዜ ጊዜ
ሄደ። አለመግባባት መጣ። እሁ
ዝያ 3 ቀን 1985 ዓ.ም. ከቀ
ሰዓት በሺመላ ጋራ አካባቢ
ወታደሮች አማካኝነት በአ
አራሽ ገበሬዎች ላይ የተ
እርምጃ ግን ከበፊቱ የተለየ ነ
ሬዎቹ በሀገራቸው መሬት በ
ጥይት ተደበደቡ። አራት
ሲሞቱ ሁለት የሚሆኑት ቆሰ
ካባቢው ዘራፊንና ሌባን ለማ
ማርተው የነበሩ የቀበሌ ታጣ
የመከላከያ ሰራዊት አባላት ች
ፈጠረ በኋላ ደረሱ። ወዲያው የ
ካነሱና የቆሰሉትን በመርዳት ላ
ሌሊት ላይ ከመተማ ዮሐንስ
ችግሩ ተሰምቶ ኖሮ የእርሻው
ቶችና አንዳንድ ታጣቂዎች መ
ታው እንደደረሱ ከቅርብ ርቀ
ገኙት የሱዳን ወታደሮች አብ
ከአምስት ደቂቃ ላላነሰ ጊዜ
ይህን ጊዜ የእርሻው ባለቤቶ
ኔታው በመበሳጨት ከአቅራ

-ትን እብሪተኛ የሱዳን ወታደሮችን
ግጠም ቢፈልጉም በቦታው የነበሩት
ህአዴግ አባላት ግጭቱ አስፈላጊ
ዳልሆን ስለገለፁላቸው ሌሊቱን
ውንና ቁስለኞችን በመያዝ ከመተማ
ጋስ የመጡት የኢህአዴግ አባላትና
ለ ህዝቡ ከባለቤቶች ጋር በመሆን
ቶ ነጋሽ ጽዋያ ለምነው ባመጡት
ኡንትሬ መኪና ተመለሱ። ይህን
ሰዓቱ 7:30 ይሆናል። በአካባቢው
ሩ ታጣቂዎች እዚያው እንዲቆዩ
ረገ።

ሚቀጥለው ቀን ሚያዝያ 4 አሁንም
የሱዳን ወታደሮች ከቦታው ባሉት
ቂዎች ላይ ንፍተው በመምጣት
ስ ከፈቱ። በተደረገው የተኩስ ልው
ከዚያኛው ወገን የተፈጠረው
ትወቅም ከታጣቂዎች ውስጥ አንድ
። አቶ በርሔ የተባሉት ታጣቂ
የቆሰሉት። (አቶ በርሔ በመተማ
ስ ተኝተው አሁን ድረስ ሕክ
ምውን በመከታተል ላይ ናቸው።)
ከተፈጠረ በኋላ የክልሉ ሕዝብ
በሌውና በየገበሬ ማህበሩ በተሰበ
ት አጋጣሚ ሁሉ ክላይ የተጠ
ን ግጭት መንስዔ በማድረግ የሱ
ን ከአስራ አምስትና ከሀያ ኪሎ
ር ባላነሰ ሁኔታ ወደ ክልላችን መግ
ውንና ማረሳቸውን በተመለከተና
ጋጋሚ በተለያዩ ቦታዎች በእ
ኝነት የሚፈፅሙት ግፍ በቸልታ
ፍ የሌለበት መሆኑንና በተለይ
ሁለትና ሦስት ዓመት ታይቶ
ታወቅ ደረጃ እየተስፋፋ መምጣ
ን በጥያቄ ቢያቀርቡም የአካ
የመንግሥት አካላት ሀይሀ ጥያቄ
ፀረ-ሰላምና ፀረ-ቻርተር ድር
ቅስቀሳ የተጠነሰሰ ሌላ ሴራ እንጅ
ፍላጎት አይደለም። ሱዳኖችም
ትባለው አልገቡም። ችግር ካለም
ረስ የሚችለው የሽግግር
ሥቱ ነው። ነገር ግን ሁለት ወዳጅ
ሀገሮችን ለማቃረን የሚደረገው
ሉባልታ አግባብ አይደለም" በማ
ማስጠንቀቂያ የተቀላቀለበት
ሰጥተዋል። የሚገርመው በተፈ
ግጭት የተጎዱ የጥበቃ አባላትና

ሀይወታቸውን ያጡ ገበሬዎች መኖራ
ቸው ከአፍንጫ ስር ያለ መረጃ መሆኑ
እየታወቀ ከላይ ያየነውን አይነት መልስ
ተሰጠ።

"የአካባቢው ሽማግሌዎች ጥረታቸ
ውን በመቀጠል በሰላማዊ መንገድ ችግ
ሩን ለመፍታት ሙከራ ቢያደርጉም
የባለሥልጣናትን ትብብር ባለማግኘታ
ቸው ሊሳካላቸው እንዳልቻለ ይናገ
ራሉ። እንዲያውም ሁኔታው ስር እየሰ
ደደና በየጊዜው ግጭቶቹ እየታዩ ከሕ
ዝቡ አቤቱታ ሲቀርብ 'ጥያቄውን እኛ
መመለስ አንችልም! ችግሩን ለበላይ
አካል ስለገፍን መልስ በመጠባበቅ ላይ
ነን' የሚል መልስ ከመንግሥት አካላት
ሲሰጥ አንጅ በተጨባጭ ያየነው መፍ
ትሔ የለም። አንድ ዱካ (በሱዳን ክፍለ
ግዛት) የሚገኝ የሱዳን ኮሎኔል ወደ
አካባቢያችን በመምጣት ከኛ ክፍለ ህዝ
ቦችና ከሠራዊቱ አዛዦች ጋር ሲነጋገር
"ሀይላችን ይወስነናል" በማለት መና
ገሩን ከቦታው የነበሩ ሠዎች ይናገራሉ።

"ንዋሪው ህብረተሰብ ይህን መሰል የሰ
ላምና የእርቅ ጥረቶችን በማድረግ እስከ
አሁን ቢቆይም ከመንግሥት አካላት
ቸል ከመባሉ በተጨማሪ ጥያቄው ሌላ
መልክ ሲሰጠው፤ በሌላ መልኩ ሱዳ
ኖች ቆሮ ከነበራቸው የጦር ሀይል በመ
ጨመርና አራት መድፎችን፤ አየር
መቃወሚያ፤ መትረየሶችን ጭምር
ጦሩን በማስታጠቅ በሚያሳዝን ሁኔታ
በመጠናከር ላይ ናቸው" ሲሉ በዝርዝር
አስረድተውናል።

ይህንና የመሳሰሉትን ቁምነገሮች
በቦታው ተገኝተን ካገኘን በኋላ ወደ
ጎንደር ከተማ እንደተመለስን ስለ ጉዳዩ
የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ስማ
ቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ አንዱ ባለ
ሥልጣን እነጋግረናቸው ሲመልሱ
"ሱዳኖች እንዲህ አይነት እርሻ የሚ
ያርሱት ከበፊት ጀምሮ አንጅ አዲስ
ነገር አይደለም፤ ዘልቀው እየገቡ ደኖ
ችን እየጨፈጨፉ ይወስዱም ነበር።
በተለይ በጦርነቱ ወቅት ትኩረት ስላል
ተሰጠው ሰፊ ቦታ ይዘው ቆይተዋል።
እርግጥ ነው የሱዳን ገበሬዎች አሁን
ድረስ ያርሳሉ። ይህ ሁኔታ በቅርቡ
ግጭት አስነስቶ እንደነበር ይታወሳል።
ግጭቱም የእርሻ መሬትን በሚመለከት

ነበር። በገበሬዎችና በሱዳኖች እርሻ
በሚገኙ ወታደሮች መካከል በተፈጠ
ረው ግጭት ከሁለቱም ወገን ሰዎች
ሞተዋል፤ ቆስለዋል፤ የአካባቢው ገበ
ሬዎች እንደተፈናቀሉ መካድ
አይቻልም። ዋናው ቁምነገር በሁለቱ
ወዳጅ ሀገር ገበሬዎች መካከል የተፈ
ጠረውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመ
ፍታት ጥረት ማድረግ ስለሆነ መፍ
ትሔው በተለያዩ ቦታዎች የገቡ የሱዳን
አራሾች እንዲመለሱ ከእነርሱ ባለሥ
ልጣናት ጋር በተለያዩ ጊዜያት በቲሆና
በመተማ አካባቢ ንግግር ተደርጓል" ሀ
ሲሉ መልሰዋል። በእርሻው አካባቢ
የጦር ካምፕ ከመኖሩ በተጨማሪ የተ
ጠናከረ ሀይልና መሣሪያ የመታየቱ
ጉዳይ አዝማሚያው ችግር አይፈጥርም
ወይ? ብለን ለጠየቅናቸው ሲመልሱ
ሀብመሠረቱ እንደነገርኩህ በተደጋጋሚ
በሠላማዊ መንገድ ነገሩን ለማብረድ
ጥረት በማድረግ ላይ ነው ያለነው። ይህ
የመሣሪያው ጉዳይ ሊሆን የቻለው
በመንግሥት ደረጃ ሳይሆን በግለሰብ
ሀብታሞች ነው። የሱዳን ጦር እንደኛ
ጦር አይደለም፤ ስርዓት የለውም።
ለጥቅም ሲሉ እንኳን ይሄን ሌላ
ያደርጋሉ። በአጠቃላይ ችግርችን ለመ
ፍታት ጥረት እየተደረገ ነው" በማ
ለት አስረድተውናል።

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው የዚህ መን
ግሥት ባለውለታ ጎረቤቶቻችን በማን
አለብኝነት ድንበራችንን እየጣሱ ማረሳ
ቸውንና መስፋፋታቸውን በዝምታ
እንደቀላል ከታለፈና ትንሽ ከቆየ የቅኝ
ግዛት ጥያቄ እንዳይመጣብን ስጋት አለ
ሲሉ አንዳንድ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

መንግሥት የሀገሩን ድንበር የማስ
ከበርና የሕዝቦችን መብት የማስጠበቅ
ኃላፊነት ስላለበት በአራቱም ማዕዘን
ሉአላዊነታችንና የግዛት አንድነታችን
እንዲከበር በአስቸኳይ ጥረት ሊያደርግ
ይገባል። እንደቀድሞዎቹ መሪዎቻችን
ባዕዳን በሚማቸው እንኳን ጥርኝ አፈር
እንዳይወስዱ አስወልቆ ማራገፍ ቢቀ
ርም ድንበር ዘልቀው ሊስፋፉ ቻል
ማለት ጥሩ ውጤት አያመጣምና የሽግ
ግሩ መንግሥት ትኩረት ሊሰጠው
ይገባል።



## ምዕራፍ 6

## በድንበርን ብቻ ከተጻፉት ማስረጃ

<u>ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ</u> ሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓም ገጽ 2 "አሁን ያለውን አጋጣሚ በመጠቀም ይህ ለምና ሰፊ መሬት መሰጠቱን አንዳንድ የዜና አውታሮች በተለይም ሱዳን ትሪቢዩን ጋዜጣ በሰፊው መዘገባቸውን የተከታተልን በሰሜን አሜሪካ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ አቋቁመን በመጀመሪያ ነሐሴ 2 ቀን 1999 ዓም (ኦገስት 8 2007)በአማርኛና በእንግሊዘኛ በተጻፈ ግልጽ ደብዳቤ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ በጉዳዩ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መልስ እንዲሰጡብትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ እንዲያደርጉ ጠየቅን። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስካሁን የሰጡት መልስ የለም። ከዚያም በማከታተል ጥር 10 ቀን 2000 ዓም (ጃንዋሪ 19 2008) በተለያዩ ድኅረ ገጾች ባሰራጨነው ጽሑፍ! ድንበሩን አስመልክቶ አቶ መለስ ዜናዊ ከሱዳን ባለሥልጣናት ጋር ካርቱም መገናኘታቸውና የሁለቱ መንግሥታት ተወካዮች ደግሞ በተባለው ድንበር ደጋግመው መገናኘታቸውን የተሰጠው የድንበር መሬት ከጋንቢላ እስከ ሁመራ እንደሚደርስ ከሱዳን የዜና አውታሮች ያገኘነውን ልዩ ልዩ መረጃ ለመላ አገር ወዳድ አቀረብን" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ በላይ በዚህ አርስት ተጽፎበት የነበረው ስም በቅርቡ ተቀይሯል። አዲሱ ስሙ የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ተብሏል።

ከጋንቤላ እስከ ሁመራ የተባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ ስነሳ ብዙ ሰዎች "ወያኔ መሬት ለሱዳን ሊሰጥ የተዘጋጀ መሆኑን መረጃህ ምንድነው? የምትጽፈው ወያኔን ለማስጠላት ሳይሆን አይቀርም። ደግሞም ጠቅላይ ምኒስትሩ ሆኑ የውጭ ጉዳይ ምኒስትር ጽፈት ቤት ያወጣው መግለጫ የተወራው ውሸት ነው ብሎ መንግሥት እየተናገረ አንተ እንዴት ይህን ልታውጣ አሰብክ" ብለው መክረውኛል። እነዚህን ወዳጆቼን ወያኔ መሬት ሊሰጥ የተስማማ መሆኑን መቼ እንደተጀመረ ከፍ ብሎ የተጻፈውንና መረጃ ይገፔ ለማብራራት ብሞክር ሊሰሙ አላሹም። እንዲያውም እነዚህ ወዳጆቼ "የኢትዮጵያ መንግሥት ሊሰጥ ያላሰበውን አሳሰበህ ኋላ ሱዳኖች የአንተን መጽሐፍ እንደ መረጃ ይዘው ቢከራከሩ አንተ በታሪክ ተጠያቂ ትሆናለህ" ሲሉ ደግመው ደጋግመው ተከራከሩኝ። እነዚህ ወዳጆቼ ሌላው ቀርቶ "የጀርመን ሆነ የአሜሪካ የአማርኛው ሬዲዮ ጣቢያ የተሳሳተ ዘገባ" አቅርቧል ሲሉም እየተናገሩ ነው። ንብረታቸው የተዘረፈባቸው ሰራተኞቻቸው የታሰሩ መሆኑን የጭልጋው አራሽ እንደፋራሽ ደጋግመው ነግረውኛል። ለዚህም ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ምክር ቤቱ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓም "ኢንቨስተሮች ተፈናቅለዋል" ብለዋል። ለዚህም ንግግራቸው አቶ ስዩ ጥሩ አድርገው ቃል በቃል ተችተውታል። ይህን

እርሳቸው የተቹትን ትችት ግማሹን ከዚህ በታች አቅርቤዋለሁ። እኔ የምጽፈው ለቅስቀሳ ሳይሆን በትክክል ታሪክ ጠቅሼ ነው።

አቶ ስዬ አብርሃ አዲስ ነገር ጋዜጣ ቅጽ 1 ቁጥር 32 ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓም "እ. ኤ.አ ከ2001 ጀምሮ የድንብር ኮሚሽን እና አንድ ልዩ ኮሚቴ ማቋቋማቸውን ሰምተናል። ይህ እየተሰራ መክረሙን በይፋ የተነገረን እ.ኤ.አ በ2008 ከሰባት ዓመት በኋላ ነው። ኢሕአዴግ ከፀሄ ኃይለ ሥላሴ እና ከደርግ ወረሰኩት ያለውን የድንበር ጉዳይ ለምን ፓርላማውን እንኳን ሳያሳውቅ ሲሄድበት እንደቆየ አልገለጸልንም። ሰሞኑን የተፈጠረው ሁኔታ ባይፈጠር ኖሮስ ይገልጽልን ነበር ወይ? የሚል ጥያቄም ይጭራል። የድንበር ክለላ የራሱ ሕግ እና ሥርዓት ያለው አንድ መንግሥት እንደ ፈለገ የሚያደርገው ጉዳይ ያለመሆኑ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቢነግሩንም ይፋ ሳይደረግ ለአገሪቱ ፓርላማ እንኳን ሳያሳውቅ ለሰባት ዓመት ሙሉ ሲካሄድ የቆየው ሥራ በምን ሕግ እና ሥርዐት ሲያካሂደው እንደ ቆየ መንግሥት ግልጽ አላደረገልንም። ድንበርን እንደ ገና የማካለሉ ተግባር እንደሚናፈሰው ወሬ ያለቀለት ሳይሆን እየተከናወነ ያለው ወደፊት የወሰን ምልክት ለማስቀመጥ የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራና የሚመለከት ነው ይለናል መግለጫው። ድንበሩን የማካለል ተግባር በውስጡ በቅድም ተከለት የሚሰሩ ሥራዎች አሉትና ሌሎቹ ሳያልቁ ወደ የወሰን ምልክት ማስቀመጥ እንደሚካሄድ ነው። ከዚህ በፊት መሰረት ያለባቸው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መኖራቸውን እውነት ነው።"

"እነዚህ ግን የድንበር ማካለሉ ተግባር አካላት ናቸው። እነዚህን ቅድመ ዝጅግት ያልቾኳቸውን ሥራዎች እየሠራችሁ ከሆነ የሚናፈሰው ወሬ ትክክል ነው ማለት ነው። ችካል መትከል የሥራው የመጨረሻ ምዕራፍ ነው። ይህ ከተሰራ ጉዳዩ አለቀለት ታሪክ ይሆናል ማለት ነው። ነገር ግን ሳያልቅ በፊት ጉዳዩ ይፋ በመውጣቱ ነው ስሕተት ተሰራ የምትሉት?በድብቅ የጀመራችሁትን ሥራ ጨርሳችሁ ነበር ሁሉ ካላቀለት በኋላ መርዶ ነጋሪ አለመሆናቸው እና አስቀድመው ጉዳዩን ይፋ በማድረጋቸው ነው የአሜሪካ ራዲዮ ማዚያ እና የጀምረም ራዲዮ ማቢያ እጅግ አጸያፊ አሉባልታ አናፈሱ ተብለው የተወገዙት መግለጫው እስከ አሁን እየተሰራ ባለው ሥራ አንድም የኢትዮጵያም ሆን የሱዳን ገበሬ አልተፈናቀለም ይለናል። እኛም የሱዳን ገበሬ ተፈናቀለ የሚል ዜና አይደለም የሰማነው። የሱዳን ባለሥልጣናት ራሳቸው ኢትዮጵያ ለሱዳን መሬት መስጠቷን ተናገሩ የሚል ዜና ነው የደረሰን። ሱዳኖች መሬት ተጨምሮላቸው ሲያበቃ እንዴት ተብሎ የሱዳን ገበሬ ተፈናቀለ የሚል ዜና ይጠበቃል? እኛ የሰማነው የኢትዮጵያ ገበሬዎች መፈናቀላቸውን ከዚያም አልፎ በሱዳን መንግሥት መታሰራቸውን ነው። ይህን የሰማነው በጀርመን ራዲዮ እና በአሜሪካ ራዲዮ በኩል በቀጥታ ከሰለባዎቹ አንደበት ነው። ታዲያ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች አይደሉም ማለት ነው ወይስ ሐሰተኛ የሰዎች ድምጽ ነው የሰማነው።"

"አቶ መለስ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓም በፓርላማ ጥያቄ እና መልስ ፕሮግራም ወቅት በዚሁ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ ሲሰጥ ኢንቬስተሮች መፈናቀላቸውን ተናግሯል። እነዚህ ገበሬዎች አይደሉምን? አብዛኛው የዚያ



አካባቢ አራሽ የሚያመርተው ምርት ለገበያ የሚያቀርብ መሆኑ እየታወቀ አቶ መለሰ በአንድ በኩል አንድም ገበሬ አልተተፈናቀለም በሌላ በኩል ደግሞ ኢንቨስተሮች ተፈናቅለዋል ማለቱ እና ኢንቬስተሮችን በገበሬ ምድብ ለማስገባት ያልፈለገበት ምክንያት ለምን ይኸን ኢሕአዴግ ለገበሬው የቆመ ስለሆነ በገበሬው ተፈናቀለ ቢባል የሳቀ ፖለቲካዊ ጉዳት ስለሚያመጣ ጉዳቱን ለመቀነስ ተብሎ ይህን የቃላት ምርጫ ውስጥ የተገባው? ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ ይሁን ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እየተነገረን ያለው የማካለሉ ሥራ እንጻልተከናወነ ነው።"

"ማካለሉ ባልተከናወነበት ሁኔታ ያላችሁበት መሬት የኢትዮጵያ መሬት አይደለምና እና ልቀቁ ብሉ ገበሬዎቹ/ ኢንቬስተሮቹ እንዲነሱ የተደረገው ታዲያ በምን ሐሳብ ነው? ነገሩ ያለቀለት ጉዳይ አይደለም እያላችሁ በሌላ በኩል ደግሞ የሱዳንም ሆነ የኢትዮጵያ ያልሆነ መሬት አለ ብላችሁ ለመለየት እንዴት ቻላችሁ?የትኛውን ቃላችሁ እንውሰድ? አንድም ገበሬ አልተፈናቀለም የድንበር ማካለል ሥራ አልተከናወነም ወይስ ማካለል እየተከናወነ ነው። በዚሁም ምክንያት ኢትዮጵያ መሬት በማስረከቧ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች/ ኢንቬርስተሮች ተነፋቅለዋል የሚባለውን ይህም እንደ ባድመ ለእኛ እንድትሆን ተፈረደልን ዐይነት ጨዋታ ሊሆን ነው እንዴ? ሲሉ" ጽፈዋል።

ግንቦት 7 ድምጽ ሐምሌ 3 ቀን 2000 ዓም "ለሱዳን በተሰጠው መሬት የኢትዮጵያውያኑ ቁጣ እየፈነዳ ነው። ከሁመራ እስከ ጋምቤላ ድረስ ያለውን ርዝመት 1600 ኪሎ ሜትር ስፋቱ ደግሞ 50 ኪሎ ሜትር የሆነውን ለም መሬት የአቶ መለሰ አገዛዝ በድብቅ ለሱዳን መንግስት በመስጠት በአገር ቤትም ሆነ በውጭው ዓለም በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተቀሰቀሰ ቁጣ እያደር እየጋመ ነው" ሲል ጽፏል። የኢትዮጵያና የሱዳን ድንብር ኮሚቴ ደጋግሞ መግለጫ አውጥቷል። መግለጫው በተደጋጋሚ የወጣ ቢሆንም በእጄ ካሉኝ ጥቂቶቹን መግለጫው የወጣበትን ቀንና ወር ለማቅረብ እሞክራለሁ።

1ኛ ጥር 10 ቀን 2000 ዓም
2ኛ ሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓም
3ኛ ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓም
4ኛ ሚያዝያ 18 ቀን 2000 ዓም
5ኛ ግንቦት 2 ቀን 2000ዓም
6ኛ ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓም
8ኛ ግንቦት 30 ቀን 2000 ዓም
9ኛ ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓም
10ኛ ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓም
11ኛ ሕዳር 2 ቀን 2001 ዓም
12ኛ ጥር 14 ቀን 2001 ዓም
13ኛ ጥር 27 ቀን 2001 ዓም

በኢትዮጵያ አንድነት ስም የተደራጁ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶችና በተለያዩ ክፍለ ዓለማት ያሉ ኢትዮጵያውያን መሬት ለሱዳን መሰጠት እንደሌለበት ተቃውመው የአቅዋም መግለጫ አውጥተዋል። አሁንም በእጄ ከሚገኙት ከዚህ

በታች ያሉትን እጠቅሳለሁ። የወጡ መግለጫዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት ሳይሆን በእጄ ያልገቡ እገጅ ብዙ ናቸው።
1ኛ ሐምሌ 26 ቀን 2000 ዓም ሳንሆዜ ካሊፎርንያ
2ኛ ነሐሴ 17 ቀን 2000 ዓም ኮሎምበስ ኦሀዮ
3ኛ 2000 ዓም ሲያትል ዋሽንግተን የጎንደር እድርና መረዳጃ ማሕበር!
4ኛ ጥቅምት 2001 ዓም ከሎንደን
ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓም የወጣው ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ያቀረበው ገጽ 2 "የመለሰ ዜናዊ መንግሥት ከአጤ ምኒልክ እስከ ደርግ የነበሩት መንግሥታት ለሱዳን የሰጡትን መሬት ነው እኛ እያስፈጸምን የምንገኘው ማለቱ ይታወሳል። ይሁንና ከአጤ ምኒልክ እስከ ደርግ የነበሩት የኢትዮጵያ መንግሥታት የአገር ሉዓላዊነትን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና የግዛት አንድነት በተመለከተ ሲቻል በረቀቀ ዲፕሎማሲያዊ መንገድ ሳይቻል ብዙ መስዋዕትነት በመክፈል ድንበሩን ጠብቀውና በአንድ ወቅት በምዕራባውያን ተወስዶ የነበረውን መሬት አስመልሰው ለሚቀጥለው ትውልድ ያስተላለፉ ሲሆን በተለይ ደግሞ የወያኔ/ ኢሕአዴግ መንግሥት ለሱዳን ገጸ-በረከት ለማስረከብ እየተደገሰ ያለውን ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትርና ጥልቀቱ ደግሞ ከ30 እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሆነውን ውሃ ገብ የኢትዮጵያ ለም መሬት ለሱዳን መስጠት ቅድመ-ወያኔ በሆኑ መንግሥታት የማይታሰብ ጉዳይ ነበር። ይልቁንስ ከወያኔ/ኢሕአዴግ በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች ይበልጥ የሚታወቁትና ታሪካቸው ሕያው ሆኖ እስካሁን የቆየው የቱርክ፣የድርቡሾና የሌሎች የኢትዮጵያ ባላንጣዎች በሰሜንና በምዕራብ በኩል ያደረጉትን ጥቃት በራሳቸውና በሕዝባቸው ከፍተኛ መሰዋዕትነት ድንበሩን አስጠብቀው ማቆየታቸው ነው" ሲል መግለጫው ያብራራል።

## በንፋስ ድምጽ ሬዲዮና የቀረበ ጥናት

ሰኔ 1997 ዓም ሁመራ ለሱዳን ሊሰጥ ነው ብለው ቀድመው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተናገሩ ሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም ናቸው። አሜሪካ መጥተው ጎንደሮች ወልቃይቴዎች ከሚበዙበት ኮሎምበስ ኦሀዮ ሕደው "ወያኔ ሁመራን ለሱዳን ሊሰጠው ነው" ብለው ተናግረው ነበር። ሰሚ ግን አላገኙም ነበር። ያሉት አልቀረም ወያኔ ከሁመራ እስከ ጋንቤላ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳን መስጠቱ ርግጠኛ ሲሆን ነው እንደገና ስለደንበሩ ጥያቄ የተደረገላቸው። ግንቦት 2000 ዓም ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምና ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ደንበሩን አስመልክቶ ከቪኦኤ ጋዝጠኛ አዲሱ አበበ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ክልሉን በተመለከተ ወያኔ የሚያደርገውን ቅጥፈት አጋልጠዋል። እንዲሁም ግንቦት 2000 ዓም ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው አሜሪካ በሚተላለፉ የንፋስ ድምጽ ራዲዮ ማለትም ኢትዮጵያዊነትና ነፃነት ለሬዲዮ እንዲሁም በተለያዩ (ፓልቶኮች) በውይይት መድረኮች ደንበሩን አስመልክቶ ቃለ ምልልስ ካደረጉ በኋላ ይህን ታሪካዊና አገራዊ ሰንኛ ለአድማቾችና ለተሰብሳቢዎች አስምተው ነበር።ቃለ ምልልሱንና ንግግራቸውን ሳይሆን ሰንኙ ይህ ነው። ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው!

## ወይ ሀገሬ

(ከሊ.ማ. አበባው ይግዛው፣ ግንቦት 2000 ዓ. ም.)

ሀገሬ ኢትዮጵያ ደጋ፣ ወይና ደጋ፣
ቆላና በረሃ እጅግ ባለጸጋ፣
ወንዞችሽ፣ ሐይቆችሽ፣ ባሕሮችሽ በሙሉ፣
ወራሪ ባልነካው ሀብት የታደሉ፣
በቁምንቁዋ፣ በነሳ ሳይከፋፈሉ፣
ምን አለ በጋራ ለልማት ቢውሉ።

ወይ ሀገሬ ክብሬ ኢትዮጵያዊነቱ፣
ተሸርሽሮ አለቀ፣ ደከመ ጉልበቱ።
አወይ ወገኖቼ፣ ትንሹም ትልቁ፣
የሀገርን ታሪክ፣ ባህል በሚንቁ፣
በጋጠወጦቹ እንዲህ ትሳቀቁ!?

ኸረ አገሬ! አገሬ ራስ-ጋይንት፣ ማማው ደብረ ታቦር፣
የሊቃውንት እምባ፣ የነጋሪት አገር፣
እንዴት በወያኔ፣ ታሪኩ ይደፈር!?
ወይ አገሬ! አገሬ አዲስ ዘመን! በለሳ ቋሊሳ፣ ዘሐጌና መና፣
እንዳላሳደገ ያንን ሁሉ ጀግና፣
ይጫወትበታል የወያኔ ሙና?!
አይ አገሬ! ወይ አገሬ ጎንደር! የፋሲል መዲና፣
የእነ ኢያሱ ዙፋን፣ እንዲህ አረጀና፣
በእነሱም አይጠፉ፣ ሆኖ ሊቀር ወና?!
አገሬ አርማጭሆ! ፊልፊልና ተንፈል!
የጀግኖች መፍለቂያ፣ የጎበዞች ክልል!
እንደምን ይደፈር፣ በምንደኛ ምልምል?!
አይ አገሬ! ወይ አገሬ ደባት! የእነጋተው አገር! አገሬ ወገራ!
አገሬ ወፍ አርግፍ! ወልቃይት ጠገዴ! ደንሻና ሁመራ!
እንዴምን ይደፈር! በትግራ ኩታራ!?

ወይ አገሬ ጭልጋ! ወይ አገሬ ቋራ!
የአባ ታጠቅ አገር፣ የጀግኖቹ ጎራ!
አገሬ አዳኝ አገር! አገሬ መተማ!\
ለኢትዮጵያ አንድነት አካሉ እንዳልደማ፣
እንዴት በወያኔ ታሩኩ ይጋማማ!?

አይ አገሬ! ወይ አገሬ ሰሜን፣ ሰሜን አምባራስ!
የነጋሪት አገር! ባለብዙ ቅርስ!
እንዴት በኩታራ፣ክብሩ ይገሰስ?!
አገሬ ሳሃላ! ወይ አገሬ ፀለምት! አገሬ በየዳ!
ደራሰጌ! ራስ ዳሸን!
እንዴት በወያኔ፣ ድንበርህ ይሸንሸን!?

እረ ጃሎ በሉ! ጎበዝ ጃሎ በሉ!
ምንሽር ወልውሉ! መውዜር አቀባብሉ!
ትናንትን ረስቶ፣ ባንዳው እንዳመሉ!
ተከዜን ተሻግሮ፣ ልግዛ ይላል አሉ!

ወይ አገሬ ሰሜን፣ አገሬ ወገራ!
ለጠገበው ጥይት፣ ለራበው እንጀራ፣
ይህ ነበር ታሪክህ፣ በጣም የሚያኮራ፣
በቁም ሊበላህ ነው የራበው አሞራ።

የሚመነጥረው፣ የሚጠርገው ቢያጣ፣
ጎንደርን እንደልብስ ሊቀደው ጋሬጣ?!
ያ መልቲ ወያኔ፣ ይኸው ልብ አግኝቶ፣
በለስ ቀናውና በቋንቋ አዘናግቶ፣
ወልቃይት ጠገዴን፣ ደንሻና ሁመራን፣ ከጎንደር ለይቶ፣
ሰሊጥ አምርተናል፣ ይበል አፉን ሞልቶ?!
ፅንቋይ* ሲቀባጥር፣ ወልቃይት ልብ በል፣ አርማጭሆም አዳምጥ፣
ትግራይ ያበቅላል ወይ፣ አንድ አገዳ ሰሊጥ?!
ተርቦ ተጠምቶ፣ የሚቀምሰው ሲያጣ፣
ወያኔ ተከዜን፣ ተሻግሮ ሲመጣ፣
ከእንግድነት በቀር፣ መች ነበረው ጣጣ።

እኒያ ደጋጎቹ፣ አገር ዘበኞቹ፣ የሀገሬ ጀግኖች፣
ዘራቸው የት ጠፋ!
አይናውጣው ወያኔ፣ ታሪክ ሲያከረፋ!
ያባቶቹን ርስት፣ ገበሬው ሲቀማ!
ሁመራ ተመርቶ! መቀሌ ሲሰማ!
ምናለ አርማጨሆ?! ምናለ ወገራ?! ይኸንን ሲሰማ?!

ለሰሚው ግራ ነው፣ እንዲህ ያለ ነገር፣
የ አርማጭሆ ሱሪ! የወልቃይት ሱሪ! የወፍ አርግፍ ሱሪ!
መች እንዲህ ነበረ!!!
"ስሜን አርማጭሆ! ወልቃይት ጠገዴ!
ማረሻው ምንሽር! መጎልጎያው ጓንዴ!"
የሚለው ቀረርቶ፣ ውሸት ነበር እንዴ?!
"እንበሳ ተኝቶ፣ ጊደር ሸናችበት፣
ከምን ያለው ጊዜ፣ እኛ ደረሰንበት?!
ያንበሳ ልጅ ሙቶ፣ የጅብ ልጅ ገነነ፣
አሳሳልፍ አለ፣ ጸጉሩ እየበነነ"
ይባል የነበረው፣ እውን እውነት ሆነ?!

* ሰሞን ፅንቋይ ለማለት ነው



ሰሜን አርማጭሆ፣ ወልቃይት ጠገዴ፣
እንዲህ እንደዋዛ፣ ሰሙን ሰወጠ እንዴ?!
ወገራና ሰሜን፣ አርማጭሆም አብሮ፣
ለትግራይ ጉልተኛ፣ ተከዜን ተሻግሮ፣
ገብሮ ያውቃል ወይ?! ቅመም ምጥን ሽሮ?!
የትግሬ ህዝብ ሲራብ፣ ቆርሶ ባጎረሰ፣
መሶብ ቤት ሆነና እጁን ተነከሰ!
ተፈርቶ ተከብሮ፣ ጀግና እንዳልኖረ!
ባይን አውጣ ወያኔ፣ ቤቱ ተደፈረ።
የወልቃይት ጎበዝ፣ የጠገዴ ጀግና፣
ቤቱ ተደፈረ፣ ቀየው ተወረረ፣ ዘመን አረጀና!!!
ያንን ጀግና ትውልድ፣ የኖረ ተፈርቶ፣
እንደምን ይሰለበው?! በቋንቋ አዘናግቶ?!
እየተቀጠረ፣ እንዳልጧጉተበት!
የሁመራን ሰሊጥ፣ ባለቤት ሆነበት?!
ወይ አገሬ! እረ አገሬ! አገር እጥሬው አረም፣ ባገሬ ሲስፋፋ፣
ሁሉም ተዳክመ፣ የሚያርመው ጠፋ!
የጊዜ ጉዳይ ነው፣ እኔ አልቆርጥም ተስፋ!
አገሬ ነው የሚል፣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣
ጥቃቱ ይሰማው፣ ሲቆረስ አካሉ!

ወይ አገሬ! እረ አገሬ!
ለሱዳን ሲከለል፣ መሬቱ ተቆርሶ፣
ዘንድሮ አርማጭሆ፣ በወየታው ለቅሶ፣
እንደዚህ ያዜማል፣ መልሶ መላልሶ።
"አረጀ አርማጭሆ! አረጀ አብደራፊ!
ይቀደድ ጀመረ፣ እንደጨርቅ እራፊ!"
አንተ ክፉ ዘመን፣ ነፍስህን አይማረው!
የወንዶቹን አልጋ፣ ትንኙ ወረረው!
የወንዶቹን ማሳ፣ የህዝቡን አጽመ ርስት፣
ሱዳን አርማጭሆን፣ ከብት አሰማራበት!?
ዘብ ሆነን እንዳልኖርን፣ በጠረፍ ጥበቃ!
በራሳችን ሰዎች፣ እንዴት እንጠቃ?!
ገደብ ይበጅለት፣ ይኸ ነገር ይብቃ!

"ከአባቴ ባድማ፣ ፍግ አታፍሱበት!
አሳቱ ቢጠፋ! ረመጡ አለበት!"
ሁመራ መተማ፣ መተማ ሁመራ፣
መች ተደፍሮ ያውቃል፣ በጠላት ወረራ?!
ዛሬ እሰጠቃን እንጅ፣ እኩይ ባሳጋራ!

ሱዳንስ ያውቀናል፣ በቅርቡም በሩቁ፣
ይብላን ለነሁሱ፣ ለነትግል ብርቁ!!!
ከዛሬ በስተቀር፣ ነገን ለማያውቁ!

"ውሽልሽል ነው! ውሽልሽል ነው እርቁ!
አውድማው ይለቅለቅ! በሮቹም አይራቁ!
እንኳን ከቀያችን! ሱተት ብሎ ገብቶ!
ከሩቁ ያውቀናል፣ ሱዳን መች ዘንግቶ!
የጀግኖቹን ቀየ፣ የህዝቡን አጽሙ-ርስት፣
እንዴት እናያለን፣ ሱዳን ሲኮሰበት!?

"የትግራይ ምንደኞች፣ እየተሳሳቡ፣
ግዙን ብንላቸው፣ ሲሸጡን አሰቡ!
ኢትዮጵያዊ ስማ! ልብህ አያመንታ!
መሀል ዳር ይሆናል! ዳሩ ከተፈታ!"

<u>ቀረርቶ፡</u> ኧረ ቀሉብን! ኧረ ፈጩብን!
እንጠብቃልን እስኪያቦኩብን!
ከዋለ ካደረ፣ አይሰማ የለ!
ድርቡሽ እንደገና፣ ቋራን እቃጠለ!?
የአርማጭሆን መሬት፣ ድርቡሽ ተካፈለ?!
ማሕበረ-ስላሴን፣ ገዳሙን ከሰለ!?

ምን ትጠብቃለህ?! ከወያኔ መንጋ?!
አካልህን ሲያፈርሰው፣ እንደ ደዌ ስጋ?!
ሰሜን አርማጭሆ፣ ወልቃይት ጠገዴ፣ አርግዟል! አርግዟል!
አልተገላገለም! ገና ምጥ ተይዟል!
ፈራን አላልናቸው?! አርዱን አላልናቸው?!
እነርሱን እንደዚህ፣ ምን አስቀዘናቸው?!
ለሱዳን ጥብቅና፣ ማነው ያቆማቸው?!
"ተሳላ ነው አገር! ተሳላ ነው! ይጓዛል እንደ ሰው!
በየበሩ ቆሞ! ጀግና ታልመለሰው!!!"



## ምዕራፍ 7

## የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ የድምጽ ሁኔድ

የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ መግለጫ ከዚህ የሚከተለውን ከተለያዩ የዜና አውታር አጠራቅሞ ያወጣው ሲዲ ክር ላይ የተወሰደ ነው:: ኢሕአዴግ በምስጢር የሰጠውን የኢትዮጵያን ግዛት በማስመልከት ባለፉት ወራቶች ሲዘግቧቸው የነበሩትን ተጠናክሮ ቀርቧል:: ይህ ታሪካዊ መረጃ ይሆን ዘንድ በጥሞና እንዲያዳምጡትና ላልሰሙት እንዲያሰሙ እንጠይቃለን:: የጀርመን ራዲዮ ጋዜጠኛ ተክሌ የኋላ ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞች ተጋድሎ በንጉስ ነገስቷ ድፕሎማሲ ጥረትና በብርታንያም የጦር መሳርያ እርዳታ በፋሽስት ኢጣልያን ላይ ድል ተቀናጅታ አጤ ኃይለ ሥላሴ በክብር ተመልሰው ወደመዲናቸው አዲስ አበባ የገቡበት 67ኛው የድል በዓል ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ታስቦ ውሏል::"

"አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእንግሊዝ ሀገር የስደት ኑሮ በሱዳን በኩል አቋርጠው የድል ጉዞ ሲጀምሩ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ ያደረጉት ጎጃም ውስጥ በቀድሞው የመተከል አውራጃ አሁን ቢሬሻንጉል ግሙዝ በሚሰኘው መስተዳደር ድንበር ላይ በምትገኘው ከተማ ኦሜድላ ላይ ነበር:: ያ የኢትዮጵያ አጽመ እርሰት እውነት ለባዕድ ተሰጥቶ ይሆን? ከሁመራ እስከ ጋምቤላ 1600 ኪሎ ሜትር ከ30 እስከ 50 ያህል ዘልቆ የሚገባ የኢትዮጵያ ለም መሬት በኢሕአዴግ መንግሥት ለሱዳን መስጠቱም ሆነ የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ በሕዝብ ስም ተቃውሞ በማሰማት ላይ ያለ የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰኘ ድርጅት ለዶቼቨሌ ማብራሪያ ሰጥቷል::"

"ኮሚቴው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያሰማው የማስጠንቀቂያ ድወል ዳሩ ማህል ሲሆን ማህሉ ዳር ይሆናል የሚል ነው:: ይህ አስደንጋጭ መግለጫ የሚሰማው በወጣትነት ዘመናቸው በሱዳን በኩል የግብጽንና የቱርክን ተስፋፊዎች እስከ ሰናር አውራጃ ድረስ በመዝመት ያስተዳደሩት አባ ታጠቅ ካሳ አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በወደቁ 140ኛው ዓመት እንዲሁም አባ በዝብዝ አጤ ዮሐንስ ዳር ደንበር ለማስከበር መተማ ላይ በተሰየፉ 119ኛው ዓመት ነው:: አሁን በቅድሚያ አካባቢውን የሚያውቁ አንድ እማኝ እናዳምጥ:: አቶ ፋሲል ሰንደቄ እባላለሁ ንዋሪነቴ በጎንደር ከተማ ሲሆን ለስራ አሁን ችግሩ በተከሰተበት አካባቢ ወደ መተማም ወደቋራም ወደታች አርማጭሆም ለስራ እንቀሳቀሳለሁ ሊመግብ ይችላል ተብሎ የተተነበየለት ከሁመራ እስከ ቋራ ድረስ ከታችም እስከ ጋንቤላ ድረስ ያለበት የኢትዮጵያ እምቅ ሀብት ያለበት በጣም አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ እወክላለሁ የሚል መንግስት

ምዕራፍ 7

## የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ የድምጽ ሠነድ

የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ መግለጫ ከዚህ የሚከተለውን ከተለያዩ የዜና አውታር አጠራቅሞ ያወጣው ሲዲ ክር ላይ የተወሰደ ነው። ኢሕአዴግ በምስጢር የሰጠውን የኢትዮጵያን ግዛት በማስመልከት ባለፉት ወራቶች ሲዘግቧቸው የነበሩትን ተጠናክሮ ቀርቧል። ይህ ታሪካዊ መረጃ ይሆን ዘንድ በጥሞና እንዲያዳምጡትና ላልሰሙት እንዲያሰሙ እንጠይቃለን። የጀርመን ራዲዮ ጋዜጠኛ ተክሌ የኋላ ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞች ተጋድሎ በንጉሰ ነገስቷ ድፕሎማሲ ጥረትና በብርታንያም የጦር መሳርያ እርዳታ በፋሽስት ኢጣልያን ላይ ድል ተቀናጅታ አጤ ኃይለ ሥላሴ በክብር ተመልሰው ወደመዲናቸው አዲስ አበባ የገቡበት 67ኛው የድል በዓል ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ታስቦ ውሏል።"

"አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእንግሊዝ ሀገር የስደት ኑሮ በሱዳን በኩል አቋርጠው የድል ጉዞ ሲጀምሩ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ ያደረጉት ጎጃም ውስጥ በቀድሞው የመተከል አውራጃ አሁን ቢሬሻንጉል ግሙዝ በሚሰኘው መስተዳደር ድንበር ላይ በምትገኘው ከተማ ኦሜድላ ላይ ነበር። ያ የኢትዮጵያ አጽመ እርስት እውነት ለባዕድ ተሰጥቶ ይሆን? ከሁመራ እስከ ጋምቤላ 1600 ኪሎ ሜትር ከ30 እስከ 50 ያህል ዘልቆ የሚገባ የኢትዮጵያ ለም መሬት በኢሕአዴግ መንግሥት ለሱዳን መሰጠቱም ሆነ የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ በሕዝብ ስም ተቃውሞ በማሰማት ላይ ያለ የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰኘ ድርጅት ለዶቼቨሌ ማብራሪያ ሰጥቷል።"

"ኮሚቴው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያሰማው የማስጠንቀቂያ ድወል ዳሩ ማሀል ሲሆን ማሀሉ ዳር ይሆናል የሚል ነው። ይህ አስደንጋጭ መግለጫ የሚሰማው በወጣትነት ዘመናቸው በሱዳን በኩል የግብጽንና የቱርክን ተስፋፊዎች እስከ ስናር አውራጃ ድረስ በመዝመት ያስተዳደሩት አባ ታጠቅ ካሳ አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በወደቁ 140ኛው ዓመት እንዲሁም አባ በዝብዝ አጤ ዮሐንስ ዳር ደንበር ለማስከበር መተማ ላይ በተሰዋ 119ኛው ዓመት ነው። አሁን በቅድሚያ አካባቢውን የሚያውቁ አንድ እማኝ እናዳምጥ። አቶ ፋሲል ሰንደቄ እባላለሁ ንዋሪነቴ በጎንደር ከተማ ሲሆን ለስራ አሁን ችግሩ በተከሰተበት አካባቢ ወደ መተማም ወደቋራም ወደታች አርማጭሆም ለስራ እንቀሳቀሳለሁ አካባቢው የመሰረተ ልማት ሁኔታዎች ቢስፋፉለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊመግብ ይችላል ተብሎ የተተነበየለት ከሁመራ እስከ ቋራ ድረስ ከታችም እስከ ጋንቤላ ድረስ ያለበት የኢትዮጵያ እምቅ ሀብት ያለበት በጣም አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ እወክላለሁ የሚል መንግስት

ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን መሬት ከተሰጠ ይመጣል መከራ ገጽ 127

ምዕራፍ 7

የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ የድምጽ ሠነድ

የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ መግለጫ ከዚህ የሚከተለውን ከተለያዩ የዜና አውታር አጠራቅሞ ያወጣው ሲዲ ክር ላይ የተወሰደ ነው። ኢሕአዴግ በምስጢር የሰጠውን የኢትዮጵያን ግዛት በማስመልከት ባለፉት ወራቶች ሲዘግቧቸው የነበሩትን ተጠናክሮ ቀርቧል። ይህ ታሪካዊ መረጃ ይሆን ዘንድ በጥሞና እንዲያዳምጡትና ላልሰሙት እንዲያሰሙ እንጠይቃለን። የጀርመን ራዲዮ ጋዜጠኛ ተክሌ የኋላ ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞች ተጋድሎ በንጉሰ ነገስቷ ድፕሎማሲ ጥረትና በብርታንያም የጦር መሳርያ እርዳታ በፋሽስት ኢጣልያን ላይ ድል ተቀናጅታ አጤ ኃይለ ሥላሴ በክብር ተመልሰው ወደመዲናቸው አዲስ አበባ የገቡበት 67ኛው የድል በዓል ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ታስቦ ውሏል።"

"አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእንግሊዝ ሀገር የስደት ኑሮ በሱዳን በኩል አቋርጠው የድል ጉዞ ሲጀምሩ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ ያደረጉት ጎጃም ውስጥ በቀድሞው የመተከል አውራጃ አሁን ቢሬሻንጉል ግሙዝ በሚሰኘው መስተዳደር ድንበር ላይ በምትገኘው ከተማ ኦሜድላ ላይ ነበር። ያ የኢትዮጵያ አጽመ እርስት እውነት ለባዕድ ተሰጥቶ ይሆን? ከሁመራ እስከ ጋምቤላ 1600 ኪሎ ሜትር ከ30 እስከ 50 ያህል ዘልቆ የሚገባ የኢትዮጵያ ለም መሬት በኢሕአዴግ መንግሥት ለሱዳን መሰጠቱም ሆነ የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ በሕዝብ ስም ተቃውሞ በማሰማት ላይ ያለ የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰኘ ድርጅት ለዶቼቨሌ ማብራሪያ ሰጥቷል።"

"ኮሚቴው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያሰማው የማስጠንቀቂያ ድወል ዳሩ ማሀል ሲሆን ማሀሉ ዳር ይሆናል የሚል ነው። ይህ አስደንጋጭ መግለጫ የሚሰማው በወጣትነት ዘመናቸው በሱዳን በኩል የግብጽንና የቱርክን ተስፋፊዎች እስከ ስናር አውራጃ ድረስ በመዝመት ያስተዳደሩት አባ ታጠቅ ካሳ አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በወደቁ 140ኛው ዓመት እንዲሁም አባ በዝብዝ አጤ ዮሐንስ ዳር ደንበር ለማስከበር መተማ ላይ በተሰዋ 119ኛው ዓመት ነው። አሁን በቅድሚያ አካባቢውን የሚያውቁ አንድ እማኝ እናዳምጥ። አቶ ፋሲል ሰንደቄ እባላለሁ ንዋሪነቴ በጎንደር ከተማ ሲሆን ለስራ አሁን ችግሩ በተከሰተበት አካባቢ ወደ መተማም ወደቋራም ወደታች አርማጭሆም ለስራ እንቀሳቀሳለሁ አካባቢው የመሰረተ ልማት ሁኔታዎች ቢስፋፉለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊመግብ ይችላል ተብሎ የተተነበየለት ከሁመራ እስከ ቋራ ድረስ ከታችም እስከ ጋንቤላ ድረስ ያለበት የኢትዮጵያ እምቅ ሀብት ያለበት በጣም አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ እወክላለሁ የሚል መንግስት

ልቀቁ አትዋጉ ለምን ከሱዳን ጋር ትጋጫላችሁ በሚል ሕዝቡን የኢትዮጵያን ሕዝቡን አጋዚ ተብሎ የሚጠራው ሠራዊት ከፊት የሱዳን ጦር በመካከል አስገብተው ሕዝቡን አሳሩን እያሳዩት ነው ጌታዬ እና 1600 ኪሎ ሜትር ከሁመራ እስከ ጋንቤላ የሚደርስ መሬት ለሱዳን አሳልፈው ለመስጠት የሱዳን መንግሥት ደግሞ በተቃራኒው ከፖርት ሱዳን ሽሬ ድረስ የሚደርስ የባቡር መስመር እንዲዘረጋ ተስማምተዋል ነው::"

"መረጃዎች እንደሚያሳዩትና ያለው መንግሥት ከሽሬ ድረስ የባቡር መስመር ለመዘርጋት ከሱዳን በኩል ፈቃድ አግኝቷል:: የኢትዮጵያን መሬት ግዛቱን አሳልፎ ለመስጠት ተስማምቷል:: ይህን የተስማሙት በአገሪቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተር የሚመራ የሉዑካን ቡድን አቶ አዲሱ ለገሰ ሁለት ጊዜ በአካባቢው ወደ መተማ መጥተው የክልሉ ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ ዘለቀ የሚባሉ እንዲያውም በአሜሪካ ራዲዮ ግቢያ ሁኔታውን አላውቅም ብለው ሲያስተባብሉ ሰምተናል:: ሌላው የሰሜን ጎንደር ምክትል ዞን አስተዳዳሪ ተሰባስቦ ነው ይህን ስምምነት እንደፈረሙ ሕዝቡ በሚገባ ያውቃል::"

"በመደርጌ በወርቃማ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የሱዳን ጦር ሰራዊት ሰፍሯል:: ከፍተኛ የሆነ ሰዕባዊ መብት እየተካሄደ ነው ያለው! በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥቃት እየደረሰ ነው ያለው:: ቤቶች ተቃጥለዋል! ሰዎች እየታፈኑ ይወሰዳሉ የት እንደሚወሰዱ አናውቅም:: በላይ አርማጭሆ አካባቢ በታች አርማጭሆ አብደራፊ ወረዳ በአብደራፊ አካባቢ በርካታ ቤቶች ተቃጥለዋል:: ሰፋሪው እንዲለቅ ከተደረገ በኋላ ቤቶችን በሙሉ የሱዳን ወታደር ካቃጠለ በኋላ ሕዝቡ ለአቤቱታ ወደ መንግሥ ቢሄድም መንግሥት ግን ካሳ ይሰጣችኋል ምንም የሚያሰጋችሁ ነገር የለም:: ቤታችሁን አስመዝግቡ የተቃጠለባችሁ ካሳ ይሰጣችኋል:: ከሱዳን መንግሥት ጋር ወይም ከሱዳን ሕዝብ ጋር ምንም ዓይነት ግጭት መግባት አይገባም በሚል አሳፋሪ ሁኔታ ሕዝቡ መሬቱን ግዛቱን ተወልዶ ያደገበትን አገር ለቆ እንዲወጣ ነው በመንግሥት በኩል ግፊት እየተደረገ ያለው::"

"አሁንም በሰሜን ጎንደር በዚያው በአብደራፊ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ ጦር ነው ሰፍሮ ያለው:: ሕዝቡ አሁንም አካባቢያችን ለቀን አንወጣም እትብታችን የተቀበረበት አገር ነው:: እነሱ ኢቃጠሉን እናተ ደግሞ ግደሉን በሚል ሕዝቡ አካባቢያችን ለቀን አንወጣም በሚል ጥቃት እየደረሰበት ነው:: በዚህ አካባቢ አሁን የሰፈረው ከሰሜን ጎንደር ከታች አብደራፊ ጀምሮ እስከ ቋራ ከየትኛውም የአማራ ክልል በሰፈራ መልክ ባለፈው አምስት ዓመት መንግሥት አምጥቶ ያሰፈራቸው ገበሬዎች ናቸው::"

"ከዋግምራ ከተለያዩ የወሎ ክፍሎች ከጎጃም ከሰሜን ሸዋ የመጡ ገበሬዎች መንግሥት አምጥቶ አስፈራቸው አሁን ደግሞ ግዛቱን ለሱዳን አሳልፎ በመስጠት ቦታቸውን ለቀው ከመጡ በኋላ አገራቸው ላይ ያለው መሬት ለሌላ ገበሬ ከተሰጠ በኋላ አሁን ደግሞ በዚህ ባሉበት ግዛት ለሱዳን ተሰጥቷል በሚል እጥፍ ድርብ ችግር ነው እየደረሰባቸው ያለው:: ለአይን ምስክርነት



በጎንደር ሆስፒታል ቆስለው መጥተው ሕክምና እየተደረገላቸው ያሉ ገበሬዎች ይገኛሉ:: ተክሌ የኋላ አድማጮቻችን ለሱዳን ሳይሰጥ አይቀርም ለተባለው የኢትዮጵያ መሬት የኢትዮጵያ መንግሥት አቅዋም ምንድነው? በዛሬው እለት ያነጋገርኳቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ቃል አቀባይ አቶ ዋሕደ በላይ በሰነዶች ላይ የተመረኮዘ መግለጫ ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ሊሰጡን ቃል ገብተዋል:: እንጠባበቃለን እንደደረሰን እንስደምጣለን::"

"አሁን ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ጋር የተነጋገረው የዋሽንግተን ዲሲ ዘጋቢያችን አበበ ፈለቀ ያጠናቀረውን ዘገባ እናስከትላለን:: አበበ ፈለቀ የኢትዮጵያ መንግሥት በድብቅ ከሱዳን ጋር ባደረገው ስምምነት መሬት ቆርሶ ለመስጠት እያደረገው ያለው እንቅስቃሴ ባስቸኳይ መቆም እንዳለበት ተጠየቀ:: ተቀማጭነቱ አሜሪካ የሆነው የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ለዶቼቨሌ እንደገለጸው ከሁመራ ጀምሮ እስከ ጋምቤላና ወለጋ ድረስ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳን ለመስጠት እንቅስቃሴ ተጀምሯል:: በዚህም ሳቢያ በርካታ ኢትዮጵያውያን መፈናቀላቸውንና ንብረታቸውም መውደሙ ተጠቁሟል:: ጉዳዩ ዛሬ የተጀመረ አይመስልም:: ሲባል ሲነገር ሲብላላ የቆየ እንጂ ባለፈው ነሐሴ ወር 1999 ዓም የኢትዮጵያ መንግሥት ለሱዳን መንግሥት መሬት ቆርሶ ለመስጠት በድብቅ ማድረጉን አስመልክቶ ግልጽ ማብራሪያ እንዲሰጡ ጠቅላይ ሚንስትሩ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሁለቱም ምክር ቤቶችና ለየግል መንግሥታትና ግልጽ ደብዳቤ መጻፋቸውን ያስታውሳሉ:: ከዚህ አሜሪካ ውስጥ የሚገኙት የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ አባላት ከዚያም ወዲህም በድብቅ ይደረጋል ያሉትን ድርድር ለሕዝብ ይፋ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል:: ኮሚቴው የሕዝብ ግንኙነት ሀላፊ"::

"አቶ ዳንኤል ኀበዜ ጉዳዩ ከድርድር አልፎ መሬት ወደማካለል ብሎም ሕዝብ ወደማፈናቀልና ንብረት ወደማውደም ማምራቱን ገልጸውልኛል:: ችካል በሕቡ መትከል እንደተጀመረና ሕዝቡ ደግሞ ያንን እየነቀለ ሲያነሳ ያለው መንግሥትም ሕዝቡን ራሱን እንዳይከላከል የማገድ ሁኔታ ሁሉ እንደደረሰ ተረድተናል:: ያው ቅርብ ጊዜም ያው ካምፖች ተቃጥለዋል:: ንብረቱ ወድሟል:: ንብረቱ እንዲዘረፍ ሁኗል:: ሲሰሩ የነበሩ ወደ 30 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በሱዳን ተወስደዋል:: የዚህ ችግር ገፈታ ቀማሽ የሆነው ሕዝብ የድረሱልኝ ጥሪ ያሳዘናቸው አቶ ዳንኤል ወደ ሱዳን የተከለለው የኢትዮጵያ መሬት እጅግ ሰፊ መሆኑን ጠቁመዋል:: በአጠቃላይ በኢትዮጵያ አዋሳኝ ያለው መሬት ነው ወደ ሱዳን እየተሰጠ ያለው:: ከሁመራ ጀምሮ እስከ ጋምቤላ ወለጋ ያለው መሬት 1600 ኪሎ ሚትር እርዝመት ያለው መሬት በቋራ ያለው መሬት ከ30 እስከ 50 ኪሎ ሚትር መሬት ይደርሳል:: ከአንዳንድ አካባቢ ደግሞ 30 ኪሎ ሚትር መሬት ስፋት ያለው መሬት ነው:: ሰም መሬት ነው እየተሰጠ ያለው"

"እና አየሀ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያውቀው እንዲያው ምክር ቤቱ ሳያውቀው የኢትዮጵያ መሬት ለባዕድ አገር መስጠት እጅግ አሳስቦናል:: የኢትዮጵያ ሕዝብም ሊናገር አልቻለም እንጂ ራሱን ለመከላከል እንኳን ቢሞክር አጋዚ

በሚባል ሰራዊት እንዳትንቀሳቀሱ እየተባለ ማስፈራሪያ እየተሰጠ ነው:: እና አካባቢው ከደለሎ ጀምሮ እስከ ሱፍ ውሃ አካባቢ ርዝመት ያለው ቦታ ነው በቋራ አካባቢ ያሉትን መሬቶችን ሰባት ገብያ የሚባሉትን አካባቢዎችን እየተሰጠ ነው በዚያ አካባቢ:: የኢትዮጵያ መንግሥት ለሱዳን መሬቱን አሳልፎ የመስጠቱን መነሻ ደግሞ ሱዳን በምላሹ የተቃውሞ ኃይሳትን በግዛቷ እንዳይንቀሳቀስ ቃል መግባቷ መሆኑን አቶ ዳንኤል ኀበዜ ገልጸዋል::"

"የተሰጠው መሬት ሁሉ እነ አጤ ዮሐንስ ሕይዎታቸውን ያሳለፉበት መሬት ነው:: እነ ቴዎድሮስ ገና በሕፃንነታቸው ጀምሮ እየተዋጉ ደንበሩን ሲያስከብሩ የቆዩበት መሬት ነው:: የኢትዮጵያ መሬት ነው:: ኢትዮጵያውያን ለአንድነት ልእዋላዋይነት አብረው በችግር ጊዜ ተባብረው ነው የሚቆሙ አሁን ያለው መንግስት ባድሜ አገራችን ደንበራችን ተወረረ ብሎ ኢትዮጵያውያን እህት ወንድሞቻችን አልቀዋል እና ይህም ደንበራችን ነው:: እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያውቀው በድብቅ መስጠት ከሃዲነት ነው:: በዚህ መሰረት ኮሚቴው ጉዳዩን በቅርብ እየተከታተለ ማጋለጥን እንደ ሚቀጥል ጠቁሟል:: የሱዳን ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ ክልል ገብተው ንብረት ካቃጠሉ ገበሬዎችን ከወሰዱ በኋላ እዚያው እንደሰፈሩና ከውጭ ሄደው ልማት ላይ የተሰማሩን ኢትዮጵያውያን ባለሃብቶችን ጨምሮ የሌሎችን ንብረት መውደኑ አቶ ዳንኤል ኀበዜ ጠቁመዋል:: የሱዳን ወታደር ኢትዮጵያ ካለው መሬት ውስጥ ገብቶ ካቃጠለና አራሾችን ከወሰደ በኋላ የፖሊስ አፊሱን ከፍቷል::"

"ከዚያ ያሉ ገበሬዎች አሁንም ወደ ከተማ ሕደዋል:: ከመንግሥትም ጩኸታቸውን እያቀረቡ የማስፈራራት ችግርም እየገጠማቸው ነው:: ሆኖም ግን ይሄ የአገር ጉዳይ ስለሆነ ንብረቱ ተቃጥሎ እስከ ትራክተሩ ተዘርፎ ሕዶ እንቨስትመንት ያካሄዱ ከውጭ እንኳን ከእስራኤል 4 ዜጋዎች ኢትዮጵያዊ ትውልዳቸው ከአሜሪካ ደግሞ 4 የአሜሪካ ዜጋ የሆኑ ኢትዮጵያውያን እንቨስት ያደረጉ ንብረታቸው ሁሉ ወድሟል:: ይሔ በደለሎና በሱፍ ውሃ በቋራ አካባቢ ባለው እንቨስት ሲያደርጉ የነበሩ ናቸው::"

"ጠቅላይ ሚንስትሩም ሆነ ለተወካዮች ምክር ቤት ብሎም በየደረጃው ለሚገኙት የመንግሥት አካላት ለጻፉት ደብዳቤ እስካሁን ምላሽ አለማግኘታቸውን የገለጹት አቶ ዳንኤል ኀበዜ ሕዝብ ሳያውቀው በድብቅ ገዳሪፍና ካርቱም ላይ በተደረገ ስምምነት መሬት አሳልፎ መስጠቱ እንዲወገድና እንዲቆም ጠይቋል:: የዶቸቬሌ ራዲዮ አበበ ፈለቀ ከዋሽንግተን ዲሲ:: የተከበራችሁ አድማጮቻችን እንደምን አላችሁ ለአለፉት ሶስት ወራት በተከታታ የአዲስ ድምጽ ርዲዮ ከኢትዮጵያ የሚያገኛቸውን መረጃ ለእናንተ እያቀረበ በውጭ አገርም በጉዳዩ ተቆርቁረው የተለያዩ ጹሁፎችን የሚጽፉ ኢትዮጵያውያንን እያቀረበ ለናንተ በሱዳንና በኢትዮጵያ የተፈጠረውን ዳር ደብነር ሁኔታ እንድታውቁ ለማድረግ ሞክረናል:: የዚህ ፕሮግራም ዋና ዓላማ ከዚያ አካባቢ ችግር የደረሰባቸው ኢትዮጵያዊ ችግራቸውን ኢትዮጵያውያን በሙሉ ተረድተን የኢትዮጵያ መንግሥትም ጉዳዩን አውቆ አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው ለማድረግ ነው:: እና ጉዳዩንም በተጨባጭ



ከደረሰባቸው ወይም ጉዳቱ ከደረሰባቸው ወገኖችን እንድትሰሙ ነው የኛ ዓላማ በዚህ መሰረት ዛሬ አቶ ጥላሁን ተድላን ከኢትዮጵያ በቀጥታ አናግራለሁ አቶ ጥላሁን ተድላ ችግሩ ከደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን አንዱ ናቸው::"

"ሁኔታው እንዴት እንደተፈጠረና ምን ሁኔታላይ እንዳለ ያስረዱናል አቶ ጥላሁን ተድላ ጊዜዎትን ወስደው የደረሰበዎትንና በሌሎችም ኢትዮጵያውያን እንቨስተሮችም እንዳሉ ሰምተናል:: የደረሰውን ለማስረዳት ፈቃድዎ ስለሆነ በአድማጮቼ ስም በመላው ዓለም ከልብ አመሰግናለሁ እግዜር ይስጥልኝ አቶ ጥላሁን:: እ እሽ እስቲ ይንገሩኝ ምንድነው የሆነው በእርስዎም ሌሎችም የደረሰባቸው ምንድነው እስኪ ታሪኩን ከመጀመሪያወ ጀምሮ እርስዎ ምንድነው ያልወት ንብረት እዚያ የደረሰብወት ምንድነው በሌሎችስ የደረሰው ምንድነው እንዴት ነው ነገሩስ የጀመረው? ኧ እንግዲህ እኛ በሰሜን ጎንደር ዞን በቋራ አካባቢ ሰንጠረዥ የሚባል ቦታ ኧ ቴዎድሮስ እርሻ ልማት በሚል ስያሜ ከ97 ጀምሮ በእርሻ ላይ እገኛለሁ::"

"ኧ በአሁኑ ወቅት የደረሰው ችግር በአቋቋምኩት የእርሻ ልማት ኧ 2000 ለ2001 የምርት ዘመን ቀደም ሲል እጠቀምበት የነበረውን አራት መቶ ሄክታር መሬት በማጽዳትና ለመዘጋጀት ላይ እያለሁ የሱዳን ጦር ሰራዊት ወደ እርሻው በመግባት ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎችን ዘርፎ ሲወስድ መውሰድ ያልቻለውን ማረሻና ኧ ቁሳቁስ የተለያየ ከማቃጠሉ በተጨማሪ በእርሻው ላይ የነበሩት 8 ሰራተኞቼን በማፈን መውሰድና በአሁኑ ወቅት ያሉበትን ለማወቅ ባለመቻላችን ችግር ውስጥ እንገኛለን:: እህ ይህ የሆነው በዚህ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ነው? አዎ የዛሬ ሁለት ሳምንት አካባቢ ነው:: በ13 ነው በኢትዮጵያ አቆጣጠር እህ አሁን ያለፈው የእርሶ እርሻ የሚገኘው በየት ቦታ ነው ከዚህ ከእርስዎ በፊት ደግሞ በሌሎች አካባቢ ይመስለኛል ወደ አብደራፊ ወደ ሁመራ ወደላይ አካባቢ ተመሳሳይ ችግር እንደደረሰ ነው የምንሰማው:: በአጠቃላይ ችግር ደረሰበት የሚባለው ቦታ እርቀቱ እርዝመቱ ማለት ከ1600 ኪሎ ሜትር ድረስ እንደሚደርስ ነው ዳርዳሩ በሙሉ የምንሰማውና ከእርስዎ በፊት የሆነ ነገር አለ? የዚህ ዓይነት የሰሙት ነገር አለ በሌሎች ቦታዎች?"

"እንግዲህ አብደራፊ ለእኛ እሩቅ ቦታ ነው:: ኧህ ይህ ወሬ ባለፈው ጊዜ የሆነ ግጭት ሕዝቡ ከሱዳኖች ጋራ ተጋጭቷል የሚባል ወሬ ነበረ:: በትክክል ግን ከቦታው አልሄድኩም በወሬ የሰማሁት እኔ የማውቀው በኔላይ የደረሰውን ብቻ ነው:: ኧህ በእኔና በሰራተኞቼና ንብረቴ በነበረበት በትክክል መናገር የምችለው:: እንደሰማነው እርስዎ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች የሌላ አገር ዜጎች ሳይቀር በአካባቢው ቦታ ተመርተው እንደሚሰሩ ነው ካሉ የወዴት የወዴት አገሮች አሉ እርስዎች በምን መልክ ነው መሬቱን ከመንግስት አግኝተው ነው? ሕጋዊ የሆ ባለቤትነት መብት አለዎት? የእርስዎንና የሌሎችን እያጣቀሱ ይንገሩኝ? ሌሎች አንድ 3 የአሜሪካ ዜጎች አሉ::"

"እኔም በዜግነት አሜሪካዊ ነኝ ሁለት እንትን ያው ኢትዮጵያዊነቴን በዚሁ ለዚህ ስራ ያበቃኝ አንዱ እርሱ ነው:: 1 እስራኤላዊ አለ:: 2 ከሳውዲያ

ዓረቢያ የመጡ ባለንብረቶች አሉ። በዚህ አካባቢ 6 ባለሀብቶች በሰፊው 4 መቶ ሔክታር ደረጃ ተሰማርተናል። ሌሎችም በመቶ ሔክታር በ30 ሔክታር በ50 ሔክታር የተሰማሩ ሰዎች አሉ። ይህን የተመራችሁት ከመንግሥት ጋር ተነጋግራችሁ ነው? ሕጋዊ የሆነ የባለቤትነት መብት አላችሁ ሁላችሁም? አዎ መንግሥት በትክክል የሚያስፈልገንን ነገር አዘጋጅቶ ቦታውን በግብርና ኃላፊዎች ተመድቦልን ተለክቶ 15 ዓመት የሊዝ እኔ በእርሻው ላይ ከተሰማራሁ 3 ዓመት ሁኖኛል። አብረን ነው በአንድ ላይ ነው የተቀበልነው ሁላችንም። ሰሞኑን ጉዳዩን እንደሰማሁት ይቅርታ ለመንግሥት እያስረዳችሁ እንደሆነ ነው የምንሰማው አሁን አስረድታችኋል ከመንግሥት ያገኛችሁት ነገር አለ?"

"አዎ ጉዳዩን አስመልክቶ በመሬቱ ለ15 ዓመት የሚቆይ ክራይ ከክልሉ መንግሥት በመውሰድና ለአለፉት አመታት እየተጠቀምኩበት እንደነበር በመጥቀስ የተከሰተውን ችግር ለመንግሥት አካላት እስከ ጠቅላይ ምኒስትሩ ድረስ በጹሑፍ አስታውቄያለሁ አመልክቻለሁ ኸህ መንግስትም ትኩረት ሰጥቶ ምናልባት መፍትሄ እንደሚሰጠን በመጠባበቅ ላይ ነን። በእኛም በኩል እንግዲህ እኛም ይሄን እናንተን ሌሎችንም የምናቀርብበት በትልቁ ለዚህ ጉዳይ በመጀመሪያ መፍትሄ ያመጣል ብለን የምንገምተው መንግሥት ነው። መብታችሁን አስከብሮ ዙሮም ደግሞ ከእናንተም አልፎ የአገሪቱን መሬት ነው መሬቱ እና ያንን ያስከብራል የሚል ተስፋ አለን። በዚህ ምክንያት ነው እንግዲህ ይህን ፕሮግራም በተደጋጋሚ እየሰራን ያለነውና የሚያስተላልፉት መልክት ምንድነው አሁን ለሚያዳምጡዎ ኢትዮጵያውያን ለሚሰሙ የመንግሥት ባለሥልጣን ተወካዮች የእርስዎ መልዕክት በአሁኑ ሰዓት ምንድነው? እንግዲህ እኔ የምለው በኢትዮጵያዊነት ከአንተም ከራስህ ጀምሮ እኔም ስናገር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለታሰሩት ወንድሞቻችን በችግር ላት ላሉት ይሄ የሕይወት ጉዳይ ስለሆነ እኔ ከዚህ ከአሜሪካ ድረስ መጥቼ ይህን ሥራ ስሰራ ባንዴራየን ጥላ አድርጌ መንግሥት አምኜ እንዲሁም ወንድሞቼንና ሰራተኞቼን ኢትዮጵያውያን ደግሞ ያለችኝን ነገር በጋራ ተካፍለን አንዱ በሥራው አንዱ በኃላፊነት አንዱ በምን ተሰማርቶ እንግዲህ ለመስራት ደፋ ቀና እያልነ ሳለ ነው ያ የሆነው።"

"እኒህ ሰዎች እንግዲህ ከመጥፎ ቦታ አልተገኙም። ከስራ በቶ ናው የተገኙት። እና እኔ አደራ የምለው ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለመንግሥትም ሆነ ተባብሮ እነዚህ ሰዎች (ርሊዝ) የሚሆኑበትን ነገርና ከአሉበት ችግር ነፃ እንዲሆኑ ነው እኔ የምማጸነው ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወገን ሕዝቡም መንግሥትም ተባብሮ እኒህን ሰዎች ነፃ እንዲያደርግልኝ እና እያንዳንዱ---ምክንያት ብዙ በሀዘን ላይ የተቸገረ ቤተሰብ አለ። ለዚያም መፍትሄ ያስፈልጋል ያሉበትን እናውቅም። በዚህ በውነቱ ለመንግሥትም በትልቁ እማፀናለሁ። ለምትሰሩት ሁሉ ለእያንዳንዱ ከመንግሥት ጎን ሁናችሁ እንድትረዱን እፈልጋለሁ።"

"በጣም ጥሩ ነው እኛም እንግዲህ ይህን መልዕክት ለሕብረተሰቡ እናደርሳለን። በተቻለ መጠን በዚህም አካባቢ ጉዳዩ አስቆጭቷቸው ራሳቸውን ተቆርቋሪ ኮሚቴ በሚል አቋቁመው የተለያዩ ኢትዮጵያውያን ኳንዳንዶቹ በጣም በዚህ



ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌላም ጉዳይ ላይ ለኢትዮጵያ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ተሰባስበው መንግሥትን እየጠየቁ ነው። ከመንግሥትም አልፎ የሱዳንን መንግሥትን ለማናገር ቅድመ ዝግጅት አላቸው። እና ሰውን በዚህ ጉዳይ ላይ ለማነሳሳት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው። ግን አንዳንድ ጊዜ እርስዎ ነዎት እኔ የደረሰብኝን ለመናገር እንደኛ መብቴም ነው። ሁለተኛ መንግሥትንም ነው እየተማፀንኩ ያለሁት እና የደረሰብኝን ለመናገር ወደ ኋላ አልልም ብለው ቀርበዋል። ከእርስዎም በፊት አንድ ሌላ ሰው አቅርቤ ነበር።"

"አንዳንዶቹ ግን ምናልባት ምናልባት መንግሥትን ያስቆጣብን ይሆናል በሚል ፍርሃት ወደ ኋላ የሚሉ አሉ። እና ይህን በመናገራችሁ በመንግሥት በኩል ምን ተፅዕኖ ያመጣል ብለው ያስባሉ? በዚህ ጉዳይስ መንግሥት ተፅዕኖ እንዳያረግ ወይም ፖለቲካ አድርጎ እንዳያየው ለመንግሥት ለራሱ በቀጥታ የሚያስተላልፉት መልዕክት አለ? እኔ ለዚህ የማፍርበት ነገር የለም። ለምን እኔ አንደኛ ስርዓቱን አምኜ አገሬን ስለምወድና ----ወደ ሀገሬም ስመጣ በደስታ ነው። መንግሥትም ጥሪ አድርጎልኝ ጥሩ መስተንግዶ ተደርጎልኝ --- መንግሥት ለሰጠኝ በጣም የሚያስደስትና የሚያስደንቅ ነው ያጋኘመኝ። እና እኔ ስናገር እኔ ስለፖለቲካ የፖለቲካ ሰው ብሆን ኑሮ በአጠቃላይ ወደዚህ አልመጣም። የፖለቲካ ሰው ወደ ግብርናም አይገባም። እኔ ወደ ልማት እንጂ የፖለቲካውን እንትን አላውቀውም። ስለዚህ ይሄ ወደ ፖለቲካ የሚዞር ነገር አይደለም። ይሄ እኔ አሁን የምናገረው በትክክለኛ መንግሥትም አምኖበት በሰጠኝና (እስታፕሊሽ)ባደረኩበት ቦታ ላይ ከንብረቱ በላይ የሰዎቹ ሕይወት ትልቅ ግምት ተሰጥቶት ሰዎቹ እንዲወጡ እንጂ ነገሮቹን ያው እንግዲህ ይህን ሥለተናገርኩኝ ወደ ፖለቲካ ይዞራል ብዬ አላስብም። መንግሥትም በዚህ መልኩ እንደማያስብ እርግጠኛ ነኝ። አቶ ጥላሁን ለሰጡን ማብራሪያ በጣም አመሰግናለሁ። ወደፊትም እንዲሁ እየደወልኩ እጠይቅወታለሁ። ሁላችንም ከእርስዎና ከሌሎች እንደርስዎ ካሉ ኢትዮጵያውያን ጎን ቁመን የእናንተ መብት እንዲቀበር ለማድረግ ጥረት እናደርጋለን እግዜር ይስጥልኝ አቶ ጥላሁን።"

"የኢትዮጵያ መንግሥት በምዕራባዊ ኢትዮጵያ ሱዳን ደንበር አካባቢ የኢትዮጵያ ይዞታ የነበረ መሬት ብዙዎች ባላወቁት ሁኔታ ለሱዳን አስረክቧል የሚለውን ዜና የሱዳን መንግሥት ባለስልጣናት አረጋገጡ። በአለፈው ዓመት ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓም የምስራቃዊ ሱዳን ጠቅላይ ግዛት አል ገዳሪፍ አስተዳዳሪ አብዱረህማን አልኪዲር በዚያው እለት የተሰበሰበ የሱዳንና የኢትዮጵያ የጋራ ኮሚቴ 17 የኢትዮጵያ መንደሮች ለሱዳናውያን የማስረከብ እርምጃውን ይጀምራል ብለው ካስታወቁ ወዲህ የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰኘ የኢትዮጵያውያን ድርጅት በተደጋጋይ የኢትዮጵያ መሬት ለባዕድ መንግሥት ሊሰጥ ነው የሚል የማስጠንቀቂያ መለዕክት ሲያሰማ መቆየቱ ተመልክቷል። ኮሚቴው መሬቱን ለሱዳን ተሰጥቷል ሲል ያወጣውን መግለጫ የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣናትም አረጋግጠዋል።

"በኢትዮጵያ የሱዳን ኢምባሲ አማካሪ ሚስተር ማህመድ ሐሰን ባብኬር ይህ የሁለቱን አገሮች ደንበር ለማካለል በመካሄድ ላይ ያለ ተግባር ነው:: ግን የሱዳን መንግሥት ያገኘው ያተረፈው መሬት ሳይሆን የሱዳን መንግሥት ቦታ የነበረ ነው:: በሁለቱ አገሮች መንግሥታት መካከል ቀጣይነት ያለው የእረጅም ጊዜ ድርድር ሲካሄድ ቆይቷል:: እናም አሁን ነው ይህን ጉዳይ እልባት እንዲያገኝ ያደረገው:: የሱዳን ጦር ሰራዊት ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ገብቶ የኢትዮጵያውያንን የእርሻ መሬት እንዲይዝ ተደርጓል 30 ገደማ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያንን ሱዳኖች አስረው መውሰዳቸው ይነገራልና ለምንድነው ይህን ዓይነት የኃይል እርምጃ የምትወስዱት ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ይህ አሉት ነው እውነት አይደለም:: በፍጹም መልሴም በጣም ግልጽ ነው:: በኢትዮጵያ በኩል የወሰድነው እስረኛ የለም::" ይህ ከዚህ በላይ የተናገሩት ሱዳናዊው ናቸው::"

ይህን ከዚህ የሚቀጥለው ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ናቸው የሚናገሩት:: "በሺህ ዘጠኝ መቶ 7 እንደፈረንጆች አቆጣጠር ደንበሩ ከተወሰነ በኋላ በሺህ ዘጠኝ መቶ 9 ዓም ሜጀር ጌዊይ የተባለው እንግሊዛዊ ደንበሩን አካሏል:: ዲማርኬሽን አድርገዋል:: ሜጀር ጊዊን ያካለሉት ደንበር ስለዚህ በኢትዮጵያና በሱዳን መኀከል ያለው ድንበር (ዴምርት) ብቻ ሳይሆን በስምምነት የተወሰነ ተኳላል:: ዲማርክ ተደርጓል:: ሱዳን ነፃ ከወጣች በኋላ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት ሞያተኞች ተመድበው ጉዳዩን ካጡኑ በኋላ የደረሱበት ድምዳሜ የጌዊን መስመር ተብሎ የሚታወቀው የሻለቃ ጊዌን ያካለሉትን መስመር ከአንዳንድ አካባቢዮች ከሺህ ዘጠኝ መቶ 7 ስምምነት በተሻለ ሁኔታ ለኢትዮጵያ እንደሚጠቅም ነው የተገነዘቡት:: ከዚህ በመነሳት በ1972 እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር በኢትዮጵያና በሱዳን መሀከል በዚህ ጉዳይ ላይ ስምምነት ተደረሰ:: ይሄ ስምምነት 1ኛ የጊዊን መስመርን መቀበል ነው:: 2ኛ ከዳግላሽ ተራራ እስከ ተከዜ ድረስ --አካባቢ የጊዊን መስመርን ተግባራዊ ማድረግ በሁለቱ ወገኖች ዜጎችን እንዳያስናክል ስለሚችል ያ አካባቢ ዳግም እንዲካለል ሪዲማርኬትድ እንዲሆን ሪዲማርኬትድ ከመሆኑ ዳግም ከመካለሉም በፊት የጋራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንዲወስድ ያ እስኪሆን ድረስ ዳግም እስኪካለል ድረስ ሪዲማርኬትድ እስኪሆን ድረስ በይዞታው ያለው ሁኔታ ረግቶ እንዲቀጥል --እንዲጠበቅ የሚል ስምምነት ነው የተፈራረሙት:: ይሄ እንደፈረንጆች አቆጣጠር 1972 ዓም በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥትና በሱዳን በኒሜሪ መንግሥት ወቅት ነው::"

ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ በተናገሩት ላይ ሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደ ማርያም ትክክል አለመሆናቸውን ሲተቹ "ይህንን እንደ (ኮሚኒኬ) ዓይነት ነገር ነው ስምምነት አይደለም:: ለሱም ቢሆን በ1972 ዶክረት ምናሴ ኃይሌ ነበረ መሪው ወይዘሮ ዮዲት አቶ ጌታቸው በቀለ ነበሩ እነዚህ ሰዎች በሕይወት አሉ:: 2ኛው በ1973 ደግሞ ሰጡ የተባለው ከዚያም ውስጥ ጄኔራል ወልደ ሥላሴ በረካ አሉ:: አሰፋ መንገሻ አለ:: መንግስቴ ደስታ አለ:: የእርሱንም መሪው ዶክተር ምናሴ ነበረ:: ከዚያ ላይ ሁላችሁም የምታስታውሱት ይመስለኛል:: በ1972



ላይ የጊዊን መስመር እንቀበላለን የሚል ከዚህ ኮሞኒቲ ውስጥ ነበረ ያም የተደረገው ምናልባት እንደሚመስለኝ ከነታዋ ጥናት ጋር ተያይዞ ነው:: በኋላ ፓርላማ ውስጥ ትልቅ ረብሻ ተነሳ:: ኢትዮጵያም ውስጥ በአጠቃላይ እንዴት መሬት ይሰጣል መሬት ሰጡ አጤ ኃይለ ሥላሴ ተብሎ ነገሩ ቀረ ቆመ:: ያ-- ስምምነት እሱም ራሱ ይህን ያህል ስምምነት የሚባል አይደለም:: አግቲ ቱ አክሴብት ዘቤስክ ዲማርኬሽን ሜድ ባይ ሜጀር ጊዌን) ነው የሚለው:: በኋላ ግን በ1973 እንደገና ዶ/ር ምናሴ በሚመራው ቡድን በሚነጋገርበት ጊዜ እንደአዲስ ጀምረው ኢትዮጵያውያን የሚያርሱትን መሬት ሱዳኒዮች የሚያርሱትን መሬት የሚያጠና ኮሚቴ ይቋቋም የሚል ነው በ1973 ዓም በፈረንጆች አቆጣጠር ያደረጉት ስለዚህ በአጤ ኃይለ ሥላሴ በደርግም የጌዌንን መስመር እንዳለ ከላይ እስከታች እንቀበለው የሚል ስምምነት አልተደረገም::" አሉ ሊቀ ጠበቡቱ::

ይህ ደግሞ የርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ቃል ሲሆን በተቻለ መጠን ቃል በቃል ለመገልበጥ ሞክሬአለሁ ነገር ግን አየር በገዛቶበት አልሰማኝ ያለ ቃላት --- እያደረኩ ትቸዋለሁ "ስለዚህ በተደረገው ስምምነት መሰረት የደርግም መንግሥት ይህ ጉዳይ እንዲጠና ብሎ ወሰነ:: እንዲጠኒና ብሎ ወስኖ ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በጉዳዩ ላይ እውቀት አላቸው ተብሎ የሚገመቱ ፕሮፌሰሮችና ሞያተኞቅችን አሰባስቦ ኮሚቴ አቋቁሞ ኮሚቴው ነገሩን እንዲያጠናው ወሰነ:: ኮሚቴው አጥንቶ ሲያበቃ ለደርግ መንግሥት ሰጥቶ ግምጋሜ 1ኛ የጊዌንን መስመር መቀበል አማራጭ እንደሌለው 2ኛው የጉዌን መስመርን መተግበር በአካባቢው ሕዝብ ላይ ችግር እንዳይፈጥር:: ሕብረተሰቡን ማማከርና ማወያየት እንደሚያስፈልግ ነው ያረጋገጡት::"

አሁን ሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም ሲተቹ "አንድ በግድ መነገር ያለበት ይሄ በዩንቨርስቲው የተቋቋመው ኮሚቴ ጄኔራል ታየ ጥላሁን የአገር አስተዳደር ሚኒስተር የነበረ ጊዜ እርሱ ጠይቆ የተቋቋመው ኮሚቴና 5 ሰዎች የነበሩበት ሲሆን ከነዚህ ከ5 አራቱ አሁንም አሉ:: ወርቁ ተፈራ ብቻ ነው የሞተው:: ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ፕሮፌሰር ብርሃኑ አበበ፣ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደ አረጋይ እና እኔ አለን:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳለው እነዚህ የጉዌንን መስመር መቀበል አለብን ምርጫ የለንም ብለዋል ነው የሚለው ይሄ ፍጹም ከውነቱ የራቀ ነው" ሊቀጠበብቱ::

እርሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ "በመጀመሪያ የነበረው ድርድር ከመቋረጡ ባሻገር በዚሁ አካባቢ ያሉ ከዳግላሽ እስከ ተከዜ ባለው አካባቢ በድንበር ዙሪያ አንዳንድ ግጭቶች በኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይልና በሱዳን መከላከያ ኃይል መካከል አንዳንድ ግጭቶች ነበሩ:: በነዚህ ግጭቶች ምክንያት የሱዳን መከላከያ ኃይል የደንበር አካባቢውን ለቆ ወደውስጥ ገብቶ ነበር:: የሱዳን መከላከያ ኃይል ያንን የደንበር አካባቢ ለቆ ከመውጣቱ ጋር ተያይዞ በአካባቢው የነበሩ የሱዳን እንቨስተሮችና አርሶ አደሮችም ፍርሃት ስለአደረባቸው የሚያርሱትን መሬት ለቀው ሕደው ነበር:: ከጥቂት አመታት በኋላ ይህን ክፍት መሬት ከጥቅም ላይ እናውለው በሚል አንዳንድ

ኢትዮጵያውያን ኩባንያዎችም አርሶ አደሮችም ይህን ሱዳኖች ያርሱት የነበረውን መሬት የተቆጣጠሩበትና የአረሱበት ሁኔታም ነበር የተፈጠረው።"

የአካባቢው ሰው "እኔ አውቃለሁ ቦታውነን መጥተው ሲያርሱት እያስለቀቅነ ቀለም እየቀባን እንጨቱን እንዳቅማችን ስናስለቅቀው ቦታችን ነው አውቀዋለሁ። ይሄ ደንበር የኛ ነው የኛ መሬት ነው መሬቱ የኛ ነው። እነሱ አያውቁትም በፍጹም አያውቁትም መንግሥት አያውቁትም። እኔ የአገሩ ተወላጅ ነኝ። ሱዳን ውስጥ ፍንሻ ከተማ ነዋሪ ናቸው አውቀዋለሁ ስለሚሉት የኢትዮጵያ መሬት ነው የሚናገሩት። ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ "በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የነበረው አለመግባባት እየተስተካከለ ሲሄድ ይህን ችግር ለመፍታት እንደገና ጥናት ሲደረግ ቆይቷል። በተደረገው ጥናት መሰረት የተስማማንባቸው ጉዳዮች አሉ። 1ኛ በአጤ ምኒልክ እንደተፈረመው በአጤ ኃይለ ሥላሴ እንደተፈረመው በደርግ እንደተረጋገጠው ሁሉ የእኛም መንግሥት የጉዊንን መስመር ይቀበላል። ሲቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም "በአጤ ኃይለ ሥላሴ በደርግም የጉዊንን መስመር እንዳለ ከላይ እስከታች እንቀበለው የሚል ስምምነት አልተደረገም።"

"ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ 12ኛ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ይህን የጉዊንን መስመር ተግባራዊ ለማድረግ በሚሰራበት ወቅት ጉዳት እንዳይከተል የጋራ ኮሚቴ ይቋቋማል ያን ጊዜ በተረጋገጠው መስመር መልኩ ከዳግላሽ እስከ ተከዜ ያለው ቦታ ብቻ ሳይሆን ከዛም በታች ያለው ዳግም እንዲካለል ሪዲማርኬሽን እንዲሆን በነዚህ ጉዳዮች ላይ ተስማማን። በነዚህ ጉዳዮች ላይ ተስማምተን የጋራ ኮሚቴ አቋቁመን ጥናቶችን ሲያካሒዱ በአካባቢው ያለው ሕብረተሰብ እንዳይጎዳ ምን መደረግ እንደሚችል ሲወያዩ ቆዩ። --ተጨማሪ ከአንድ ጉዳይ ላይ ለመስማማት ተቻለ። የጉዊን መስመር የትም ይሁን የት የማካለሉ ስራ በሚሰራበት ወቅት አንድ ኢትዮጵያዊ ወይም አንድ ሱዳናዊ ከሚያርሰው መሬት ላይ መፈናቀል የለበትም የሚል ስምምነት ላይ ተደረሰ። እደግመዋለሁ የጉዊንን መስመር ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ተግባር በምንሸጋገርበት ወቅት የጉዊን መስመር ለኢትዮጵያ ይጥቀም ለሱዳን ይጥቀም አሁን በአካባቢው እያረሰ ያለው ሕብረተሰብ አሁን እያረሰው ካለው መሬት ማንም ግለሰብ መፈናቀል የለበትም። የማካለሉን ስራ ከመጀመራችን በፊት በዚህ መርህ ላይ እንስማማ እያፋቀርን በኢትዮጵያ በኩል በሱዳንም በኩል ተቀባይነት አገኘ።"

አቶ ተመስገን "---በዚያን ቀን የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስተር ጉዳዩን ሲያብራሩ አንዳንዱ ሴራ ነው አሉባልታ ነው። ተቀባይነት የሌለው ነው አድርገው ነው ያነሱት። አሉባልታው ምንድነው አቶ ተመስገን ያሉት ያሉት እርሳቸው? ሰዎች መታሰራቸው ነው መፈናቀላቸው ነው ምን ነው አሉባልታው። "አንድም ሰው አልተፈናለቀም ነው ያሉት? እርሳቸውማ እንደዚያ ነው። ተፈናቃዮቹ ከመንግሥት ሊዝ ፈርመው ሲያበቁ ከ97 ዓም ጀምሮ ከዚያ ቆይተው ተፈናቅለዋል። ከዚህ ዋሽንግተን ዲሲ የየሚገኘው የኢትዮጵያ መንግሥት ኢምባሲ ዋና ዲፕሎማትም ሰዎች መታሰራቸውን ከኢትዮጵያ



መሬት መወሰዳቸውንም ተናግረዋል። ከእናንተ ውይይት በኋላ አስደምጠዋለሁ። እሽ አቶ ተመስገን ምንድነው አሉባልታው ያሉት እርሳቸው? አይ ለእኛም በጣም የገረመን ይህ ነው። ይህንን ከተናገሩ በኋላ ----ችግሮች እንዳሉ ነው። እኛም የጠየቅናቸው ችግሮች አሉ ወይ የሉም ነው ችግሮች አሉ በመጀመሪያ አሉባልታ ናቸው አሉና እንደገና አሉባልታ አይደለም ደግሞ በንግግራቸው አረጋገጡ። አድምጫለሁ። በእኛ በኩል---ዋና መሰረታዊ አድርገን ነው ጥያቄውን ያቀረብነው ከዚህ በተጨማሪ ከትውልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነቱ አሜሪካዊ የሆነ እንቬስተር 400 ሔክታር ተሰጥቶት ከዚያ መሬት ላይ መፈናቀሉንና የእርሱ ሰራተኞች የሆኑ 28 ሰዎች አሁን በሱዳን ውስጥ በእስር ላይ እንደሚገኙ የአቀረበውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ ነው። ሰውየውም ሌሎችም በዚህ መንገድ የተፈናቀሉ በአካል የሚገኙና ሁኔታው እንደተከሰተ ያረጋገጡ ስለሆነ አሉባልታውም ሴራውም የት ላይ እንደሆነ ግልጽ አይደለም።"

ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ "ከዚህ ጋር ተያይዞ ሱዳኖች ያነሱት ጥያቄ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ በመሬት ላይ ያለው አሁን ያለው ሁኔታ ይረጋል ነው ውላችሁ ተስማምታችኋል። ይረጋል ብላችሁ ስታበቁ ከአጤ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የማስፋፋቱን ስራም አላቋረጣችሁም። ይባስ ብሎም በ96 በፈረምጆች አቆጣጠር በ96 ዓም በአካባቢው የነበረው የሱዳን ሰራዊት ሲለቅ የሱዳን እንቨስተሮች የሚያርሱት የነበረውን መሬት ወስዳችሁ ለራሳችሁ እንቨስተርና ለውጭ እንቨስተር ሰጥታችኋል። ይህ ትክክል አይደለም ይሄ ነገር መቆም አለበት። እስኪካለል ድረስ የማስፋፋቱ ስራ የሚቀጥል ከሆነ --የሚል ተገቢ ጥያቄ ነበር ያነሱት። ይህን ተገቢ ጥያቄ ለማስተናገድ በኢትዮጵያ በኩል የተወሰደው አቅዋም ምንድነው ከ96 በኋላም ቢሆን በአርሶአደሮች የተያዘው መሬት ከዚህ በፊት እንደተያዘው መቆጠር አለበት የእንቨስተሮች መሬት የግለሰቦቹ ሁለት ሶስትም ኩባንያዎች ስለያዙት እሱንም ልንመልስላቸው እንችላለን።"

"ስለዚህ አንድ የውጭ እንቨስተር እና አንድ የአገር ውስጥ እንቨስተር ይዞት የነበረውና የሱዳን መንግሥት በ96 ዓም የእኛ መከላከያ ኃይል ያፈናቀለውን መሬት ለኢንቨስተሮች እንዲመለስ ከዚያ ውጭ ግን ሱዳናዊ ባልታረሰ መሬት ላይ ካልሆነ በስተረቅ---ኢትዮጵያውያንን አፈናቅለው እንደማያርሱ ስምምነት ተፈፀመ። ሱዳን አገር ያለው ምድር ኢትዮጵያዊ የሚያርሱትን መሬት በሙሉ ለይተናል። ኢትዮጵያውያን ከማያርሱት መሬት ውስጥ ሱዳናውያን ሊያርሱት እንደሚችሉ ተምማምተናል። እንግዲህ--ሱዳኖች እንዲያርሱ ተምማምተናል ባልታረሰ መሬት ውስጥ የምንለው የጊዊን መስመር የሱዳን መሬት ነው ብለው ከዚህ በፊት ካመለከቱበት ቦታ ላይ ነው። ኢትዮጵያውያን በፊት የገጠሙት በኋላ መከላከያ ኃይላችን ሲቆጣጠር የገቡት ከ96 ዓም የያዙት መሬት እንደያዙት ይቆጠራል። አይፈናቀሉም አይፈናቀሉም ብቻ ሳይሆን በሚካለልበት ወቅት ደንበሩ በሚካለልበትም ወቅት አይፈናቀሉም። የሚል ስምምነት ነው የፈረምነው። በማዕከላዊው የሱዳን መንግሥት በኢትዮጵያና በሱዳን መሀከል ስምምነት እንዲኖር ስለሚፈልግ የሱዳን መንግሥት በተግባር

አንዳንድ ሰዎች እንደሚገልጹት የእኔ የእኔ ነው የአንተን እንካፈል የሚል የኢትዮጵያም አቅዋም ተሸከሞን ነው ያደረው:: ይህን ተቀብሉ ነው ያደረው የሱዳን መንግሥት:: ይህን ተቀብሉ በማደሩ ጅላጅልነት ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም:: እንደ እንዝላልነት ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም:: አርቆ አሳቢነት ነው--የጋራ ጥቅምን ማየቱን ያመለክታል::" ብለዋል::

ሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም ሲተቹ "ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲናገር የሱዳን ጠበቃ መስሉ ነው እንጂ በኢትዮጵያ በኩል ያለውን ሁኔታ ወይም ደግሞ የሕግ መብት ለማስረዳት የቀረበ አልመሰለኝም እኔ:: ሱዳኖች ደጎች ናቸው የኳሆች አድርጋችሁ አትዩአቸው እንደዚህ አይነት ነገር ሁሉ አለበት:: እነሱ ለራሳቸው በደንብ አድርገው አጥንተውታል:: እኔ እንኳን የማውቀው ሁለት የፔቸዲ ዲሰርተጅን የሰሩ ሰዎች አሉ:: በዚህ ጠረፍ ላይ" ብለዋል:: ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ "---ምንም በማይታወቅበት ሁኔታ የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን ተሰጠ፤ ኢትዮጵያውያኖች ተፈናቀሉ? ተብሎ የሚነገረው ተረት ተራ ተረት ቢሆን ጉዳት ባልነበረው አንድም የተፈናቀለ ኢትዮጵያዊ የለም:: አንድ አድን የተፈናቀለ ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን አንድም የሚፈናቀል ኢትዮጵያዊ የለም:: አሁን ብቻ ሳይሆን ደንበሩ ሲከለል አንድም የሚፈናቀል ኢትዮጵያዊ የለም::" አሉ::

ጋዜጠኛው "እስኪ ከዚህ ዋሽንግተን ዲሲ ያለው የኢትዮጵያ ኢምባሲ ዲፕሎማቱ ሚኒስትር ሙሌ አገር ፍቅር በተባለ በዚህ አካባቢው ባለው ራዲዮ ቀርበ በተናገሩት ይህን እናድምጥ "ነብስ ገቢያ ላይ ወደዚያ የገቡና የተሰማሩ ሰዎች ይዘው ሕደዋል:: እነዚህ ሰዎች ቁጥራቸው እስከ 28 የሚደርሱ ሰዎች ናቸው:: ከአካባቢው አሁን ባለኝ መረጃ መሰረት ጠይቄ በቀጥታ ያገኘሁት ነገር ነውና የምናገረው እነዚህን ሰዎች አስረዋል ወስደዋል::"
በሱዳኖች ታፍሰው የወሰደው ከታሰሩበት መካከል ጋዜጠኛው በስልክ ሲጠይቃቸውና ታሳሪዮች ሲመልሱ "ከእርሻ ቦታ ነው የመጣነው:: ያው መኪናም 8 ሰዎች ከአንድ መሸሮ የመጣነው:: የትኛው የማን መሬት ነበር የምታርሰው? የብስ ገቢያ ቋራ ወረዳ ይባላል:: ስንት ናችሁ አሁን እስር ቤት ያላችሁ? አሁን ያለነው ያው 2 ሴት 26 ወንድ ነን ያለነው:: ከሴቶቹ አንዷን አቅርብልኝ እኔና አንተ እያወራን ሰው ሳክልኝ እስቲ? እንኳን አሁን ቀን ራሱ ከሴቷ ጋር መገናኘት አንችልም:: አ ለምን? መብታችን በጣም ነው ታፍኖ ያለው! ዱላ ነው እኮ ያለነው ስቃይ ነው በቃ ርሃብ ነው ያለነው!"

ጋዜጠኛው "እስኪ ከዚህ ዋሽንግተን ዲሲ ካለው ድፕሎማቲ ሚስተር ሙሉ አገር ፍቅር የተባለወ የዚህ አካባቢ ራዲዮ ቀርቦ ከተናገሩት ይህን እናድምጥ:: ስለዚህ በደንበር አካባቢ ያሉ መንግሥታት የወረዳ የዞን የክልል በፌደራል ደረጃ ግንኙነት አለን ከሱዳን ጋር በየደረጃው ባሉ መንግሥታት እነዚህን ዜጎቻችን የአለአግባብ ነው የአሰራችሁ መልሱልን በሚል የጋራ ውይይት እያደረጉ ነው ያሉት:: እነሱ ደግሞ ወንጄል ሰርተው ነው ያገኘናቸው ይላሉ:: ኖ ይህ ትክክል አይደለም ከእርሻ ተግባር ላይ ተሰማርተው እያሉ ነው የወሰዳችኋቸው በግድ መልቀቅ መቻል አለባችሁ በሚል ይፋ የሆነም ደብዳቤ



ተጽፏል:: መሬቱ የኢትዮጵያ መሬት ነው:: በአለሃብቶች ተመርተው በኢትዮጵያ መንግሥት ተመርተው በአካባቢው በወረዳው አስተዳደር ወይም በዞኑ አስተዳደር ቦታ ተመርተው የሚሰሩ ናቸው::"

"ለሱዳን ተሰጠ የተባለው የኢትዮጵያ መሬት ድርድሩ ምስጢራዊ ነበር ይላሉ አንድ በስፍራው እንደነበሩ ቃላቸውን ለቪኦኤ ሰጥተዋል:: ማን ይናገር የነበረ ማን ያርጻ የቀበረ እንዲሉ አዛውንቱ ምስጢራዊ ድርድሩ እንዴትና በነማን ተጀመረ ብለንም ጠይቀናቸዋል:: መሪጌታ የሚለውን የማዕረግ ስማቸው በቀር ለጊዜው ወይም እንድንገልጥ ያልፈቀዱት እኚሁ አዛውንት ቋራ ውስጥ ከልጅነት እስከ እውቀት የኖሩና ዛሬም በዚሁ አካባቢ በመምህርነት የሚያገለግሉ ናቸው:: ያወያያቸው ባልደረባችን አዲሱ አበባ ስለ መሬቱ ምስጢራዊ ድርድር ከማውጣታቸው በፊት የኢትዮጵያ መሬት ናቸው ስለሚሏአቸው አካባቢዮች እንዲገልጡለት ነበር የጠየቃቸው መርጌታ ይመልሳሉ:: ከሁመራ አንስቶ ያው ባህረ ሰላም የሚባል ወንዝ አለ ከሁመራ ዝቅ ብሎ አብደራፊ የሚባለው አለ:: አብርሃጅራ የሚባለው አለ:: እነዚህ መንደሮች ናቸው:: እንደ ገና ሙሴ ባንብ የሚባል አለ:: ደለሉ የሚባል አለ:: ሽመለጋራ የሚባል አለ:: የጠረፍ ከተማዎች ናቸው የምጠራልህ ያለሁ:: እሺ መተማ ዮሃንስ መርምያ ወርቅ አምባ ጉንዶ ተራራ ቲሃ ከተማ ሰኳር ተራራ መተርሃት፤ፋዝራ፤አስከኝት ነብስ ገብያ አላጢሽ በርሃ ሽመለ ጃዊ፤ አይማ ወንዝ እነዚህ ሁሉ የታወቁ ከአጤ ዮሃንስ ጀምሮ ከአጤ ምኒልክ እስከ አጤ ኃይለ ሥላሴ አሁንም እስከ ደርግ ድረስ ያው የኢትዮጵያ ከተሞችና የኢትዮጵያ የግመዝ ብሔረሰቦች የሚኖሩባቸው ናቸው::"

"እኔ ትውልዴ ከዚያው አካባቢ ነኝ:: ትምህርቴ በቤጌምድር አካባቢ ያው ተምሬ ልደግና የቅኔ ትምህርት ሆነ የአቋቋም ትምህርት እየተዘዋወርኩ በኢትዮጵያ ያሉትን ስማር የኖርሁ በኃይለ ሥላሴ ጀምሬ እንጂ የተወለድኩ እዚያው ቋራ ነኝ:: እሽ ይቀጥሉ አሁን ከተሞችን እየጠሩልኝ ነበር እሺ:: እነዚያ ከተማዎች ከ20 ከተማዎች በላይ ማለት ጠርቼልሃለሁ የማለት የደንበር ከተማዎች ናቸው:: በመጀመሪያ እኛ 40 ዓመታችን ነው በበዚያው አካባቢ ግን የነበሩት ግና እኛ የምናውቀው ከኃይለ ሥላሴ ከተረከቡ ግና የሚያርሷቸው የነበሩትን ሀብታሞችን በአጠቃላይ የአርማጭሆ ተወላጆችን የኢትዮጵያ ሃብታሞችን ከሁመራ አንስቶ እስከ ቋራ የጠረፍ ከተማዎች ለምሳሌ እን ዋክሹም ነወጠ የተባሉ ሀብታሞች እነ ቢትወደድ አዳነ የእነሱ ቤተሰቦች በአጠቃላይ ሲያርሷቸው የነበሩ ናቸው እነዚያ የአብደራፊ የደለሉ የሽመለጋራ ያልኩን ቦታዎችን ሁሉ የኢትዮጵያ ሀብታሞች ያርሷቸው የነበሩ ናቸው በኃይለ ሥላሴ ጊዜ:: እና እነዚህ ሁሉ የኢትዮጵያ ናቸው ነው የሚሉኝ እርስዎ:: እነዚህ የኢትዮጵያ ናቸው ከሁመራ አንስቶ እስከ ቋራ ድረስ አላጥሽ ተራራ ያለውን አካባቢ 70 ኪሎ ሜትር የገቡ አሉ ሱዳኖች 50 ኪሎሚትር የገቡ አሉ:: በእያቅጣጫው ማለቴ ነው:: በሁመራ አካባቢ ደግሞ 35 ኪሎ ሜትር በአብደራፊ ደግሞ 60 ኪሎ ሜትር በመተማ ደግሞ ነጋዴ ባህር ይባላል እስከ ጭልጋ አውራጃ ማለት ነው:: ማህበረ ሥላሴ ገዳም ታውቀዋለህ አጤ ቴዎድሮስ የተማሩበት እስከዚያ ገብተውበታል::"

"ሱዳኖች አዎ ሱዳኖች! ይሄ በትክክል ነው የምንግርህ! የገቡት ለምንድነው እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ነው? ወይስ በኃይል ነው! እንዴት ነው? እኛ መጀመሪያ ጊዜ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ያን ቦታ ከልለን የአገር ባላባቶችና የአውራጃ አስተዳደሮች ባሉበት ተከልሎ ያን ቦታ የቀድሞውን እናውቅም አሁን የምንግርህ በተጨባጭ ነው:: ስለዚህ አውራጃ አስተዳደሮችም የችልጋ አውራጃ አስተዳደሪ ከቦታው ሕዶ ከልሎ የወሰን ድንጋይ አስፍረዋል:: ስለዚህ አሁን ግን ያለው መንግስት ግና እኛ የህገር ሽማግሌዎችን በ1996 ዓም በእኛ አቆጣጠር በኢትዮጵያ ማለት ነው:: እኛ የተወሰኑ ሰዎች ባላባቶችን ጠርቶ የወሰን ከተማ ከኢትዮጵያና ከድንበር ከተማዎችን ልንከልል ነውና እናንተ ባላባቶችን ተመርጣችኋል ተብለን 1ኛ አቶ አስማማው አድሮ 75 ዓመታቸው 2ኛ አቶ እሸቴ ፈረደ 70 ዓመታቸው ነው:: 3ኛ አባ አረጋዊ ገብረ ሥላሴ የዳስ ነዋሪ ማለትም የአንድ ገዳም ነዋሪ 80 ዓመታቸው ነው:: አቶ ሲሳይ ብርሃኑ 70 ዓመታቸው ነው:: እኔ ሁነን አቶ ስዩም መስፍንና አቶ አዲሱ ለገሰ ጠርተውን ወደ ገዳሪፍ አውራጃ ወይም ወደ ገዳሪፍ ከተማ ተጠርተን ሕደናል::"

"የመተማ ከተማ አስተዳዳሪ አስተባባሪ! ማን ነበሩ ያኔ የመተማው አስተዳዳሪ? አቶ ሙሉዓለም ገድሴ ይባላሉ:: ስለዚህ ከዚያ ሕደን እንዴት ነው ብለው ነገሩን አዲሱ ለገሰ እና ስዩም ያው ግብግብ ተደርጎልነ እኛ ቦታውን መከለል እንፈልጋለን ነዳጅ በዚህ እንዲሔድልነ ከሱዳን ጋር ደግሞ መልካም ወዳጅነት እንድናደርግ እና ምን ይመስላችኋል እናንተ የአገር ሽማግሌዎች ናችሁ ሱዳን ከእኛ መሬት አለው ለሱዳን ልንሰጠው ነው እኛ አጠቃላይ ሳይሆን ነዳጅ እንዲያቀርብልነ መልካም ግንኙነት እንድናደርግ እንደገና ደግሞ ያው የሱዳን ሀብታሞች ከእናንተ ጋር ገብተው እንዲያርሱ እንዴት ይመስላችኋል አሉን:: እኛ በዚያን ወቅት ተበሳጭተን ኢትዮጵያዊነታችን ረስተነው እኛ 150 ብር ነው የሚከፈለን አበል አይሆንም እኛ ይህ የኢትዮጵያውያን ሃብት ነው:: የኢትዮጵያውያን ጠረፍ ነው አትባራ የሚኖር ውሃ በፊሰስ አትባራ ወንዝ ይህ የኢትዮጵያውያን ስለሆነ እኛ አባቶቻችን ሲያርሱት የነበረ ስለሆነ እንዲያው አይመስለንም እኛ እንስማማበትም ብለን አምስታችንም ነገርናቸው:: ከነገርናቸው በኋላ እነዚህ ሰዎች ሻጥረኞች ናቸው:: ጥሩ ሰዎች አላመጣችሁም ብለው ለወረዳው አስተዳዳሪ ተቆጡት:: መልሳቸው በአመጣሃቸው ከሚና መልሳቸው ተብለን ከገዳሪፍ ተመልሰናል::"

"ሌላ ተተካ ታዲያ? ከዚያ በኋላ ሌላ ሽማግሌ ተመርጦ እነሱን የሚደግፉ ሰዎች ከነሱ የሚመስሏቸው አባሎች ተመርጠው ተፈራርመው እንደገና በ97 ዓም ሊሰናከል ቻለ:: ይሔ ሊሰናከል የቻለው 97 ምርጫውን ተከትሎ ነው ሊሰናከል የቻለ እንጂ በዚያን ወቅት ተግባራዊ ሉሆን የቻለ እንጂ ይህ ምስጢራዊ ሰነድ ፊት ነው የተስማሙት:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያውቅ ምስጢራዊ ሰነድ ተስማምተዋል:: ሁኔታው ሊፈጸም ሲል ምርጫው አሰናከለው ነው ያሉኝ እስኪ ከዚያ ላይ ግልጽ ያድርጉልኝ:: አዎ ምርጫውን ተከልቶ ግርግር ሲሆንበት ፈራና ደብቆት ቆየ! ያ የተዳፈነ እሳት አሁን



ተጋጋመና አሁን እንደገና 150 ሺህ የሚሆኑ ገበሬዎች እየተፈናቀሉ በደለሉ በአብደራፊ በሁመራ በቋራ፣በነፍስ ገቢያ፣በሽንፋ አካባቢ ያሉ ገበሬዎች አጠቃላይ እየተፈናቀሉ ኒውሳን ገበሬ በመኪና የማያርሱ ተፈናቅለው ማረሻቸውን ጠቅልለው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል በአለፈው ዓመት:: እናንተ አትሆኑም ተብሉ ከተመለሳችሁ በኋላ ሌሎች ሰዎች ተመርጠው ነበር ብለውኛል እኛ እነዚያ የተመረጡ ሰዎች ምንም አላደረጉም?"

"እነዚያ የተመረጡ ሰዎች ምን እንዳደረጉ ደርሰው የመጡ መሆናቸውን እንጂ ምን እንዳደረጉ አላወቅናቸውም:: ምክንያቱም በስውር ነው የሄዱት በስውር ነው የተመለሱ:: ስለዚህ ያው እንግዲህ:: ተፈርሟል ማለት ነው? ተፈራርመዋል አዎ ያውቃሉ መፈራረማቸውን? አዎ ተፈራርመዋል! ምንድነው የተፈራረሙት! ምንድነው ውለታው! ያውቃሉ? ውለታው ምን መሰለህ አጤ ምኒልክና ኃይለ ሥላሴ አሁንም በደርግ የተዋዋሉት ውል አለ! የጉዌን መስመር ለምሳሌ ከአላጥሽ በርሃ እንስቶ እስከ ምንሃጅር ያለውና አካባቢ እንግሊዛዊው ጄኔራል ጉዌን የቀየሰውን ቦታ ለሱዳን ልንሰጥ ነው ስለዚህ እኛ በኦፊሴል ደረጃ ልንሰጥ ነው የጉዌን መስመር በዚያው ነው የተዋዋሉ:: የጉዌስን ክለላ እንቀበላለን ነው? እንቀበላለን በፊርማ እናፀድቃለን ነው በዚያን ወቅት ኃይለ ሥላሴ እኛ እናውቃለን አላፀደቁም::"

"እንዲያውም ሱዳኖች ቢመጡ የአውራጃው አስተዳዳዊ ቀኛዝማች ማን ነው የሚባል ነበር የዚህ የጭልጋ አውራጃ ሕዶ ጠረፌኛ ነበር የሚባለው ጠባቂ ደንበር ጠባቂ አባሮ ነው የሰደዳቸው እንጂ በዚያን አካባቢ ኃይለ ሥላሴ ፈርመው አልሰጡአቸውም:: እኛ እናውቃለን:: የጉዌን መስመር የቱን የቱን ቦታ ነው ለሱዳን ያደረገው የቱን የቱን ቦታ ነው ለኢትዮጵያ ያደረገው ያውቃሉ? እንደማውቀው እኔ አሁን ነብስ ገብያ የሚባል አለ ነብስ ገብያ ማለት እንግዲያ አሁን ሱዳን የወሰዳቸው ቦታዎች አሉ:: ፋዝራና ማክሰኝት ነብስ ገቢያ መተርሃዲ የሚባሉ ከተማዎች የእኛ ነበሩ አሁን እነሱን ሱዳኖች የሱዳን ጦር ይዟቸዋል::"

"ከ97 ጀምሮ ሊዝ ከመንግሥት ጋር ተፈራርመን ስናርስ ነበር ከዚህ ከምናርስበት ቦታ ነው የተባረርነው ሱዳንም የኔ ነው የምትለው የኢትዮጵያ መንግሥት በሊዝ የሰጠነን ቦታ ነው የሚሉ ሰዎች ባለፈው አነጋግሬ ነበረ ስለነዚህ ቦታዎች እስኪ ይንገሩኝ? እነዚህ ቦታዎች በመጀመሪያ መንግሥት ይህን ነገር ሊሰጣቸው የቻለ እነዚህ ሰዎች ከውጭ የመጡ ሰዎች ናቸው ሁለቱ እስራኤላዊ ናቸው:: አንዱ አሜሪካዊ ነው:: ሌሎች የህገር ባለሃብቶች ነው:: ከነሱ ውስጥ አንዱ አቶ አሊ አብዱ ይገኛሉ::"

"አቶ አሊ አብዱ ተሸላሚ የሁመራ ባላባት ሀብታም ናቸው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሸልመዋቸዋል:: እርሳቸው ነው ዋናው አንደኛው እርሻ የተቃጠለው እርሻ የእርሳቸው ነው:: እነዚህ ቦታዎች ነብስ ገቢያ፣ ነብስ ገቢያ ማለት ደግሞ ቋራ መሃል ነው:: ነብስ ገቢያ ሲባል እናንተ ሩቅ አገር ሁናችሁ ወደመሀል ሱዳን እንዳይመስላችሁ ወደዚህ ወደ ቋራ ከተማ ነው:: ነብስ ገቢያ

የኛ ነው ነብስ ገቢያ ማለት --ፋዝራ እነዚህ ሽመለ ጃዊ አላጥሽ በርሃ የሚባል ብርቅዬ አራዊቶች ያሉበትና የኢትዮጵያ የዱር አራዊት ብርቅዬ ያሉበት ሀገር እና እንዲያውም ለዓለም ብርቅየ የሆኑ ዝሆን፣ አንበሳ፣ ቀጭኔ፣ሰጎን አንቁላል ቀይ ዝንጀሮ፣ ቀይ ጦጣ፣ ትልቁ የዘንዶ ዝርያ ቀይ ተኩላ ያሉበት ወርቅዬ ያሉበት ቦታ ነው አሁን ሱዳን የወሰደው::"

"በትውልድ ኢትዮጵያውያን የሆኑ በዜግነት ደግሞ ከእስራኤል ከአሜሪካ የሆኑ ሰዎችም ነበሩ የሚያውቁት አለ ስለ ሰዎች የሚነግሩኝ ለነገር አለ" አዎ አንዱ አሁን በይሰሞን ተፈቶ መቷል አቶ መሃሪ ተፈቶ መቷል:: ምክንያቱም እሱ 2 ሚሊዮን የሱዳን ፓወንድ ተሰጥቶ ተፈቷል:: ከዚያ አካባቢ ምንድነው ሁኔታው ሰዎቹ ነዋሪው ምን ይላል? ውጊያው እንደቀጠለ ነው ያለው! ውጊያ አለ እንዴ? አዎ ውጊያ አለ በ27 ግንቦት 27 ቀን ከረፋዱ 3 ሰዓት ጀምሮ ሽምቅ ተዋጊዮች እና ሽምቅ ተዋጊዮች የሚሏቸው? የእኛ ሽምቅ ተዋጊዮች ናቸው የእኛ የኢትዮጵያውያን ሁኖ ሽምቅ ተዋጊዮች አካባቢውን የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያውያን ሽምቅ ተዋጊዮች ናቸው::"

"የኢትዮጵያን መንግሥት የሚቀዋወሙ? አዎ ግንቦት 27 ቀን ከረፋዱ 3 ሰዓት ጀምሮ ሽምቅ ተዋጊዮች እና የአብደራፊ ምክትል አስተዳዳሪ አቶ ሽምበል ቻላቸው የሚባለው በግንቦት 27 ቀን ተገኗል:: የቀብራቸው ሥን ሥርዓት ጎንደር መጥምቁ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ግንቦት 30 ከጠዋቱ 2 ሰዓት ተከናውኗል:: ሌላስ በኢትዮጵያውያን በኩል የሞቱ ብዙ አሉ ብዙ አሉ? አዎ አንድ 23-አሁን ችግሩ አገር እየተቆረሰ እኛ መቶ ምሉዮን ሕዝብ ነን እንባላለን ሱዳን 35 ሚሊዮን ሕዝብ አላት።እሱ ከኛ ቦታ ስትፈልግ እኛ ቦታችን እየቆረስን ለሱዳኖች ስንሰጥ ለሚቀጥለው ትውልድስ ምን ሊሆን ነው? ይህን ነገር የኢትዮጵያ ሕዝብ በደንብ እንዲያውቀው ነው የምንፈልገው አሁን እኛ ኢትዮጵያ ተደፍራለች አባቶቻችን ሙተዋል ድሮ እኛ የምምሄደው በመጽሐፉ ነው:: ኢትዮጵያ ታብጽን ሀብ ኢግዚአብሔር እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች አሁን ግን እጇን ተኮርኩማለች" ሲሉ ተናግረዋል::

ይህ ከዚህ በላይ የድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ያወጣው ክር እኔ ቃል በቃል ከድምጽ ወደ ጹሑፍ ስቀይር በተለይ የርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ሆኑ የአቶ ዳንኤል ኀበዜ አንዳንዴ ንግግር እያስቸገረኝ የቀረብኝ ይመስለኛል:: ለወደፊቱ ከዋናው ክር ጋር እስኪመሳከር ድረስ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ሌላው ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ አጤ ምኒልክ ተስማምተዋል ያሉት ትክክል አለመሆናቸውን ከዚህ በታች ያለውን አጤ ምኒልክ ለእንግሊዝ መንግሥት የላኩት ደብዳቤ ለአንባቢያን አቅርቤዋለሁ:: አጤ ምኒልክ ሆኑ አጤ ኃይለ ሥላሴ ብሎም የርዕሠ ብሔር ኮሉኔል መንግሥቱ መንግሥት የተስማሙት ውንድ የለም:: በተለይም አጤ ምኒልክ እንኳን ሊሰጡ ቀርቶ ድንበራቸው የት እንደሆነ ደብዳቤው ያስረዳል:: ይህ ከዚህ በታች ያለው የእርሳቸው ደብዳቤ ሲሆን እኔ ለአንባቢያን እንዳያስቸግር በማለት በዘመናዊ ተብየዋለሁ:: ዋናው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሲሆን ማህተም አለበት:: ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱ ማህተም ያረፈበት በሚቀጥለው ገጽ ይመልከቱ::



ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!

ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ ይድረስ ለወዳጃችን ከንግሥት ቪክቶሪያ፣ የታላቂቱ ብርታንያ የዓየርላድም ንግሥት የሃይማኖት ረዳት የሕንድ ነገሥታት ንግሥት፣ሰላም ለእርስዎ ይሁን:: የከበረች የጤናዎን ደሕንነት በጣም እንጠይቃለን:: በመስከረም 25 ቀን 1883 ዓም የተጻፈ ደብዳቤ ልኬ ነበር:: መድረሱን አላወቅሁም፣ ታላቁ የእንግሊዝ መንግሥት እስከ ዛሬ ድረስ ለኢትዮጵያ መንግሥት ወዳጅ ስለሆነ በመልካም ነገር ሁሉ ማሰቡን እያወቅን እናመሰግናለን:: አሁንም የመንግሥታችን የኢትዮጵያን ድንበር ለወዳጆቻችን ነገሥታት ማስታወቅ ስለወደድን ፅፈንላችኋልና እናንተም በመልካም ልቡናችሁ ትመለከቱታላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

የኢትዮጵያ ድምበር ይህ ነው!

ከኢጣልያ ድምበር ባህር ዳር ካለው ካራፍሊ አንስቶ ወደ ምዕራብ ከዥግራ ሜዳ ይዞ ማሂዮ ሃልይ፣ ዲክሳን ጉራ፣አዲባሮ ይደርሳል:: ካዲባሮ አንስቶ የመረብ ወንዝና ያራተብ ወንዝ መገናኛ ድረስ፣ከመረብና ከአራተብ ወንዝ መገናኛ አንስቶ ወደደቡብ ያትባራ ወንዝ ከባህር ሰቲት ወንዝ መገናኛ ቶማት፣ የሚባል ከተማ ካለበት ይደርሳል:: ከቶማት አንስቶ የገዳሪፍን ግዛት ይዞ ዓባይ ከተማ ካርጎግ ይደርሳል::

ከካርጎግ አንስቶ ነጭ ዓባይና የሶባት ወንዝ መገናኛ ይደርሳል:: ከነጭ ዓባይና ከሶባት ወንዝ መገናኛ አንስቶ የሶባትን ወንዝ ይዞ አርቦሬ ጋላን ጨምሮ ሳምብሩ ባህር ደርሶ ወደ ምስራቅ ቦረኔ ጋላን ይዞ አሩሲን ሁሉ ይዞ እስከ ሶማሌ ድንበር ድረስ ኦጋዴንን ጨምሮ ወደ ሰሜን ተመልሶ አበራውልን ገደቡርሲን ኢሳ ሶማሌን ይዞ አምቦሳ ይደርሳል:: ከአንቦሳ አንስቶ ያሰልን ባህር ጨምሮ የጥንቱ ዜጋችን የመሀመድ ልገፌርን ግዛት ሁሉ ይዞ በባህር ዳር ዳር እየሄደ አራፋሊ ይደርሳል::

ይህንን ዛሬ የያዝኩትን ድንበር ስለጻፍኩ እግዚአብሔር እድሜና ጉልበት ከሰጠኝ የጥንቱን የኢትዮጵያ ግዛት እስከ ካርቱም እስከ ኒያሳ ባህር ጋላ የተባለ ሁሉ ለማቅናት እፈልጋለሁ:: ሺ.400 ዓመት ሙሉ ኢትዮጵያ እንደ ክርስቲያን ደሴት በአረመኔ ባህር ተከቦ ሲኖር ከሩቅ አገር የመጣ መንግሥት አፍሪቃን እንካፈላለን ሲል ዝም ብዬ ማዳመጥ አላስብም::

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እስከ ዛሬ እንደጠበቃት እንግዲህም ወዲህ ይጠብቃታል ያሰፋታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ እንጂ ለሌላ መንግሥት አከፋፍሎ ይሰጣታል ብዬ አልጠረጥርም:: ቀድሞማ የኢትዮጵያ ደንበር ባሕር ዳር ነበር! የኢትዮጵያ ጉልበት ቢያንስ የሚረዳን ክርስቲያን ብናጣ የባሕር ደንበራችን ከእስላሞች እጅ ገባ! የባሕር ዳር ድንበራችንን በጉልበታችን እናገኛለን አንልም:: የክርስቲያን ነገሥታት ክርስቶስ አመልክቶአችሁ የባሕር ዳር ድንበራችንን ትመልሱልናላችሁ:: ባይሆንም ከባሕር ዳር አንዳን አንዳንድ ቦታ ትሰጡናላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: በሚያዝያ 14 ቀን ባዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ፣ በ1883 ዓም!



[illegible]



[illegible]

# ክፍል አራት

## ምዕራፍ 1
## የታሪክ ቅኝት ስለ ወልቃይት

ወልቃይት ወይም ወልቃይቴ ማለት ለአንዳንድ አካባቢ ወይም ደግሞ ይህን የተፈጠረውን ችግር በጥሞና ላልተረዳ ሰው ሁኔታውን ሊያውቅ አይችልም:: ስለዚህ ወልቃይት የትና ከዬት አካባቢ እንደሆነ መንደርደሪያ ላቅርብ:: ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች ወልቅጤንና ወልቃይትን ለይተው የማያውቁ ብዙ አሉ:: ድምጻዊ ሰሎሞን ተካልኝ ኮሎምቦስ አኳዮ ለስራ ጉዳይ ይሄዱና ከአንድ ቡና ቤት ሲገቡ ደስ የሚሉ ሁለት ኮረዳዎች አዩ:: ጨዋታው ደርቶ እያወጉ ሳለ "የት አካባቢ ናችሁ" ብለው ድምጻዊው ጠየቁ:: ኮረዶች "ጎንደር" ይላሉ:: ድምጻዊው "ጎንደር የት" ብለው ሲጠይቁ "ከረዶች ወልቃይት" ብለው ይመልሳሉ:: ድምጻዊ ሰሎሞን ለአንዱ ስልክ ይመቱና "ኧረ ና ሳስተዋውቅህ ሁለት ውልቅጤ ቆንጃጅቶች አግኝቻለሁ" አሉ ተብሎ መሳቂያ ሁነው ነበር:: ለዚህም ነው ወልቃይትና ውልቅጤን ለይተው የማያውቁ ስላሉ ወልቃይት የት እንደሆነ ለማስረዳት ያሰብኩት:: በዚህ ባሳለፍናቸው ዓመታት ውስጥ ብዙ አዳዲስ ታሪክ መጻፍ ጀመረ ወያኔን በጥቅም ሲደግፉ የነበሩ ግለሰቦች የሚጽፉትና የሚናገሩት ታሪክ አዳዲስ መሆኑ አይዘነጋም:: ሌሎች ደግሞ ትክክለኛ ታሪኩን መስመር አሲዘው ያላወቀ እንዲያውቅ ለማድረግ ጥረት አድርገዋል:: እኔ ስለ አንድ ነገር ታሪክ መጻፍ ስጀምር ረዘም ብዬ ታሪክ መሳብ ደስ ይለኛል:: ሁሌም በእኔ እምነት አንባቢያ እንዳይጠራጠር በታሪክ የተደገፈ ሠነድ ማቅረብ እወዳለሁ::

አለቃ ታየ ወልደማርያም <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 16 "ከለው ከሳባ ወደ ምዕራብና ወደ ደቡብ ያለ ያማራ የወልቃይት፣ የጠገዴ ሕዝብ አባት ነው:: ከነዚህም የኢትዮጲስ ልጆች የወንድማማቾቹ ነገድ ሕዝብ ሁሉ በመልካቸውና በቁርበታቸው ይመሳሰላሉ:: ከሌሎች ከአፍሪቃ ሕዝብ ተለይተው በልዩነት የሰው ልጆች ተብለው ይጠራሉ:: እነሀም ሕዝብ የያዙት አገር በጥቅሉ ባባታቸው ስም ኢትዮጵያ ተብሎ ይጠራል:: ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ባላባቶች የሴም ዘሮች 7 ወገን ናቸው:: እርሳቸውም አማራ ትግሬ፣ አገው፣በደው፥አሰግዴ፣ በቅላ፣ሐባብ ናቸው:: በደው አሰግዴ በቅላ ሐባብ እነሀ 3ቱ ነገድ በእስልም ሃይማኖት ገብተው ከወንድሞቻቸው ተለይተው ልዩ ወገኖች ሁነዋል:: አማራ ትግሬ አገው ግን በፊት በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ በሕገ ኦሪት ያመኑ በኋላም በክርስቶስ ያመኑ በየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት የጸኑ ከጥንት ጀምሮ መንግሥት ያልጠፋባቸው ባዕድ ገዥ ያልገባባቸው የእግዚአብሔር ረዳት ያልራቃቸው ሕዝብ ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል::



አለቃ ታየ ወልደማርያም አጻጻፍ የአማራው አባት አሰግዴ ግንዱ ከወልቃይት ጠገዴ አርማጭሆ ከዚያም እያደገና እየሰፋ አማራ ሳይንት ድረስ የደረሰ መሆኑን ገልጸው ጽፈዋል:: ሌላው ደግሞ አለቃ ታየ ደህና አድርገው መልስ የጻፉበት ዋና የሆነው ከየመን ቅዱስ ቁርዓን ዘመናዊ ሁኖ ሲታተም "ሳባ የመናዊት" ናት የተባለውን የታሪክ ሰነድ ጠቅሰው መልስ ሰጥተዋል:: ከዚያም "አማርኛ ቋንቋ የወታደር ቋንቋ ነበር፥በተለይ በአጤ ላሊበላ ዘመን ያደገ ነው ብለው አለቃ አጽሜ ጊዮርጊስ በጻፉት መጽሐፍ ላይ አለቃ ታዬ ወልደማርያም መልስ ሰጥተዋል:: ገጽ 22 "አማርኛ ቋንቋ እንደነበረ በፊተኛው ክብረ ነገሥት ተጽፏል:: ከዚያ ዘመን ውስጥ ከነገሱት አያሌ የነገሥታት ስም ባማርኛ ቋንቋ ነበረ:: ይህም ሲታወቅ ወረደ ነጋሽ፣አግባ ጉም፣ አስጎምጉም፣ለትም ተላተም፣ያደ ጎሽ፣አይዙር፣መራ ተክለ ሃይማኖት በመባላቸው ይገለጣልና ይታያል:: በፊት አማርኛ ቋንቋ ተሌለ ይህ ሁሉ ስም ከምን መጣ? ይህ ሁሉ በግዕዝ፣በትግርኛ፣ የሌለ ያማርኛ ስም ነው" ሲሉ ጽፈዋል:: ከክርስቶስ ልደት በፊት የነገሡትን የአማራ ስሞች ልለፍና ከክርስቶስ ልደት በኋላ የነገሡበትን ዓመት ከዚህ እጽፋለሁ::

1ኛ አግባ 105 ዓም
2ኛ ወሰን ሰገድ 585 ዓም
3ኛ ጉም 725 ዓም
4ኛ አስጎምጉም 730 ዓም
5ኛ ለትም 746 ዓም
6ኛ ተላተም 767 ዓም
7ኛ መራ ተክለሃይማኖት 912 ዓም ሌሎች የአማራ ስሞች ከነገሥታት ታሪክ ውስጥ ያሉ ብዙ ናቸው:: የሩቁ ታሪክ ከላይ የተጠቀሰ ነው:: የቅርቡ ደግሞ አማራዎች ከወልቃይት ወደ አርማጭሆና ደንቢያ ከዚያም ወደ ክምክም ቃሮዳና አልፎም አማራ ሳይትንታ መቃድሾ ድረስ ተስፋፍተዋል:: ከዚሁ ከምክም ሳይርቅ መና መቀጥዋ ትውልዱን ዘር የሚቆጥረው መራ ተክለ ሃይማኖት ነው:: ይህን ታሪክ አገዎችም ያምናሉ:: ለዚህ ጥናት ዋና ሁኖ የቀረበው ደግሞ በአገዎች የተጻፈው መጽሐፍ ይሆናል:: ታሪክ ነውና እገሌ ሲወልድ ብለን መቁጥር የታሪካችን አንዱ መሰረቱ ሲሆን አንዳንዴ መኳንንቶች ሕዝብን ከሕዝብ የሚለዩበት ዘዴ አድርገውት ኑረዋል:: በሌሎች የታሪክ ደራሲያን ዘንድ ደግሞ ከጫፉ ለመድረስ ሲባል ወደ ኋላ ተሕዶ ከግንዱ ይደረሳል ስለዚህ አንድ የታሪክ መጽሐፍ ጠቅሼ ላልፍ ወደድኩ::

ዶ/ር አያሌው ሲሳይ <u>የአገው ሕዝብና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 100 "እረፍተ ድንግል የተባለችው የላስታ ቡግና ሴት ዋግ ውስጥ ወፍላ ከተባለው አገር ልዩ ሥፍራው ፍላና ከሚባለው ቀለምሲስ የተባለውን ባላባት አግብታ ወልደ ጊዮርጊስን ወለደች:: ወልደ ጊዮርጊስ የሹም ዳርጎቴን ልጅ ወለተ ቅዱሳንን አግብቶ ፊልጶስን ላስታ ተሻግሮ ተቅዋመ መርቅን አግብቶ ታዴዎስን፥ታዴዎስ በጌምድር ወርሶ የሀሙስ ወንዝ ባላባት የሆኑችውን ብርሃናዊትን አግብቶ ሊቀ ካህናት መርሀ ክርስቶስን፥ሊቀ ካህናት መርሀ ክርስቶስን ዋድላ ሄዶ ማርያም ስናን አግብቶ መራ ተክለ ሃይማኖትን መራ ተክለ ሃይማኖት ከመናመቀጥዋ ባላባት ሂሩተ አምላክን በአሁኑ ዘመን

የቅዱስ ሀርቤ ገዳም ከሚገኝበት የቀደሞ ስሙ አንደኛ ሩህ ከተባለው አግቡቶ በማምጣት መይራሪን፥ሀርበይን ወለደ" ሲሉ ጽፈዋል። መራ ተክለ ሃይማኖት ራሱ ከአማራ የተወለደ ሲሆን ትግሬዋን ሞሰበ ወርቅን ከማግባቱ በፊት ከአማራው ወገን የወለዳቸው ልጆች ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል።

ወደ ኋላ ልመለስና አለቃ ታዬ ከጻፉት ላይ ስንመጣ ምናልባት ዛሬ አንዳንድ ፀረ አማራ የሆኑ ዘመናዊ ደራሲያን የሚገልጹት ታሪክ ትክክል አለመሆኑን ከላይ የተሰመረበት ሲሆን በእኔ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ የተዋሕደ ሕዝብ መሆኑን ባምንም ቅሉ የአማራው መሰረት ወልቃይት ነው። ዛሬ ክላሽ ኮፐ ጠበንጃ ታሪክ የሚያጽፍ በመሆኑ ወያኔ እነዚህን ወረዳዎች ወደ ትግሬ ለማስገባት ያደረገው ጥረት ከላይ ከተጠቀሰው ታሪክ ውጭ ነው። ለአንባቢያን ወልቃይት ማለት ታሪኩ ይህ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን የሚገኝበት በጎንደር ክፍለ ሀገር በወገራ አውራጃ ለም ወረዳዎች ናቸው። በነዚህ ወረዳዎች ውስጥ ታዋቂ የሁመራ ልማት ሲሆን የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ወድቆ የደርግ መንግሥት ሲመሰረት ሁመራን ጥር 1969 ዓም ኢዲዩ ዘርፏት ሲሔድ ሰኔ 1969 ዓም ደርግ "የመንጥር ጦር ሄደ ግንባር" እየተባለ ይዘፈንለት የነበረው የጦር ኃይል መልሶ ከያዘ በኋላ የመንግሥት ልማት በአንደኛ ደረጃ ተመደበች "የአረንጓደው ልማት" ይባልላት የነበረች የሁመራ ገበሬዎች አካባቢውን አስተራረስ የሚያውቁት ከዘመናዊው ምሁር ጋር አልተግባቡም። አርሶ አደሮች ለአርሻ መጽሐፍ አያስፈልግም ሲሉ ዘመናዊ ምሁራኖች ደግሞ በእንግሊዘኛ የተጻፈን መጽሐፍ መመሪያ አድርገው ማረስ አለብን ሲሉ አርሶ አደሮች እንዲህ አሉ

"በሬው ከሸዋ እራሹ ከጎንደር
ይጠፋል በቅርቡ የሁመራ መንደር"

እሉ እየተባለ ይሳቅ ነበር። የሁመራ እርሻ ልማት የጠፋበትን ምክንያት የግብርና ባለሞያዎች መርምረው ሊያቀርቡ ይገባል። ምሁራኑ በተማሩበት ትምህርት ብቻ በመመራት የአካባቢውን የመሬት ልማድ ባለመረዳት ነው። ዛሬ ያለን ትውልድ ታሪክ ለማወቅ ጥረት የማናደርግ በመሆኑ እንጂ ወልቃይት ማለት ሰፊና ትልቅ አገር ነበር። እድሜ ለቅኝ ገዥዎች ከወልቃይት እየተቆረሰ ወደ ሱዳን የገባው እሁን የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ መሀል ከመጣ በኋላ ነው "ዳሩ ዳር ሲሆን መሃሉ ዳር ይሆናል" እንደተባለው ወልቃይት ዛሬ መሀል መሆኑ ቀርቶ ዳር ሁኖ ይገኛል። ስለ ወልቃይት ማንሳት ማለት የጎንደሬዎች ብቻ አልያም ደግሞ አንዳንድ ሆድ አምላኪዎች የወልቃይት ልጆች የነሱ አስመስለው ያዩታል። በመሰረቱ በተለይ ወልቃይት የወልቃይቴ ልጆች አልያም የጎንደሬዎች ብቻ ሳይሆን የአማሮች አባት መፍለቂያ መሆኑን መረዳትና ዳር ደንበሩን ለማስጠበቅ መነሳት የአንድ ዜጋ ግዴታ ይመስለኛል። በእኔ እምነት ወልቃይቴ ማለት ጠባብነት አይደለም። ለምሳሌ ከነገሥታት የትውልድ ወረዳ ብንነሳ ስለ ቴዎድሮስ ሲነገር "ቋራ" ስለ አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ሲነገር "ስቆጤ" ስለ አጤ ዮሐንስ ሲነገር "ተንቤኔ" ስለ አጤ ምኒልክ ሲነገር "አንኮለሌ" የሚባለው የትውልድ መንደራቸውን ለመጥቀስ ነው። ከዚህ በላይ ምሳሌ እንደቀረበው ሁሉ አንዳንድ ልጆች ወልቃይቴ ነኝ ቢሉ ጠባብነታቸውን ለመግለጽ ብለው የተጠቀሙበት አይደለም። ወልቃይት ወደ ትግሬ ሲከለል




ታስበና ዛሬ ልጆቹን በሁት ከፈላቸው ወደ ሚለው ታሪክ ስንገባ ይሆን ይመስላል።

ወያኔ ሕውሓት ትግራይ ሪፓብሊክ ተብሎ የሚመሰረተው መንግሥት ከውጭ አገር ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት ለም መሬትና ባህር ማግኘት እንዳለበት ጥናቱን ለአንድ ዓመት ካጠና በኋላ በ1968 ዓም ሪፓብሊክ ትግራይ መንግሥት ዳር ደንበር ብሎ ባሰራጨው "ማኔፌስቶ" ለመጀመሪያ ግዜ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ከወሎ እንዲሁ አሸንጌን ከአሰብ አስተዳደር አሰብ እደቡን ጨምሮ የትግራይ ግዛት ነው ብሎ አወጣ። ይህን ገፀ ምድር ካርታ ከሳለ በኋላ ከወልቃይት ልጆች ቅይጦችንና ሆድ አምላኬዎችን መያዙ አይዘነጋም ይህ ታሪክ ከግቡ እንዲደርስ ከሰሜን አውራጃ ወደ ትግሬ የተከለሉትን ወረዳዎችና ከወገራ አውራጃ ወደ ትግሬ የተከለሉትን የወረዳውን ተወላጆች አንጋፋውን ኢዲዩ ወጣቱን ኢሕአፓ እያሉ በደርግ ተሹመው ስሜን አውራጃ ገዥ የነበሩት አስር አለቃ ገብረ ሕይዎት ገብረ እግዚአብሔር በሊማሊሞ ገደል ይሰዱአቸው ጀመር። ወያኔ ከአገር ውስጥ ያሉትን ብቻ ሳይሆን በስደት ዓለም ሱዳን ያሉትን የነዚህን ወረዳ ተወላጆች ጨርሷቸዋል።

ለአንባቢያን መሰረታዊ ታሪክ ማስጨበጥ የፈለኩት ወያኔን የተከተሉት በብዛት የኤርትራን መንግሥት ከፍ ለማድረግ ታጥቀው የተነሱ መሆናቸው ምልክቱ በ1968 ዓም "ማነፌስቶ" ላይ አሰብ ከትግራይ ሪፓብሊክ ውስጥ የተቀረፀች መሆንዋን ከዚህ ዝቅ ብሎ ያለውን ካርታ በጥሞና ተመልከቱት። በዚህ ወቅት ሻዕቢያ አሰብ በኤርትራ ውስጥ አለመተዳደሩን ከታሪክ ያውቅ ስለነበር የኤርትራ ግዛት አድርጎ አይቆጥራትም ነበር። ከወያኔ ማነፌስቶ ላይ ሲሳል እንዴት ያላለው ከቀደም ጀምሮ አሰብ አስተዳደር በባህረ ነጋሽ ውስጥ ተዳድሮ ስለማያውቅ ነው። አሰብን ወደ ኤርትራ እንዲሆን ጥረት ያደረጉት የዛሬው የኢትዮጵያ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ፤ ናቸው። በ1968 ዓም ከወጣው ካርታ ላይ ዛሬ አሰብ የትግራይ አስተዳደር ውስጥ ባትገባም ሌሎችን ከወሎና ከጎንደር የተከለሉትን እንሆ በትግራይ አስተዳደር ውስጥ እንዲሆኑ መደረጉ ከታሪክ ውጭ መሆኑን ከዚህ በፊት ደግሜ ደጋግሜ መጠቆሜን አረሳም። እኛ ብቻ ሳንሆን ራሱ የወያኔ ፈጣሪ ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ እንኳን እንዲህ ይላሉ።

ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፍወርቅ <u>አስር መጽሔት</u> 1990 ዓም ጋዜጠኛ ላደረገላቸው ቃለ መጠየቅ ጥያቄ "ወያኔ በ1968 ዓም ማነፌስቶ አሰብ ወደ ትግራይ ክልል አስገብተው ነበር። ስለዚህ እናንተ በዛን ሰዓት ምን አላችሁ?" መልስ ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ "እኛ ይህ ይመጣል ብለን አላሰብነም" የሚል መልስ ሲሰጡ ጋዜጠኛው እንደገና "የሪፓብሊክ ትግራይ ድንበር የተወሰነው ከጎንደር ወልቃይትን በመቁረስ እስከ ሱዳን ሲደርስ ከወሎ ደግሞ ሰቆጣ አሸንጌና አላማጣና ቆቦን ጨምሮ አሰብ ድረስ የሚሄድ ካርታ ነበር። የሕዝባዊ ግንባር በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠው መልስ ነበር?" ሲላቸው ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፍወርቅ "እዚህ ላይ መገንዘብ ያለበት ይሄ በ1968 ዓም የሕወሀት መግለጫ ምክንያታዊ ነበር ወይም አልነበረም ወቅታዊ ነው አይደለም" በሚል

ዘግተውታል፡፡ ከዚህ ላይ ታሪክን ጠንቅቀን እንድናይ ግድ ይላል፡፡ ከዚህ ዝቅ ብየም የምጠቅሰው ታሪክ ከጎንደር ወደ ትግሬ የተከለሉ ወረዳዎች በትግራይ ግዛት ውስጥ ለማስገባት የታሰበው ወያኔ ከተመሰረተ ከ1967 ዓም ወዲህ ሲሆን በሰነድ የተገለጸው ግን 1968 ዓም ነው፡፡




ወያኔ ሲመሰረት ሪፓብሊክ ትግራይ ካርታ

አቶ ገብረ መድህን አአርያ እና አቶ አብርሃም ያየህ የወያኔው ታላቅሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 34 የወጣው ስዕል ነው፡፡ የሕወሓት ማኒፌስቶ 1968 ዓም ከወጣው ላይ የወጣ ካርታ!



## ምዕራፍ 2

## "ወልቃይት ወደ ትግሬ ሲከለል ጎንደሬዎች ዝም አሉ?"

ትግራይን ከኢትዮጵያ ሊገነጥል የተመሰረተው ድርጅት ከወያኔ ኮት ላይ የኢሕአዴግን ካፖርት ደርቦ የኢትዮጵያን ሕዝብ አጭበርብሮ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም አዲስ አበባን ከያዘ በኋላ በ1968 ዓም ያወጣውን ገጸ ምድር ካርታ ከሥራ ላይ ለማዋል ሲል አሰብን ትቶ ከወሎና ከጎንደር የወሰዳቸውን ወረዳዎች በትግሬ አስተዳደር ውስጥ አስገብቶ ይፋ ሲያደርግ የጎንደር ተወላጆች በገጠር ያሉት ቀደም ሲል ጀምሮ በውጊያ የነበሩት ውጊያቸውን አጠንካረው ሲነሱ በከተማ ንዋሪ የሆኑ ታዋቂ ምሁራን ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት እንዲሁም በቋራ በኩል ወደ ቤሪ ሻንጉል የተከለሉትን ወረዳዎች አስመልክቶ አቤት እያሉ መሆናቸውን ሰነዶች ዋቢ ሲሆኑ ክቡር አቶ ታየ ረታ ግን ብቻቸውን ለፍልፈው የቀሩ መሆናቸውን በአደባባይ በመናገራቸው መልስ በማስፈለጉ ከዚህ የሚከተለውን እንድጽፍ አስገደደኝ፡፡

ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓም የሲያትል ዋሽንግተን የቅንጅትና ሕብረት ያዘጋጁት ስብሰባ ነው ተብሎ በዚሁ ቀን ተነግሮነአል፡፡ የኢትዮጵያን ደንበር ያውቃሉ የተባሉ ክቡር አቶ ታየ ረታ እና ክቡር አቶ ሽፈራው እንቆ ባህሪ መጥተው ነበር፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ክቡር አቶ ታየ ረታ ሲናገሩ "ወልቃይት ሁመራ ወደ ትግሬ ሲከለል ብቻዬን ለፍልፌ ቀረሁ! ጎንደሬዎች ዝም አሉ "ሲሉ ተናገሩ፡፡ እኔም ጎንደሮች ዝም አለማለታቸውን አሳስቤአለሁ፡፡ ከቤቴ መጥቼ ቀደም የታተሙ መጽሔቶችን ባገላብጥ እርሳቸው የጻፉት ሳላገኝ ቀረሁ፡፡ ምናልባት እኔ ካለኝ ሰነድ ውስጥ ሳይሆን ቀርቶ ከሆን ቢያብራሩልኝ ደስ ይለኛል፡፡ እርስዎ የጻፉት ሠነድ ቢኖርም እንኳን ጎንደሮች ዝም አላሉም፡፡ ይህን በተመለከተ ማብራራት ያስፈልጋል፡፡ ወያኔ በወልቃይት ተወላጆች ላይ የፈጸመው ግፍ በተመለከተ ሰሚ ጠፍቶ እንጂ ትግሉ ዛሬ ሳይሆን ከ1973 ዓም መጨረሻ ጀምሮ ነው፡፡

ከሩኝ የተመሰረተው በወልቃይት ጠገዴ ጠለምት ልጆች ነበር የሚሉ አሉ፡፡ ኢዲዩ ሕዝቡን አስፈጅቶ ሱዳን ሲገባ ኢሕአፓ በራሱ ችግር ሲፈርስ በአቶ ጎሺ አግደውና በአቶ ምትኩ ባንቲ ላይ የካቲት 18 ቀን 1972 ዓም ከገደላቸው በኋላ ከአቶ አሰረስ አግደው ቤተሰቦች ጋር ሲዳማ ከአርማጭሆ ወደ ሽንፋ ገብቶ መሳሪያውን ለሱዳን አስረክቦ አውሮፓና አሜሪካ ሲገባ መሳሪያውን ለጎንደር ሳይሆን ለሱዳን ሰጥቶታል፡፡

ከጅብሃ ጋር የነበረው ኢሕአፓ በ1973 ዓም መጨረሻ ላይ በወልቃይት አልፎ ግጨው ከተባለው በርሃ ሲሰፍር ቀስ በቀስ ከአርማጭሆ ሕዝብ ጋር የሻከረውን ጠብ ለማለሳለስ ጥረት በሚያደርግበት ወቅት በ1975 ዓም ጥር 18 ቀን የ84

ዓመት አዛውንት ቢትወደድ አዳነ መኮንንንና አቶ አበበ ጆንበርን ሌሎችንም በመግደሉ ከአርማጭሆ ሕዝብ ጋር ችግር ገብቶበት ወደ ቋራ ሲለቅ የትግራይ ትውልድ ዘር የነበራቸው አቶ ደርጋ ደስታ ትብብር በማድረግ ወያኔን ከወልቃይት ወደ አርማጭሆ እንዲገቡ ሲደረግ የቆላው ሕዝብ በነበሩት ድርጅቶች እምነት ባለመኖሩ ምክንያት ፥ከፋኝ፥ ብሎ ወያኔን እየወጋ ደርግንም እየወጋ ብዙ ዓመታት ከቆየ በኋላ የርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም መንግሥት አቢዮታዊ ፋኖ ብሎ የተወሰነ እርዳታ ያደርግላቸው እንደነበር አይዘነጋም:: ወያኔ አዲስ አበባን ሲይዝ በመጀመሪያ ኤሊኮፍተር የጣሉበት ከፋኞች ነበሩ:: እነዚህን ጀግኖች ለወያኔ መቅሰፍት የነበሩትን አንዳንዶች ቀንበር ሲጠብባቸው ከወያኔ ጋር በሽምግልና እንዲገቡ ተደርገው ገቡና ተገደሉ ለምሳሌ ኪዳነ ማርያምን መጥቀስ ይቻላል::

ሾተል አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሰኔ 1985 ዓም ገጽ 24 "ኢሕአዴግ ጎንደር ከተማን ሲቆጣጠር እየገሰገሰ ሲመጣ ለስምንት ቀናት ያህል በከተማው ዙሪያ ከፍተኛ የሆነ የመከላከል ተግባርን ካከናወኑ በኋላ ኪዳኔና የሽምቅ ጦር አባላት የሁኔታውን መበላሸት በማጤን ስልታዊ ሽሽት በማድረግ ወደለመዱት በርሃ ገቡ:: ኢሕአዴግ ጎንደርን ተቆጣጠረ:: ከዚያም በኋላ በሰሜን ጎንደር ክልል በአርማጺጋ፤ በጠለምት መሐልና በተከዜ ዳርዳር በአርማጭሆና በማያፀብሬ በብራ፡በዳንሻና በመሳሰሉት በርሃዎች እየተንቀሳቀሱ የኢሕአዴግን ጦር በተደጋጋሚ የገጠሙ ሲሆን እንደሚታወቀው ኪዳን ማርያምና የተወሰኑ ጓደኞቹ በምኅረት እንዲገቡ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሽማግሌዎችን በመላክ ከፍተኛ ጥረት ካደረጉ በኋላ በሃያ የማያንሱ ካህናትና ሽማግሌዎች የየአድባራቱን መስቀል በመያዝ አርማዛሊ ከተባለው በረሐ ዳር በአርማጺጋ ውስጥ ከሚገኙት ከእነ ኪዳን ማርያም ጋር ጥር 10 /1985 ዓም በመገናኘት ድርድር ተጀመረ" ሲሉ ጽፈዋል::

ወልቃይት ጠገዴንና ሌሎችንም ወረዳዎች በተመለከተ መጽሔቶች ብዙ መጣር ጋዜጦች ላይ የወጡትን ጹሁፎች ሰብስቦ ማንበብ የወልቃይት ሕዝብን ትግል ለመረዳት አያዳግትም:: ክቡር አቶ ታዬ ረታ ማስታወሻ ያ እንዲሆናቸው ከዚህ በታች ጸሐፊዮች በመጽሔትና በጋዜጣ የጻፉትን ስማቸውንና የታተመበትን ዓመተ ምሕረት ጠቁሞ ማለፍ በማስፈለጉ ትንሽ ልቀጠር:: በአገር ውስጥና ውጭ አገር የሚኖሩ የጻፉት ነው!

## መጽሔት

1ኛ ሙዳይ መጽሔት መጋቢት 1985 ዓም "የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ አዲሱን ካርታ አልተቀበለውም"የሚለውን ጹሑፍ ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ የመጀመሪያውን ይመልከቱ:: በውጭ አገር የወልቃይት እና ጠገዴ ሕዝብ ጉዳይ አስተባባሪ ኮሞቴ ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 2ኛ 11 ቁጥር 2 1996 ዓም "መልስ ያጣ የወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ ዕንባ"ተብሎ የወጣውን መግለጫ ከዚሁ ምዕራፍ በመጨረሻው ላይ ያለውን ይመልከቱ::



3ኛ አያናአዝጊ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም ገጽ 38 "ማርያም ሁመራይቱ ወይ ፍረጅ ወይ ውረጅ"

4ኛ መልዓከ ሰላም ሲሳይ አየለ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም ወልቃይት በትግራይ እና በጎንደር ሕዝቦች መሀል የተቀበረ ፈንጅ

## ጋዜጣ

1ኛ አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅፅ 7 ቁጥር 8 መጋቢት 6 ቀን 1993 ዓም "እ! ወልቃይት"
2ኛ አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 6 ጥር 24 ቀን 1993 ዓም "እ!ወልቃይት"
3ኛ አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 7 የካቲት 21 ቀን 1995 ዓም "እ!ወልቃይት"
4ኛ ጎሹ ገብሩ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 3 ጥቅምት 22 ቀን 1995 ዓም "የወልቃይት ጠገዴ ጀግና ሕዝብ ያስጠቃው ማን ነው?"
5ኛ ጎሹ ገብሩ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 4 ሕዳር 22 ቀን 1995 ዓም "የወልቃይት ጠገዴን ጀግና ሕዝብ ያስጠቃው ማን ነው?"
6ኛ የሰሜን ጎንደር ተወላጆች በጀርመን ሞገድ ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 20 የካቲት 2 ቀን 1987 ዓም እውነተኞቹ የወልቃይት ተወላጆች በወያኔ ባንዳዎች አይወናበዱም::

## መጣጥፍ

1ኛ አሸብር ተቆርቋሪ የሌለው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ አሁንም ቢሆን ወያኔ በቆፈረቻቸው ጉድጓዶች የቁም ሥቃይ እያየ የወገን ያለህ ይላል::

2ኛ በአውሮፓ የሚገኙ የወልቃይት ተወላጆች መሰደብ ከአገር መቀማት አይብስም ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል::

3ኛ በወልቃይት ሕዝብ ላይ የደረሰው ችግር ሕዝቡ እንዲወያይበት የቀረበ የመንደርደሪያ ሐሳብ ጹሑፍ (ወልቃይት ሳይጠፋ በሕብረት እንግፋ) በሚል ርዕስ የተጻፈ:: ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው ሠነዶች እንዳሉ ሁነው ሌሎችም ስለ ሌላ ታሪክ ሲጥፉ እግረ መንገዳቸውን ወልቃይት የትግሬ አለመሆኑን እያስመሩበት አልፈዋል:: ይህ በጎንደሬዎች ብቻ ሳይሆን ሌሎች ኢትዮጵያውያን የተጻፈት ነው::ለማንኛውም ባይበዛም ትንሽ ጠቆም ሳድርግ::

ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 6.1992 ዓም ገጽ 36 "በሁመራ ዘንድሮ ከ200 ሺ ኩንታል በላይ ሰሊጥ ተመረተ አዲስ ዘመን ታህሳስ 25/92 ይላል" በሙሻዘር አምድ ሲያቀርብ መልሱ ደግሞ እንዲህ ይላል "ሁመራ ትግራይ